
ይስማዕከ ወርቁ

# ዴርቶጋዳ




ልቦለድ

፲፱፻፺፩ ዓ.ም
አዲስ አበባ

All Rights Reserved to Yismake worku.

🖎 ዘፈሪቶ ወዘሠረቶ በስልጣነ ክ.ን ወጥበብ ውጉዝ ለይኩን፡፡ © ይስማዕከ ወርቁ-፳፻፩

# DERTOGADA

A Novel by Yismake Worku

የመጀመሪያ ዕትም ሚያዝያ ፳፻፩ ዓ.ም

ሁለተኛ ዕትም ሰኔ ፳፻፩ ዓ.ም

ሦስተኛ ዕትም ሐምሌ ፳፻፩ ዓ.ም

አራተኛ ዕትም ነሐሴ ፳፻፩ ዓ.ም

አምስተኛ ዕትም ጥቅምት ፳፻፪ ዓ.ም

ስድስተኛ ዕትም ህዳር ፳፻፪ ዓ.ም

ሰባተኛ ዕትም ታህሣስ ፳፻፪ ዓ.ም

ስምንተኛ ዕትም ታህሣስ ፳፻፪ ዓ.ም

ዘጠነኛ ዕትም ሚያዝያ ፳፻፪ ዓ.ም

**ዋና አከፋፋይ ፡- አይናለም መጻፍት ቤት**

**አድራሻ፡-ከብሔራዊ ቴአትር ቤት ጀርባ**

**☎ 011 550 58 44/011 550 58 45**

የሽፋንና የውስጥ ዲዛይን፡-ይስማዕከ ወርቁ
ኮምፒዩተር ትየባ፡- መላኩ ኃ/ሚካኤል

**E-mail: ramatohara@gmail.com**

## መግለጫ

በዚህ በተራቀቀና በህዋ ቅርምት (space exploration) ዘመን በአማርኛ ተፅፎ ለመነበብ በቂ ብቃት ያለው ፊር ቀዳጅ ልቦለድ እነሆላችሁ፡፡

ሀ) ቋንቋው እስከነ ታሪክ አወቃቀሩ እንከን አይወጣለትም፤ ከዚያም ጋር ከማንም ሌላ ፀሐፊ የሚለየው ይስማዕከ የራሱ «እንትን» አለው (style)::

ለ)ብዙ ሳይንስ ፊክሽን አንብቤም በሲኒማ አይቼም አውቃለሁ፤ ይሄ የምታነቡት ፀሐፊውንና እንዲፅፍ ቀስቀሰው ያስቀጠሉትን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ስናነበው፣ ከማንኛቸውም ይስተካከላል፡፡

ሐ) ትረካውን ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ስንከተለው ልብ አንጠልጥል ነው፣ አንድ ነጠላ ታሪክ ይዞ ችክ አይልብንም፣ የብዙ ውስብስብ ታሪኮች ጭማቂ ሆኖ አንድ ገፅ ስንገለብጥ አዲስ ነገር እናገኛለን፤ በድርጊት የተሞላ ነው (ፍጥነቱ)፡፡

መ) ሳይንስ፣ ስለላ፣ ሮማንቲክ፣ ታሪካዊ ልቦለድም ጭምር ነው....ከዚህ እንጻር፣ ትስስሮሻቸው እስካሁን ያልታዩንን የተለያዩ ክስተቶች አቀራኝቶ አቅርቦልናል፡፡ ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን ያስተሳሰረ ተሻጋሪ ልቦለድ ነው፡፡

ሠ) ይሄ የመጨረሻው ነጥብማ....ከሚያውጠነጥናቸው ሀሳቦች አንዱዋ ብቻ እቻት፡፡ ለቁሳዊ ሀብትና ለአዕምሮአዊ ሀብት ስለሚደረግ ትንቅንቅ፡፡ ደም ሀገር ወዳድነት... ማን ለራሱ ሲል ምን ተከፍሎት ማንን ወይስ ምንን ይሸጣል? ማንስ ለሀገሩ «እስከመጨረሻዋ ደም ጠብታ» ይፋለማል? ወዘተ... የተቀረውን አንባቢ ከወዘተ ጋር ቢወያይበት ይመረጣል፡፡

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

## ምስጋና

የሁሉም ነገር አባቴ ዓለሙ ቢያድጌ ጌታሁን ...ያንተን ታላቅ አባትነት መመስከሪያ ቃል ካላቸው ገና ከዘመናዊው ትምህርት ጋር በደንብ ሳልተዋወቅ ጀምሮ የገዛህልኝ መጻሕፍት ይመስክሩልኝ። እነሆ የልጅ ቡራኬ።

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር (አቦይ) የዚህ መጽሐፍ ረቂቅ በኔ ቢረቀቅም ባንተ ደምቋል። በየትኛውም ዘመን ውስጥ ከየትኛውም ትውልድ ጋር መኖር የመቻልህ ምስጢር ይህ አንዱ ፈርጁ ነው። አዲስ ዘመን፣ አዲስ ትውልድና አዲስ እሳቤ አንተን አያስፈሩም። ያለፈኝን ዘመን ባንተ ኖሬያለሁና እነሆ ስብሐት ለአብ!

ጋሼ የሻው ተሰማ (ደራሲና ሀያሲ) በሌላ ቅንፍ ውስጥ የኮተቤው ወጌሻ....በጥበብ እጅ ሲታሸ የማይጠገን የስነፅሁፍ ውልቃት፣ የማይጠግግ ወለምታ እንደሌለ አይቻለሁና እነሆ ብዕሬን ለምስጋና አነሳለሁ። ደራሲና ገጣሚ በዕውቀቱ ስዩም፣ ዶ/ር ዮፍታሄ ስዩም፣ ደራሲና ገጣሚ እንዳለጌታ ከበደ፣ ደራሲና ገጣሚ ዘላለም ጌታቸው፣ ዶ/ር ከፈለኝ፣ አሜሪካዊው ደራሲ ዳንኤል ጆንሰን ሁላችሁንም ከጥበብ ማዕድ አይለይብኝ።

ገጣሚ በለው ገበየሁ በቅንፍ ውስጥ የኔ ገማልያል... እነሆ የተዋረስነው ጋኔን ስሙ ሥነ ጽሁፍ ነውና በጠበልም በመገረፍም በስቅላትም አይለቅም። ብንሞትም አብሮን አይሞትም። እንግዳ ወርቅ ሀብቴ በቅንፍ ውስጥ የኔ ቤተ መጻህፍት... ያነበብከውን ሁሉ ለማዳመጥ መቃብራችን እስኪቆፈር ያቆየናል። ታድለን!

ፀጋ እንዳርጌ....ለዛ ሁሉ ልፋት ምስጋና በቂ ነው ወይ? ከሆነ እነሆ እስከ መጨረሻው ጊዜ የሚያቆይ ምርቃት ጀባ ብያለሁ። መላኩ ኃ/ሚካኤል፣ እመቤት እንዳለ፣ ብሩክ ተስፋዬ፣ቃልኪዳን ጌታቸው፣ ትዕግስት ሰለሞን፣ ፋሲካ ጌታቸው፣ ናርዶስ ፀጋዬ፣ መ/ር አላዛር ጌታቸው፣ አቶ ደረጀ ዋለ፣ ጌትነት ዳናና ድልዓለም አዩ መርቄያለሁና...አሜን በሉ።



## መግለቢያ

ከላይኛው ደራሲ ዘንድ የተላከ ታላቅ መልእክ በመንፈቀ ሌሊት በሬን በርግዶ ገብቶ ከእንቅልፌ አባነነኝ። ራሴን ነዝንዝ በራሴ ላይ ተኝቼ ነበር። ከወርቃማ ክንፉ ላይ አንድ ላባ ነቅሉ ብዕር ቀርፆ ሰጠኝ። በታላቅ ሰሌዳ ላይም «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ብሎህ ጻፍ አለኝ። ከነገረኝ ቃል አንዳች ባጎድል ከህይወት መፅሐፍ ላይ እንደሚሰርዘኝም አስጠነቀቀኝ።

በሰጠኝ ብዕር ከላቤ ወዝ ቀለም እየጠቀስኩ ስከትብ የነገረኝን ቃል የሚናገሩ ገፀ ባህርያት (አምሳለ ሰብዓት) ከዘመኔ ጨለፍኩ። የፈጠርኳቸው ጥቂት አምሳለ ሰብዓት በዘመኔ ከማውቃቸውና የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ጋር በሥጋ በነፍስ ተዛመዱ። በ'ርግጥ እግዜር የፈጠራቸው ገፀ ባህርያት የተሠሩት ከጭቃ ሲሆን እኔ መፍጠርን ከፈጠረኝ ተምሬ የፈጠርኳቸው አምሳለ

ሰብዓት ግን የተጨለፉት ከሰው ላይ ነው። ከ'ኔና ከመሰሎቼ ግዘፍ ነስተው፣ ከሰው ሥጋ ሥጋን፣ ከሰው ምኞት ምኞትን፣ ከሰው ህልም ህልምን...... ወስደው ፍፁም ሰው ፍፁም እነሱን ሆነው ተፈጠሩ።

ሆኖም እኔ በፈጠርኳቸውና የላይኛው ደራሲ በፈጠራቸው አምሳለ ሰብዓት መካከል አንድ ልዩነት አለ። የላይኛው ደራሲ የፈጠራቸውን ገፀ ባህርያት ይገድላቸዋል። እኔ ግን አልገድልም፤ አላድንምም። ከሞቱም 'ራሳቸው ይሞታሉ እንጂ! ከዳኑም ራሳቸው ይድናሉ እንጂ። እኔም ከእነሱ ያልተሻልኩ ነኝና። ለመሞታቸውም ለመትረፋቸውም ተጠያቂ አለመሆኔን ስነግራቸው ፈነጠዙ። እንዲህም አልኳቸው። «እኔ ብዕር እንጂ ሰይፍ የለኝም። አልጠብቃችሁም። ለጉስቁልናችሁ....ለመደወያችሁ ሁሉ ማንም ተጠያቂ አይሆንም። ራሳችሁን አድኑ። ሁላችንም የራሳችን በሽተኞችና የራሳችን ዶክተሮች ነን። እኔ ራሴ የራሴ ታማሚ የራሴ አስታማሚ የራሴ ዶክተር የሆንኩ የላይኛው ደራሲ የፈጠረኝ አስተኔ ገፀ ባህርይ ነኝ። ሁላችንም የላይኛው ደራሲ የፈጠረን ገፀ ባህርያት ነን። አዎ፤ በእርግጥ ...እኔ ፈጣሪያችሁ ነኝ። ስለናንተ ሐጢአት ግን በመስቀል ላይ አልቸነከርም።...... ስለእናንተም ከእናንተ በላይ አላውቅም።...እኔ ከላይኛው ደራሲ የምለይበት አንድ ሌላ ነገር... ብትሞቱብኝ በእኔ ዘንድ የማወርሳችሁ ገሀነምና መንግሥተ ሰማያት አለመኖሩ ነው። ገሀነሙም መንግሥተ ሰማያቱም ያለው ከእናንተ ውስጥ ነው። በምድር ላይ ኃጥዕና ጻድቅ እኩይና ሰናይ ገፀ ባህርይ የለም። ከእናንተ በተቃራኒ የቆመ ኃይል እኩይ ሲላችሁ እናንተ ደግሞ መልሳችሁ እኩይ ትሉታላችሁ። ሁሉም ለራሱ ሰናይ ገፀ ባህሪ ነውና። ሰናይ እኩ ስል አላዳላም። ደረስኳችሁ እንጂ አልደርስባችሁም» ብዬ ስነግራቸው ሁላቸውም ተደሰቱ። የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህሪያትም ጋር ተቀላቀሉ። ከአምሳለ ሰቦቼና

የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ከህይወታቸው እየጨለፍኩ ይህን መጽሀፍ ጽፌ ስጨርስ ከተኛሁበት የቀሰቀሰኝ መልአክ ቀሪውን የህይወታቸውን ምስጢር እንዳልናገርባቸው ፍም በመሰለ ነበልባላዊ ሰይፉ ከንፈሮቼን አተማቸው። አስቀጥሎም ‹‹ዕቀብ ቃለ ተነብዮቱ ለዝንቱ መጽሐፍ እስመ በፅሐ ዘመኑ›› ብሎ በጥንታዊዉ የግዕዝ ቋንቋ ተናግሮኝ ክንፉን እያማታ ወደ መጣበት ተመለሰ። ‹‹ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል ጠብቀው›› ማለቱ ነው። የላይኛው ደራሲ ‹‹የፈጠርኩትን ላባ የት አባህ ጥለኸው መጣህ!?›› ብሎ እንዳይቆጣው የፈራ ይመስል ከወርቃማ ክንፉ ላይ ነቅሎ የሰጠኝን ላባም መልሶ ክንፉ ላይ ተክሎት ነበር የበረረው።

✍ ይስማዕከ አዶኒ



# ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ

ለሳይንቲስት ኢንጂነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ



# ቅድመ ታሪክ

**አሜሪካ፡-** በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1989 ዓ.ም። በአሜሪካ አየር ኃይል ቢሮ ውስጥ የተቀመጠውን ጥቁር መዝገብ የክፍሉ ዋና አዛዥ ሲያገላብጡት ከቆዩ በኋላ ሰፊው ጠረጴዛ ላይ በብስጭት ወረወሩት። የአሜሪካ አየር ኃይል አባል የነበረው ጌራ ከተልዕኮው እስከዛሬ አልተመለሰም። ባለክንፉ ፓይለት በመባል ይወደስ የነበረው ጌራ ከተሰወረ ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካ አየር ኃይል አባላትና የጦር መኮንኖች ስሙን ሳያነሱት ውለው አያውቁም። ይህ ኢትዮ - አሜሪካዊ ወጣት ፓይለት ከመሰወሩ በፊት በአሜሪካ የህዋ ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ስሙ ከገነነው እውቁ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ጋር በተደጋጋሚ አብሮ ታይቷል ይባላል። ከመሰወሩ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ኢንጂነር ሻጊዝን መርምሮት ነበር። እሱ ግን ስለጉዳዩ እንደማያውቅ ተናግሮ ድርቅ አለ። በአነስተኛዋ የጦር አውሮፕላን ወደ አፍሪካ እንደበረረ የሚጠረጠረው ጌራ ግን እስከ አሁን ሊገኝ አልቻለም።

ይህ ከሆነ ከሁለት አመት በኋላ እውቁ የሚሳዬል ባለሙያ ኢትዮ-አሜሪካዊዉ ሳይንቲስት ኮሎኔል ፍስሐ ስለረጅም ርቀት ተወንጫፊ ሚሳዬል የጀመረውን ቀመር በጅምሩ ጠረጴዛው ላይ ትቶ ተሰወረ። "ኢትዮጵያ" በሚል ቅጽል ስም የሚጠሩት የሥራ ባልደረቦቹ ደርቀው ቀሩ። ስለ ኢትዮጵያ በስሜታዊነት ሲናገር ይቀልዱበት ነበር። አንዳንዴም «....አንተ ሰው!..... ወይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነህ! ወይም መንግሥቱ ኃይለማርያምን ውጠኸዋል!...." እያሉ ሲቀልዱበት ስቆ ዝም ይል ነበር። ይህ ኢትዮ-አሜሪካዊ የሚሳዬል ሳይንቲስት ከጭንቅላቱ በቀር ይዞት የጠፋው ቤሳ ቤስቲን የለም እተባለ ቢወራም ሀብቱን ግን ከመሰወሩ በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንዳሸሸ የአሜሪካ የመረጃ ሰዎች ደርሰውበታል ይባላል። ይህ ሰው በጠፋ በሶስተኛው ቀን የናሳው ሻጊዝ እጅጉ ከአንተ ጋር አብሮ ታይቷል በሚል ተመርምሮ ነበር። እሱ ግን "...አሁንስ ከኢትዮጵያ ያመጣችሁት ዶሮ ካለ እሱም ቢጠፋባችሁ እኔ ዘንድ እንዳትመጡ ስጋሁ" ሲል ተሳለቀ።

**እስራኤል፡-** መጋቢት 1990 ዓ.ም። በቴልአቪብ አቅራቢያ ምድር ውስጥ በተገነባው ህቡዕ የምርምር ጣቢያ ውስጥ በሥራ ከተጠመዱትሳይንቲስቶች መሀል ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች ሳይታሰብ የውሃ ሽታ ሆኑ። እነዚህን ሳይንቲስቶች ለመያዝ የእስራኤል ኮማንዶዎች ያልመነቀሩት ጉዋዳ ጎድጉዋዳ የለም ነበር። ነገር ግን እስከ አሁን ሊያገኙዋቸው አልቻሉም።

**ሰሜን ኮሪያ፡-** መስከረም 1991 ዓ.ም። የኮሪያ ዘማች ከነበሩትና ኮሪያ ከቀሩት ኢትዮጵያዊ አባቱ እና ከአንዲት ኮሪያዊት የተወለደው ኢትዮ-ኮሪያዊው ሳይንቲስት በሮቦቶች ከሚታገዘው ህቡዕ

የኒውክሰር ማብላያ ጣቢያ መሰወሩ በምስጢር እንዲያዝ ተደረገ። ፍለጋው እስከ አሁን ቀጥሎ ነበር.... የበላው ጅብ ሲጮህ አልቻለም እንጂ።

**ህንድ፡-** ነሐሴ 1992 ዓ.ም። እውቁ የኮምፒዩተር ሳይንስ ሊቅ ግርማቸው ዘለቀ የሂማሊያ ተራራዎችን ለመጎብኘት እንደሄደ እስከዛሬ አልተመለሰም። በሄሊኮፕተር የታገዘው የህንድ ፖሊሶች ሀሰሳ መና ሆኖ ቀረ። በሂማሊያ ተራራዎች መሃል ቀልጦ የቀረው ግርማቸው ለህንድ አስፈላጊ ሰው ነበር ይባላል።

**ሩሲያ፡-** ጥቅምት1994 ዓ.ም። ወደ ቀድሞዋ ሶቭዬት ህብረት ለትምህርት ከተላኩት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ከመሔዱ በፊት "አሞራው" በሚል ቅጽል ስም ይጠራ ነበር። ባለብሩህ አዕምሮ ከመሆኑም በላይ ራሺያ ያየችበት ልዩ ተሰጥኦው በቀላሉ እንዳትለቀው ግድ አላት። ነገር ግን የራዳር ቴክኖሎጂ ሳይንቲስቱ "አሞራው" ከሩሲያ እጅ ከወጣ ከአራት አመት በኂላ አንድ የሩሲያ ጋዜጣ የመጥፋቱን ዜና አተመው።

**ቻይና፡-** ታህሣሥ 1995 ዓ.ም ኢንጂነር ሻጊዝ በምስጢር ወደቻይና በሮ ነበር። ባልታወቀ ምክንያት ድርድሩ አልሰመረም። እውቁ የናሳው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ለቻይና የህዋ ምርምር ተቅዋም እንዲሠራ ቻይና ያቀረበችለትን ረብጣ ገንዘብ ረግጦ ሆንግ ኮንግን በለቀቀ ማግስት በቻይና የህዋ ምርምር ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ የነበረው ኢንጂነር ኢዩኤል አጥናፉ መሰወሩ ከቻይና የደህንነት ሰዎች ጆሮ ደረሰ።...... አንዲት ድምጽ አልባ አውሮፕላን ከቤቱ ጀርባ በድቅድቅ ጨለማ ስታርፍ ኢዩኤል ያለውን ሀብት በሙሉ በባንክ ወደ ኢትዮጵያ ለአንድ መነኩሴ አዛውሮ መመለሱ ነበር። መነኩሴው ደውለው ገንዘቡ እንደደረሳቸው ከነገሩት ከአርባ ደቂቃ በኂላ ከቤቱ ጀርባ ባረፈችው ድምጽ አልባ አውሮፕላን ቻይናን ለቆ ወጣ። ሆንግ ኮንግ በቻይና ኮማንዶዎች ብትታመስም ኢትዮጵያዊዉ የቻይና የህዋ ሳይንቲስቶች ባልደረባ የትም ሊገኝ አልቻለም። የቻይና የደህንነት ሰዎች የኢዩኤልን መሰወር ከኢንጂነር ሻጊዝ ወደ ቻይና መጥቶ መመለስ ጋር ቢያያዙትም እስካሁን ግን የተረጋገጠ ነገር አልተገኘም።

**ኩባ፡-** ጥር 1995 ዓ.ም። ፊደል ካስትሮ አንድ መርዶ ተነገራቸው። መርዶውን እንደሰሙ ወዲያው ላልተወሰነ ጊዜ ከኩባ ማንም እንዳይወጣ አዘዙ። የኩባ ኬላዎች በሙሉ ተዘጉ። የኩባ አውሮፕላኖችም ላልተወሰነ ጊዜ ከበረራ ታገዱ። በዛች ቀን ያልተፈተሸ ነገር ቢኖር የፊደል ካስትሮ ኪስ ብቻ ነውም ተብሎ ተቀልዷል። ተራ የህዝብ ማመለሻዎችና የቤት መኪናዎች በየመንገዱ በሰልፍ ተፈተሹ። ከሰማይ ጠቅስ ፎቆች እስከ ደሳሳ ጎጆዎች ተመነቀሩ። ኩባ ደብቃ ያኖረችው ኢትዮጵያዊ የሜድካል ላቦራቶሪ ሳይንቲስት ግን የትም ሊገኝ አልቻለም። የትም!



## አመክንዮ

**ኢትዮጵያ፡-** 1961 ዓመተ ምህረት። ጀምበር በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ልትጠልቅ አቅላልታ ነበር። አንድ የተበሳጨ መነኩሴ በብስጭት የምንኩስና ቆቡን ከራሱ ላይ መነጨቀው። ከራሱ ላይ የመነጨቀውን የምንኩስና ቀይ አስኬማ ከአዲስ አበባ እምብርት አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ግርጌ ወርውሮ ሲጥለው በዛ የሚያልፉ መንገደኞች በትንግርት እየተመለከቱት ነበር።

ከአራዳው ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በታች ወደሚገኙት መሸታ ቤቶች እየተገላመጠ ወርዶ አማርጦ ገባ። ሲጠጣ ቢያመሽም ሽንቱ ከመምጣቱ በቀር ፍንክች አላለም ነበር። አሁንም ብቻውን እየተበሳጨ ከማንም ጋር ታንቲራ ሳይገጥም የጠጣበትን ሸኽሬታ ከፍሎ ሲወጣ በምናምንቴ የተወጠቀችውን ከረጢቱን በጉያው አጥብቆ ይዞ ነበር። "ወይኔ ዲዲሞስ!" ይላል በየደቂቃው። "ከአሁን ወዲህ ማንም አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ! ማንም! .....እኔ አያሌው በላይሁን ነኝ። አያሌው በላይሁን! .....አያሌው በላይሁን ነኝ!.... አያሌው ጀግናው! .....ጀግናው አያሌው እንደ ዝንጆሮ ጭሮ ያደገው! ....ማንም ከአሁን በኂላ አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ!..ማንሽም አባ እንዳትይኝ! አባሽን ፈልጊ!....." እያለ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ተመለሰ። ሽንቱ ፊኛውን እንደ ንፋፊት እንደ ወጠረው ነበር።

ከአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን በረጅሙ እያንፎለፎለ "አንተ ድንጋይ! አሸናብሃለሁ!..." ሲል ባካባቢው የሚያልፉት ሰዎች መንገዳቸውን ገተው መሳቅ ዠመሩ።

"አንተ ድንጋይ! ...... አሸናብሃለሁ። ....ይኸው እኔ ግን አለሁ ..... እንቁልልጭ! አንተ ግን ድንጋይ ሆነሃል .....ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ተው ብየህ አልነበረም?..... አንተ ድንጋይ!..... ክፉ ቀንን ማለፊያ ጥበብ አልነገርኩህም ነበር?.... አንተ ድንጋይ!..... ሆን ብለህ ነው!...... ሆን ብለህ !....ክፉ ቀንን በጥበብ ከማለፍ በላይ ጥበብ የለም! ...አንት ድንጋይ! ....ይህንም ነግሬህ ነበር። ይህቺ ደም መላስ የለመደች ሀገር የምትለወጥ መስሎሃል! .....ቴዎድሮስን በላች! አልተለወጠችም።......ገብርዬን በላች! አልተለወጠችም። ....ምኒልክ ደከመላት!..አልተለወጠችም።...... ፋሲልን...በላች! አልተለወጠችም። አሉላን በላች! አልተለወጠችም! አንተንም በላች አልተለወጠችም!....... የበላይን ደም ጠጣች! ይኸው አልጠረቃችም። ስንት ጀግኖች ሞቱላት.........አልተለወጠችም። አልነገርኩህም?! .....ጴጥሮስ! አልነገርኩህም?! ....አትሰማም። ወይኔ ዲዲሞስ! ወይኔ አያሌው በላይነህ! ...አንተ ብትኖር ኖሮ ይሄኔ አቡነ ዲዲሞስ እባል ነበር። የዚህች ሀገር ዕጣፋንታ በእጃችን ይወድቅ ነበር። እንለውጣት ነበር። ግን ሞትክ! ተው እያልኩህ ሞትክ! ጵጵስና ሳትሾመኝ ሞትክ።

ይኸው እኒህኛው ጳጳስ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔት እንኳ ያድርጉኝ ብላቸው ከለከሉኝ። አባ ዝንበሩን ሾሙት። አንተ ብትኖር ግን ወንበዴዎች ጳጳስ ሆነው አይሾሙም ነበር። እኔና አንተ የምናውቀው የዚህች ሀገር ውድ ምስጢር በወንበዴዎች እጅ አይገባም ነበር። አፈር ብላ!....አፈርስ በልተሃል አንተ ድንጋይ! እሸናብሃለሁ። አንተ ድንጋይ ስልጣን ፈልጌ እንዳይመስልህ! አበምኔትነት ስልጣን አለመሆኑን ታውቃለህ። ጵጵስናም ተራ ነገር መሆኑን አታጣውም። ለምን ስልጣኑን ሳትሰጠኝ ሞትክ? ለግሌ እንዳልሆነ እያወቅህ! ለዚህች ሀገር ታላቅ ሥራ ልንሠራ ተስማምተን ከዳኸኝ አንተ ድንጋይ። እሸናብሃለሁ። ...አንት ድንጋይ! ጓደኞችህ ተመችቷቸው በማርቼዲስ ሲንሸራሸሩ ይኸው አንተ ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ድንጋይ! እሸናብሃለሁ..." እያለ ሲለፈልፍ አንድ ወጣት "ድንጋይ አይደለም! ....ድንጋይ አይደለም!..." እያለ በደም ፍላት ዘሎ ግብግብ ገጠመው።

"ድንጋይ ነው!" ሐውልቱ ላይ ሲሸናበት የነበረውን ዕቃውን አራግፎ ወደ ሱሪው ሰገሰገው። "ድንጋይ ነው!"

"ድንጋይ አይደለም!" እድሜው በግምት ወደ ሃያ አምስት አመት የሚጠጋው ወጣት ተንተገተገ። ወጣቱን ያውቀዋል። በዛ ወቅት አለ የሚባል ገጣሚ መሆኑን ያውቃል። ይህን ወጣት እዛው አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ስብሰባ ሲገባ በጊዜ አይቶት ነበር። ወጣቱ ከስብሰባው ሲወጣ ጠብቆ ሐውልቱ ላይ ሽንቱን መሽናቱ....... ከወጣቱ ጋር ግብግብ መግጠሙ ሁሉ ወጥመዱን በትክክል ማጥመዱንና ወጥመዱም በጊዜ መያዙን እያረጋገጠለት ነበር። አንገት ላንገት ተናነቁ። በቡጢ ሲቃመሱ ያ ወጣት በትክክል ፀጋዬ ገብረ መድህን መሆኑን እያጤነ ነበር። ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ገላገሏቸው፡

ወጣቱ ገጣሚ እየተበሳጨ ቤቱ ሲገባ በቅርብ ርቀት ሰውዬው እየተከተለው ነበር። ፀጋዬ ሌሊቱን አልተኛም፤ ሲፅፍ አደረ። ‹‹ጴጥሮስ ያችን ሰዓት›› የተሰኘውን ቴአትር በዛች ሌሊት ፅፎ እንዳገባደደ በደረቀው ሌሊት የሚፅፍበት ቤት በር ተንኳኳ። በሩ እደተከፈተ ሰውዬ ዘው ብሎ ወደ ውስጥ ገባ። ያኔ ፀጋዬ እየተንቀጠቀጠ ነበር። በሁዋላ ግን ሊያጠቃው እንዳልመጣ ተገነዘበ።

እንዲያውም በዛች ሌሊት የፃፈውን የቴአትር ረቂቅ አንስቶ ወረቀቶቹን እያተረማመሰ "እኮራብሃለሁ። ገና....ገና....ዓለም ሳታስበው ታከብርሃለች። ብዕርህን ወደ ሰገባው እዳትመልሰው። አየህ...ይህች አገር ህዝብ አላት ሰው ግን የላትም። እንጨት ብቻውን



ቆሞ ቤት አይሠራም። ማገር ያስፈልገዋል። ህዝብም ብቻውን ሀገር አይሆንም። አንድነቱን የሚጠብቁ ካስማዎች ያስፈልጉታል። የዚህች ሀገር አንድነት ካስማዎች እነ ቴዎድሮስ እነ ምኒልክ...... አሁን የሉም። አንተ እነሱን መሆን አትችልም። ራዕያቸውን ብትጋራ ግን እነሱን ትተካቸዋለህ። እነሱን ለመተካት ደግሞ ግዴታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆን አይጠበቅብህም።" ንግግሩን አቁሞ ቅንድቡን ዓይኑ አፋፍ ድረስ አንጠለጠለና የፀጋዬን ዓይነ ውሀ ጠልቆ መረመረው። ፀጋዬ ምንም መልስ አልሰጠውም። ባግራሞት እየተመለከተ ዝም አለው።

በምናምንቴ ነገሮች ከተወጠቀችው ከረጢቱ ውስጥ አንድ ሰፊ ብራና መዝገብና ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው። የነተበው ጥንታዊው የብራና ገፅ ላይ በቀይ ቀለም የተቀረፀ ካርታ ይታያል። ፅሑፉ በጥንታዊው የግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ ነው። የወለል ምንጣፍ በሚያክለው የብራና ገፅ ላይ በጥቁር ቀለም ፴፱ የሚል ቁጥር ከላይኛው ህዳግ ላይ ይታያል።

"ማልልኝ!" አለው የፀጋዬን። "በኢትዮጵያ አምላክ ማልልኝ!" አለው እንደገና መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀይ ቀለም የኢትዮጵያ ካርታ የሳለበትን ገፅ እያወጣ። ፀጋዬ እጁን እመፅሐፉ ላይ ሳያቅማማ አሳረፈ።

"ቴአትሩን ፅፈህ ጨርሰኸዋል?" አለው ስልቻው ውስጥ እጁን ልኮ ሌላ ነገር እየበረበረ።

"በግርድፉ......." ፀጋዬ መለሰለት።

"ጥሩ። ይህ ደግሞ ለቴአትሩ መዝጊያ የገጠምከው ግጥም ነው!" ፀጋዬ ለጴጥሮስ ያችን ሰዓት ቴአትር መዝጊያ የፃፈውንና «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» የሚል ርዕስ የሰጠውን ግጥም አንስቶ ሰውየው ድምፁን ዘለግ አርጎ አነበበው። ድምፁ እንደ ሐምሌ ነጎድጓድ አስገምጋሚ ነው። "ገጣሚ በሆነ!" አለ ፀጋዬ በልቡ አነባበቡ ደስ ብሎት።

ግጥሙን አንብቦ እንደጨረሰ "ግሩም ነው! .....ደብል ነው! ....ጨብጠኝ!" አለ ሰውየው። በደስታ ስክሮ ሲጨብጠው መዳፉ አንበሳ የሚሰባብር ያህል ጠንክረበት። ጨብጦ ሲነቀንቀው እጁን ለመንቀል የሚታገል መሰለው። አጥብቆ ቢመታው ኖሮ በአንድ ስንዘራ ህቅ እንደ ሚያደርገው አመነ ፀጋዬ። ከዛም ሁሉም ነገር ገባው።

"ነገር ፈልጎኝ ነው ለካ።"

"መልካም! አሁን ነገሩ ተለወጠ ማለት ነው።አንድ ሥራ ላዝህ ነበር። ከባድ ሥራ። አሁን ግን በቀላሉ ሥራውን እንዲህ

እናድርገው......" እስ በሌላ አጭር ብራና ላይ የሰፈረ የቃላት ዝርዝር እያወጣ፡፡ "እነዚህን ቃላት እዚህ ግጥም ውስጥ በታትነህ ትደባልቃቸዋለህ፡፡ አዘበራርቀህ ዝራቸው፡፡ ለግጥምህ ጉልበት ከመሆናቸውም በላይ እኔም ከእንግዴህ ይህን ከረጢት ይዤ አልንከራተትም፡፡....በል!...ዝራቸው!"

ፀጋዬ የተሰጡትን ቃላት በፃፈው ግጥም ውስጥ በታትኖ ዘራቸው፡፡ ቃላቱ 48 ናቸው፡፡ ሰውየው ባድናቆት እንደገና ጨበጠውና 48ቱ ቃላት የተዘሩበትን ግጥም እየተመለከተ በሌላ ወረቀት ላይ አንድ ጉጥ ያለው መስቀል መሳል ጀመረ፡፡ በመስቀሉ ላይም እያሌ ቁጥሮችንና አንዳንድ ከባባድ ቃላትን ከቀረፀበት በኋላ ሰቆቃወ ጴጥሮስ የሚለውን ምስጢራዊ ግጥም በብራና ወረቀት ላይ ከከረጢቱ ባወጣው መቃ-ብዕርና ቀለም ቀዳው፡፡ በብራናው ላይ ገልብጦ ከጨረሰ በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደገና አነበበው፡፡ በሚያስገመግም ድምፅ፡፡ ..............

ሰቆቃወ ጴጥሮስ

እየ+ ምነው እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ምነው ቀኝሽን ረሳሽት?
እስከመቼ ድረስ እንዲህ+ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን+ ሰቀቀንዋን+ጣሯን ይበቃል ሳትያት?
እላንቺ እኮ ማንም የላት....
እውሮጳ እንደሁ ትናጋዋን+ በፋሽስታዊ ነቀርሳ
ታርሳ+ተምሳ+ በስብሳ
ሂትለራዊ እባጭ ጫንቃዋን+ እንደ ኮረብታ ተጭኗት
ቀና ብላ እውነት እንዳታይ+ እንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት
ነፍሷን ድጦ ያስበረከካት
ሥልጡን ብኩን መፃጉዕ ናት፤....
እና+ ፈርቼ እንዳልባክን+ ሲርቀኝ የኃይልሽ ውጋጋን
እንቺ ካጠገቤ አትራቂ+ በርታ በይኝ እመ ብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት+ እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን፡፡
እምን+ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሽግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ÷
እማማ ኢትዮጵያን መንፈሴ+ተፈትቶ እንዳይከዳት ሠጋሁ..
እዋጅ+ የምሥራች ብዬ+የትብት ምግቤን ገድፌ
ከናቴ ማህፀን እልፌ
በኢትዮጵያ ማህፀን እርፌ+
ከእፈርዋ እጥንቴን ቀፍፌ
ደሜን ከደሟ እጠንፍፌ
ከወዟ ወዜን ቀፍፌ
በሕፃን እግሬ ድኼባት+በሕልም እክናፌ ክንፌ
እረኝነቴን በሰብሏ+ በምድሯ ላብ አሳልፌ



ከጫጩትና ከጥጃ+ከግልገል ጋር ተቃቅፌ፤
በጋው የእረኛ አደባባይ+ ክረምት እንደወንዙ ፍሳሽ
በገጠር የደመና ዳስ+ በገደል ሸለቆ አዳራሽ
ከቆቅና ከሚዳቋ+ ከዥግራ ጠረን ስተሻሽ
በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ+ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ
ከፍልፈል ጋር ሩጫ ስገጥም+ ከቀበሮ ድብብቆሽ
ከናዳ ጫፍ ሳር አጨዳ+ለግት ላሜ ትንሽ ግጦሽ
ለጥጃዬ የሌት ግርዶሽ
ለጥማድ በሬዎች ራት+ ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ
ለግልገሌ ካውሬ ከለል
እማሳው ሥር ጎጆ መትከል
ለፀሐይ የሾላ ጠለል+ ለዝናብ የገሳ ጠለል
ውሎ የንብ ቀፎ ማሰስ+ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ
ግጦሽ ሣር ሲለመልም+ ሲለማሩ ሰደድ ሜዳ
አዝመራው ጣል ከንበር ሲል+ ከብቱ ለሆራ ሲነዳ
ፈረስ ግልቢያ ስሽመጥጥ+ ከወፎች ዜማ ስቀዳ
ልቤ በንፋስ ተንሳፎ+ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ...
ያቺን ነው ኢትዮጵያ የምላት
እመ ብርሃን እረሳሽት?
ያችን የልጅነት ምሥራች? የሕፃንነት ብሥራት
የሣቅ የፍንደቃ ዘመን+ የምኞት የተስፋ ብፅእት
ያቺን የልጅነት እናት?
እሣኚቱ እንዴት ብለሽ+ ጥርሶችሽን ትነክሽባት?
ስሜን በስምሽ ሰይሜ+ባገልግሎትሽ ሰዋትት
ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት+ ከድጓ ቤት እመፅሕፍት
ካንቺ ተቆራኝታ ዕድሌ+ ካንቺ ተቆራኝታ ነፍሴ
ከቀፈፉ ደጇ ሰላም+ ከቤተ ልሔም ቅዳሴ
እኮ+ ቀፎ+ ዳባ ለብሶ
ቅኔ ዘርፎ ግሥ ገሦ
መቅደስ እጥኖ+ማኅሌት ቆሞ
በልብሰ ተክህኖ እጊጦ+በብር እክሊል ተሸልሞ
እመ ብርሃን ያንቺ ጽላት+ ነፍሴ ላይ በሳት ታትሞ
የመናኒው ያባ ተድላ+ ረድ ሆኜ እብሮኝ ታድሞ
ሕይወቴ እምነትሽን ጸንሶ
ሥጋ ፈቃዴ ተድሶ
ለሕንፃሽ መዲና ቆሞ+ ለክብርሽ ድባብ ምሰሶ!
ስሜን በስምሽ ሰይሜ+ ሆነሽኝ የእምነቴ ፋኖስ
ለዋዜማሽ ግሸን ማርያም÷ ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ
ስሮጥ+ በወንበሩ እኖርሺኝ+ በአንበሳው በቅዱስ ማርቆስ
ታዲያን ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወድቅ+ ከምትሰጪኝ ለፍርሃት ጦስ
ምነው በረኝነት ዕድሜ+ ዓይኔን በንጎጣት የሉስ
የጋኔል ጥንብ እንሳ ከንፎ+ ወርዶ በጨለማ በርኖስ፡፡
ባክሽ እመብርሃን ይብቃሽ+ ባክሽ ምስለ ፍቁር ወልዳ

ጽናት ስጪኝ እንድካፈል+ የእናቴን የኢትዮጵያን ፍዳ
ከነከሳት መርዝ እንድቀምስ+ ከነደደችበት እቶን
የሷን ሞት እኔ እንድሞታት+ ገላዋ ገላዬ እንዲሆን።...
አዎን+ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ።...
ሕፃን ሆኜ የእርግብ ጫጩት+ አንዳንዴ ራብ ሲያዳክማት
ችጋር ከጎጆዋ ገፍቶ+ እዛፍ ግርጌ ሲጥላት
እናቷ በርራ ደርሳላት
በእክናፏ ሙቀት ታቅፋት
እፍ እያለች ግንባሯ ላይ+ ሕይወት ስትተነፍስባት
ወዲያው ነፍስ ትዘራለች
ሽር-ብር-ትር እያለች።
ባክሽ አንቺም አትራቂብኝ
እመ ብርሃን እናቴ+ ትንፋሽሽን እፍ በይብኝ
ዕናትሽን እፍ በይብኝ+
ወይም ይቺን የሞት ጽዋ+ ጥላዋ ነፍሴን ካፈናት
እንዳልጠጣት አሳልፊያት
መራራ ክንፏን ገንጥለሽ+ቀጠሮ+ቃልዋን ግደፊያት!...
አለዚያም ዕናትሽን ስጪኝ+ ልጠጣው ኪዳኑ-ውሉን
የኔ ፍቃድ እምነትሽ ነው+ ያንቺ ፍቃድ ብቻ ይሁን።
እንደ ጳውሎስ እንድፀና+በፍርሀት እንዳልታሰር
በውስጤ ከሚታገለኝ+በሥጋ አውሬ እንዳልታወር
ለዕየለቱ ሞት እንዳልሰንፍ
የኪዳኔ ቃል እንዳይነጥፍ
ቃልሽ በሕሊናዬ ዲብ +ኃይልሽ በህዋሴ ይረፍ።
ፍርሀት ቢያረብብኝም +አንቺ ካለሽ አልሰጋም
ኩርትም ብዬ እችልበት +እሽሽግበት አይጠፋም
የግማደ መስቀሌን ጉጥ + እታገስበት አላጣም
አለዚያማ ብቻዬን ነኝ+ኢትዮጵያም አላንቺ የላት
አንቺ አዕኝኝ እንድጸናላት።
አስርጪብኝ የእምነት ቀንጃ+ለሥጋቴ አጣማጅ አቻ
ለጭንቀቴ-መቀነቻ።.......
አዎን+ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሽሽግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ.....
[illegible] ቀበና (ፀጋዬ ገብረ መድህን)

"ግሩም ነው! እሳት የላሰ ግጥም! እሳት የላስክ ልጅ!" የፀጋዬን ግንባር ግጥም አድርጎ ሳመው። "ማስጠንቀቂያ!" አለው ከዚያ። "ከዚህ ግጥም ላይ አንድም ቃል አንድም ነጥብ እዳይለወጥ! ይህ ምስጢር ነው። ከዚህ ግጥም ውስጥ አንድ ቃል ብታወጣ ከሀገርህ ጋር ያለህ ወዳጅነት ይጎድፋል። ለመሆኑ.......ታሳትመዋለህ?"



"እንደ አምላክ ፈቃድ........."

"እንግዲያውስ እንደነገርኩህ! አንድም ቃል እንዳይለወጥ! አንድ ቀን ይህ ግጥም........" ትኩር ብሎ አይቶት በብራና ላይ የፃፈውን የሰቆቃወ ጴጥሮስን ቅጂ ከረጢቱ ውስጥ ቋጥሮ ሲወጣ ነግቶ ወፎች እየዘመሩ ነበር።ፀጋዬ አፉን ከፍቶ ቀረ። እየሮጠ ተከትሎ "ስምህ ማነው? ዳግመኛ ላገኝህ እፈልጋለሁ...." ሲል ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ጠየቀው። ሰውየው እርምጃውን ገቶ ወደኋላ ዞረ። "የፈለከውን ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ። እኔና አንተ ከአሁን በኋላ የምንገናኘው የግጥም መጽሀፍህ ሲታተም ብቻ ነው። ደህና ሁን!" እርምጃውን ቀጠለ። ፀጋዬም በዓይኑ ሸኘው።

ይህ ከሆነ ከአምስት አመት በኋላ በ1966 ዓ.ም የፀጋዬ ገብረ መድህን እሳት ወይ አበባ የሚባለው የግጥም መጽሀፍ ታተመ። ‹‹እሳት ወይ አበባ›› ለህትመት ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በገባበት ዕለት ከሰአት በኋላ ማተሚያ ቤቱ ውስጥ አንድ መነኩሴ ታይተው ነበር። መነኩሴው ካሜራ ክፍል የገቡት ሰቆቃወ ጴጥሮስ የሚለው ግጥም በዛ ጥራዝ ውስጥ መካተቱንና ቃሉም አለመለወጡን አረጋግጠው ለመውጣት ቢሆንም ወደ ማተሚያ ቤቱ ሲገቡ ግን ለህትመት የተዘጋጀ «አክሳፎስ» የሚል ርዕስ ያለው መጽሀፍ ይዘው ስለዚሁ መጽሀፍ የህትመት ጉዳይ ለመነጋገር በሚል ሰበብ ነበር። «አክሳፎስ» የሚባል መጽሀፍ ግን እስካሁን ድረስ ታትሞ ለንባብ አልበቃም።

ይህ ከሆነ ከብዙ አመታት በኋላ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን በራሱ ድምፅ አንብቦ «እብረን ዝም እንበል» በሚል ሪዕስ ባሳተመው የግጥም ሲዲ ካሴት መግቢያ ላይ ሰቆቃወ ጴጥሮስን የፃፈበትን ምክንያት እንዲህ ብሎ ሲያብራራ ተደመጠ።

"ሰቆቃወ ጴጥሮስ የጴጥሮስ ያችን ሰዓት መዝጊያ የታሪካዊ ጀግናው የመጨረሻ ቃል ነው። ‹የመጨረሻውን ቃል ለጀግናው ተውለት።› ይላሉ፤ ጥንታውያን የታሪካዊ ቴአትር ፀሐፍት.... እነ ኢከራን ኤፍራት...እነ ዩሩፒድዩስ።....አቡነ ጴጥሮስ ሌሊቱን በግራዚያንና በባንዶቹ.. በባንዶች አሽከሮች አኮርባሽነት በገነተ ልዑል ጉድጓድ ቤት ውስጥ ሲገረፍ... ሲመረመር 'ኢትዮጵያን ከድተህ በሞሶሎኒ እመን' ተብሎ ሲተለተል አድሮ በማግስቱ ጠዋት በአደባባይ በጥይት ተደበደበ። በግራዚያኒ ትዕዛዝ የጥይት እሩምታ ተኩሰው የጠቀጠቁት ጣሊያን ያሰለጠናቸው የሰሜን ባንዳዎች ወንድሞቻችን ናቸው። ጴጥሮስ እንኳንስ ህዝቡ ምድሪቱ ጭምር ለፋሽስት እንዳትገዛ አውግዞ ሞተ። ..... በልጅነቴ ከአምቦ ከተማ ለመጀመሪያው ጊዜ በ15 ዓመቴ ክቡር ዘበኛ ካዴት ልገባ ጠፍቼ ስመጣ አዲስ አበባ እምብርት መዳረሻ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት

ከትሬንታኪትሮ ወርጄ......አባቱ ስለአቡነ ጴጥሮስ የእረኝነት እድሜና የጀግንነት ጀብድ ህይወት በከፍተኛ አድናቆት ያጫውቱኝ የነበረው ትዝ ብሎኝ ሐውልቱ ሥር ቆሜ ቀረሁ። .......ይህ በሆነ ከአሥር ዓመት በኋላ አለቃችን የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ክቡር ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ማስታወቂያ ሚኒስትር እዛው አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ስብሰባ ጠርተውን ቢሮአቸው አምሽተን ስንወጣ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ አንድ ሞቅ ....እ.... ያለው የተበሳጨ ጀብራሬ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን እየሸና 'አንተ ድንጋይ! ጓደኞችህ ተመችቷቸው በማርቼዲስ ሲንሸራሸሩ ይኸው አንተ ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ....ድንጋይ! እሸናብሃለሁ!.... ሲል በልጅነት ደም ፍላት ዘልዬ ከጀብራሬው ጋር ግብግብ ገጠምኩ። ‹ድንጋይ ነው››......"ድንጋይ አይደለም!"....በሚል

በቡጢም ተቃመስን። ከስብሰባው የተበተነኑ ሰዎች ገላገሉንና እየተበሳጨሁ ቤቴ ገባሁ። ሌሊቱን አልተኛሁም። ‹ጴጥሮስ ህያው ነው› ለማለት፣ ‹ጴጥሮስ ድንጋይ አይደለም› ለማለት ይመስለኛል፤ ጴጥሮስ ያችን ለአትን ስጭር አደርኩ። እንዳልኩት ይህ ስነግጥም የታሪካዊ ጀግናው የመጨረሻ ቃል ነው...." ይህ የራሱ የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የምስክርነት ቃል ነው። ይህን ንግግርም ብዙ ኢትዮጵያውያን አዳምጠዋል። ሎሬቱን ...መጽሀፉን ያነበቡም ያላነበቡም ያደንቁታል። ነገር ግን ስለ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እንዲ በዚህ ንግግሩ ውስጥ ‹‹ጀብራሬ›› ተብሎ ስለተጠቀሰው ኃያል ሰው የሚያውቅ ማንም የለም። በሎሬቱ ንግግር ውስጥ ግን አንድ ነገር መገንዘብ ይቻላል። "ሞቅ..........ያለው የተበሳጨ ጀብራሬ" የሚል የሚያሻማና ብዙ ጥያቄ የሚቆሰቁስ ገለፃ አለ። ሞቅ ያለው! ደግሞ የተበሳጨ! ደሞ ጀብራሬ! ደሞ በቡጢ የሚያቀምስ! ደሞ ግብግብ ተጋጥሞ የማይወድቅ! ደሞ በንግግሩ ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው ስለ አቡነ ጴጥሮስ ብዙ የሚያውቅ የሚመስል! ደሞ በራስ በመተማመን የተሞላና "ድንጋይ!" ብሎ የሚሳደብ! ደሞ ስንት ቦታ ባዶውን ተቀምጦ ሀውልት ላይ የሚሸና!

ሆኖም ቶብ ጣዩ መነኩሴ ዲዲሞስ ጀብራሬው ባይኖር ኖሮ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን ባልሸና! አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን ባይሸና ጴጥሮስ ያችን ለአትን የመሰለ ቴአትር ባልተፃፈ....ሰቆቃወ ጴጥሮስም ባልተገበመ። አንድም ቃል ሳይጨመርበት አንድም ቃል ሳይቀነስበት የታተመውና በጣፋጭነቱ ላለፉት ብዙ አመታት ሲከመከም የኖረው ሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም ባለ 105 ስንኝ ነው። ቃላቱም 497 ናቸው። ሎሬቱን ጨምሮ...48ቱ ቃላት ያጨቁትን ምስጢር ለመፍታት የቻለ ግን እስካሁን አልተገኘም።



# ፩

## ካሊፎርኒያ፣ አሜሪካ
## ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅግ ራሱን ስቶ ከተኛበት የማይንዘገዝ ክፍል ውስጥ ከሰመመኑ ከነቃ ከሰዓታት በኋላ አንድ ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቅ ጠይም ዶክተር ቆሞ በጭንቀት እየተመለከተው ነበር።

"እንኳን በሰላም ነቃህ፣ ኢንጂነር ሻጊዝ" አለ ዶክተሩ ፈገግ ብሎ።

"ከነቃሁ እኮ ቆይቻለሁ......ሆኖም ስለፈገግታህ አመሰግናለሁ" አለው ኢንጂነር ሻጊዝ ዓይኖቹን ገርበብ እንዳደረገ።

"እኔም አመሰግናለሁ ኢንጂነር ሻጊዝ። በእርግጥ ግራ ተጋብቼ ስለነበር ያከምኩትን ገመምተኛ ከሰመመኑ ሲነቃ መቀበል በሚገባኝ ብሩህ ፊት ስላልተቀበልኩ ይቅርታህን እለምናለሁ። ‹በሽተኞችን የሚፈውሳቸው ከዶክተሩ የህክምና ርዳታ ይልቅ ብሩህ ፊቱና ፈገግታው ነው› ብዬ አምናለሁ። የደመቀ ፈገግታና የፈካ ፊት የማይፈውሰው በሽታ የለም" አለ ጠይሙ ዶክተር። ፊቱ በብዙ ጥያቄዎች መሀል እንዳለ ያሳብቃል። ግራ መጋባት ይታይበታል።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በምስጢር ወደ አሜሪካ ከተላከ ረዥም ጊዜ የሆነው የኢትዮጵያ ደህንነት አባል በመጨረሻ ሁሉ ነገር እንደ ጨለመበት ተረዳ። ቤቱ ተከቧል። እጅህን ስጥ ሲባል «እንኳንስ እኔን አንዲት ዘለላ ፀጉሬን አታገኟትም» ሲል በስልክ ተሳልቋል። ድምፃቸው ይሰማዋል። ዳናቸው ወደበሩ እየቀረበ ሲመጣ ሽጉጡን በራሱ ጭንቅላት ላይ ደቀነው። «እቀድማችኋለሁ......በሱ ጭንቅላት ላይ ምላጭ አልስብም...»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"የወንዜን ሰው ትመስላለህ" አለው ኢንጂነር ሻጊዝ። "ከሐበሻ ምድር የመጣህ ሳትሆን አትቀርም።"

"አልተሳሳትክም" አለ ጠይሙ ዶክተር ብዙ ወረቀቶችን እየተረማመሰ። "ዶ/ር ሚራሻር እባላለሁ። ወደ አሜሪካ ከመጣሁ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል። እዚህ ሆስፒታል ውስጥ ከተቀጠርኩ ግን ጥቂት ጊዜዬ ነው። .....በዚህ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ስላንተ የህክምና ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ለማወቅ ችያለሁ" የኢንጂነሩን የህክምና ሁኔታ የሚገልፁ መረጃዎች የያዙት ብዙ ወረቀቶች እያገላበጠ ሰማያዊው ወንበር ላይ ተቀመጠ። በጠይም ፊቱ ላይ ያንገበበውን የጥያቄ ደመና የሚያዘንበበት ጊዜ መድረሱን አምኗል።

"ኢንጂነር ሻጊዝ..፡ ከአሁን በፊት ብዙ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ማድረግህን ያወኩት በቅርቡ ባገኘሁት ምስጢራዊ ሰነድ ላይ

ነው" አለ ሚራዥ ግንባሩን በመዳፉ አሻሸ፡፡ "ከ1969 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በደረሰብህ የልብ ህመም ምክንያት ብዙ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ተደርጎልሃል፡፡ ከዛም ወዲህ በየሁለት ወሩ ቀዶ ጥገና ይደረግልሃል፡፡ በየሁለት ሳምንቱም በሃኪም የመታየት ግዴታ አለብህ፡፡ ያስቅቃል!" ዶ/ር ሚራዥ በማያውቀው ስሜት ራሱን ነቀነቀ፡፡

"ለመሆኑ አንተ ማነህ?" ሲል ዶክተሩን በጥሞና እየተመለከተ ጠየቀው ሻጊዝ፡፡ "እንዴት እንድታክመኝ ፈቀዱልህ?"

"እዎ.....አክሜህ አላውቅም፡፡ የህክምናህን ጉዳይ ግን ብዙ ጊዜ እከታተል ነበር፡፡ ይህን ጊዜም ስናፍቅ ነበር፡፡ ያገኘኋቸውን መረጃዎች ላካፍልህ ስጠብቅ ነበር፡፡ ይኸኛውን ቀዶ ጥገና ብቻዬን አይደለም ያደረኩልህ፡፡ ከሌሎች ዶክተሮች ጋር በመሆን ነው፡፡ ቀዶ ጥገናውን በበላይነት እንዲመራ የተወከለው ሐኪም ዶ/ር ሉስ ካን ባልታወቀ ጉዳይ ወደ ሌላ ሆስፒታል በመዛወሩና ተረኛም ስለነበርኩ ተክቼው እንድሠራ ተደርጓል፡፡ በእርግጥ እስካሁን እኔን አታውቀኝም፡፡ አሁን ተዋውቀናል፡፡ የሀገርህ ሰው በመሆኔ ብቻም ሳይሆን የሙያ ግዴታዬና ህሊናዬ የሚጠይቀኝ በመሆኑ ነው የጤንነትህን ጉዳይ በጥብቅ መከታተል የጀመርኩት" በረጅሙ ተንፍሶ ንግግሩን ቀጠለ፡፡..........."አንተ እኔን ባታውቀኝ አይገርምም፡፡ የሚገርመው እኔ አንተን ባላውቅህ ነው፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ስላንተ ማሠቅ ,ጀመሩት በቅርቡ ነው፡፡.... በቅርቡ፡፡ ስላንተ በጣም የሚታወቀው በሰለጠነው ዓለም አካባቢ ነው፡፡ ስላንተ ብዙም ባይሆን በጥቂቱ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ከመገናኛ ብዙሃንና ከሰዎች አንደበት ብዙ ሰምቻለሁ፡፡ በህዋ ምርምር ዓለማችን ካፈራቻቸው እውቅ ሳይንቲስቶች መሃል ግዙፍ ስም ያለህ ሳይንቲስት መሆንህን አውቃለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ እንደምኮራብህ ልነግርህ እወዳለሁ፡፡ ልኮራብህም ይገባል፡፡ ኢትዮጵያም ልትኮራብህ ይገባል፡፡ በህዋ ምርምር አንቱ የተባለ አንድ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ማግኘት ቀላል አይደለም፡፡ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነህ፡፡ ኢትዮጵያ እንዳንተ ያለ ሰው ለማፍራትና ለማሰልጠን ብዙ ቢሊዮን ዶላር ማፍሰስ ባስፈለጋት ነበር፡፡ ብቻህን ታግለህ እዚህ ደረጃ መድረስህ ለብዙ የሀገርህ ልጆች አርአያነቱ ላቅ ያለ ነው፡፡ ከዲፕሎማ ተነስተህ የአለማችን ታላቅ የህዋ ሳይንቲስት መሆንህ ለሀገርህ ሰዎች ታላቅ መነሳሳትን ይፈጥራል፡፡ ኢትዮጵያውያን አትንኩኝ ባዮች ብቻ ሳይሆኑ እድሉን ካገኙ መሰልጠንና መበልፀግ የሚችል አዕምሮ ያላቸው እንደሆኑ ለዓለም ታላቅ ምስክር ሆነሀል፡፡"

"ለመሆኑ ሰነዱ በእጅህ ይገኛል?" ኢንጂነር ሻጊዝ በመደመም ጠየቀው፡፡ እሱ አቅቶት የተወውን ነገር ይህ ሰው እንዴት ሊደርስበት እንደቻለ ተደንቆ፡፡

"ሙሉ አይደለም" አለ ዶ/ር ሚራዥ ትንሽ ትክዝ ብሎ፡፡



"በእጅህ ስላለው........." ኢንጂነር ሻጊዝ ሰውነቱ ላይ በተተካከሉት የህክምና መሣሪያዎች እንደተተበተበ ሳይነቃነቅ ጥቃቅን አይኖቹን ብቻ እያንቀዋለለ የዶክተሩን መልስ መጠባበቅ ጀመረ፡፡

ዶክተር ሚራዥ የተረጋጋ መንፈስ አይታይበትም፡፡ ብዙ ጊዜም በር በሩን ይመለከታል፡፡ "ብቻ ግን አንድ ነገር አለ" ሚራዥ ቅጭም ብሎ በእጁ የያዛቸውን ወረቀቶች አርገፈገፋቸው፡፡

"እዎ አውቃለሁ፤ አሁን ማወቅ የምፈልገው የደረስክበት ምስጢር ካለ ያንን ነው" ሻጊዝ በጥያቄ መልክ የግንባሩን ቆዳ ሸበሸበው፡፡

"ነገሩ በቀላሉ የሚገባና ግልፅ የሆነ ነገር አይደለም፡፡ ሰነዱ ላይ ያለው ሪፖርት በትክክል የልብህን በሽታ ምንነት አይገልፅም፡፡ ብቻ የመጀመሪያው የልብ ቀዶ ጥገናህ ላይ የሆነ ጉዳይ ሳይኖር አይቀርም፡፡ ያሁኑ የልብ ቀዶ ጥገናህ ሲደረግ ያየሁትና..... የተደረገው ሌላ ሪፖርቱ የሚለው ሌላ፡፡ አሁንም ቢሆን የተፃፈው ሪፖርት ከበሽታህ ጋር የማይገናኝ ነው፡፡ የ.ማ.ይ.ገና.ኝ!» ተቁነጠነጠ፡፡

«የሆስፒታሉን ዳይሬክተር ለማናገር ገብቼ ነበር፡፡ ያገኘሁት ምላሽ ምን እንደሚል ታውቃለህ? ‹አያገባህም አርፈህ ሥራህን ሥራ› ነበር ያሉኝ፡፡ እንዲያውም ይህን ክትትሌን ካላቆምኩ በሰዓታት ውስጥ ከሆስፒታሉ እንደሚያሰናብቱኝ በጥብቅ አስጠነቀቀውኛል፡፡ እኔ ደግሞ እንደዚህ አይነት ነገሮችን መጋፈጥ ደስ ይለኛል፡፡ ይህን ጉዳይ አንተ ቻል ብትለው እንኳ መጋፈጤን አላቆምም፡፡ አሜሪካ እንደምትፈልግህና እንደምታስፈልጋትም አውቃለሁ፡፡ ግን በዚህ መልኩ መሆን የለበትም፡፡ ነፃነትህንና ሰብአዊ መብትህን ከዚህም በላይ በህይወት የመኖር መብትህን መጋፋት ታላቅ ወንጀል ነው፡፡ የተደረገልህ ቀዶ ጥገና የተለየና በየትኛውም ከአሜሪካ ውጭ ያለ ሀገር ሊሰጥ የማይችል ነው..." ዶ/ር ሚራዥ ለማስረዳት ግራ ተጋብቷል፡፡

"እሱንማ...... አውቃለሁ፡፡......ከአሜሪካ ውጭ መታከም ስለማልችል አይደል እንዴ የዚህች ሀገር እስረኛ ሆኜ የቀረሁት?! እሱንማ አውቃለሁ» አለ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ፡፡ "ይልቅ የተለየ የደረስክበት ምስጢር ካለ ንገረኝ፡፡ እርዳታህን እሻለሁ፡፡ የፈለከውን ያህል ለመክፈልም ዝግጁ ነኝ" አለ ሻጊዝ በተማፅኖ፡፡

«እኔንም ይህ ጉዳይ ይመለከተኛል፡፡ አንተኮ ለሀገርህ ብቸኛ ሰው ነህ፡፡ አንተን ብረዳ ረድቻት የማላውቃትን ሀገሬን መርዳት ቻልኩ ማለት ነበር፡፡ ግን እንዴት አድርጌ? በጣም በጥብቅ የተያዘ ምስጢር ይመስለኛል፡፡ ብቻ እግዚአብሔር ከረዳኝ ባደርግልህ ደስታውን አልችለውም ነበር፡፡" ዶ/ር ሚራዥ አፍንጫው ላይ የተሰካውን ነጭ መነፅሩን አንስቶ ከነጭ ጋዋኑ

ኪስ ባወጣው መሐረቡ የአይኑን ሥር እየጠራረገ ተነስቶ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ቁልፎች መነካካት ጀመረ፡፡

ኢንጂነር ሻጊዝ ግንባሩን ወደላይ እንደሸበሸበ ዶ/ር ሚራዥን በጥያቄ ይከታተለዋል፡፡ ከዕውቅናውና ከስኬቱ ጀርባ ውጣ ውረድ የበዛበት የህይወቱ ጉዞ ከአዕምሮው ተሰነቀረ፡፡

ጠፈርን ገዝተዋል ከሚባሉት እውቅ የህዋ ሳይንቲስቶች አንዱ የሆነው ኢንጂነር ሻጊዝ ለአሜሪካ የህዋ ምርምር ተቋም ናሳ ያበረከተው ግኝት ገና በ43 አመቱ በአሜሪካ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅናን አስገኝቶለታል፡፡

በናሳ ውስጥ የመንኮራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር ሆኖ ጨረቃ ላይ በመውጣት ሁለተኛ ሰው ከሆነው የአፖሎ ጠፈርተኛ ቡዝ አልድሪን ጋር በመሆን ሁለት የህዋ መንኮራኩሮችን ዲዛይን አድርጓል፡፡ የጁፒተር፣ የሳተርን በተለይም በቀጣይ ለአሜሪካና ለዓለማችን ሀያላን ሀገራት ማረፊያነት ተስፋ የተጣለባት ፕላኔት ማርስን ውስጣዊና ውጫዊ አካል የሚያጠናውን ልዩ የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ በመሆን ለጠፈር ምርምር ያደረገው አስተዋፅኦ ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት የመሬትን ውስጣዊና ውጫዊ ሀብት ከመመርመሩም ባሻገር ስለ ሳተላይቶችና ራዳሮችም የጠለቀ እውቀት ካላቸው ሳይንቲስቶች ግንባር ቀደሙ ሳይንቲስት ነው፡፡

ይህ ሰው ወደ አሜሪካ ካገባ ጊዜ ጀምሮ በሥራው አስደናቂ ሥራ ምክንያት ከአንድ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እጅ በጣም ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙትን ሽልማት ተቀዳጅቷል፡፡ በተራቀቁ ላቦራቶሪዎችና በአሜሪካ ምስጢራዊ የቴክኖሎጂ ተቋማት ውስጥ በያዛቸው ጥብቅ የቴክኖሎጂ ምስጢሮች ምክንያት አንድም ቀን አንዲትም ደቂቃ ከጥበቃና ከክትትል ውጪ ሆኖ አያውቅም፡፡ እንዲያውም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣበት ጊዜ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያ የገባው የሲ.አይ.ኤ ቡድን ለደህንነቱ ሥጋት የሆኑ ነገሮችን ካጠናና ካስወገደ በኋላ ነበር አሜሪካ የፈቀደችለት፡፡ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ይደረግለት የነበረው ጥበቃም አንድ አሜሪካዊ ባለስልጣን ከሚደረግለት ጥበቃ በላይ ነበር ይባላል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይቀርም ለተፈቀደለት ጊዜ ብቻ የሚያቆይ ምስጢራዊ ህክምና እንደተሰጠው እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ፈጥኖ የተመለሰበትም ምክንያት ይህ ነበር፡፡ በግልፅ ከተቀጠሩለት እስከ አፍንጫቸው ከታጠቁ አጃቢዎቹ በተጨማሪ በዙሪያው የሚያንዣብቡ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች በዓይነ ቁራኛ ይጠባበቁታል፡፡ ወደሚንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ እየተንቀሳቀሱ በጥብቅ ይጠብቁታል፡፡ ጠፈርን የገዛ የአሜሪካ



የጠፈር ምርምር ሳይንቲስት መሆኑ ብቻም ሳይሆን የቋጠረው የአሜሪካ የቴክኖሎጂ ምስጢር የበለጠ ጥበቃውን አክሮታል፡፡

ቻይና፣ ጃፓን፣ ኢራን፣ ህንድ፣ ፓኪስታን፣ ሰሜንኮርያ፣ እስራኤልና ሩሲያ ይህንን ሳይንቲስት በእጃቸው ለማስገባት ጥያቄያቸውን በምስጢር ሲያቀርቡለት ረብጣ ገንዘብም በመቁጠር ነበር፡፡ እስራኤልም ከነዚህ ሀገራት ጋር ያረገውን ግንኙነት ስታነፈንፍ ከኖረች በኋላ ጥያቄዋን አለመቀበሉን ስትረዳ ከእሷ በቀር ወደ የትኛውም ሌላ ሀገር እንዳይሄድ በተለይም በአረብ ሀገራት እጅ እንዳይገባ በስለላ ድርጅቷ ሞሳድ በኩል ጥብቅ ክትትል ለማድረግ ከሲ.አይ.ኤ ጋር ተቀላቅላለች፡፡ ከአሜሪካ መንጋጋ ፈልቅቀው ለመውሰድ የሚኳትኑትን ሀገራት አሻፈረኝ ቢላቸውም ክትትላቸውን ግን አላቋረጡም፡፡ በነዚህ ሀገራት ክትትል ምክንያትም ሞሳድና ሲ.አይ.ኤ የበለጠ ጥበቃቸውን እንዲያጠናክሩ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንን ሳይንቲስት ሁሉም የዓለም ሀገራት ይፈልጉታል...ከኢትዮጵያ በቀር፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ቤቱ ከተከበበ ሶስተኛ ቀኑ ነው። ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ እንደ ደቀነው በሩ በኃይል ተንኳኳ። «ገዳዮቼ እያንኳኩ ነው» ሲል ለራሱ ተናገረ። የኢንጂነሩ የቅርብ ሰው ለመሆን በመቻሉ ጉዳዩን እሱ ይዞት ቢቆይም ከባለፈው ስብሰባ ወዲህ ግን ሌላ ሁለት ደህንነቶች እንዲከታተሉት ተቀይረው መጥተዋል። የኢንጂነሩን መወገድ በሚቃወሙና በሚደግፉ ጎራዎች በተከፈለው በዛ ስብሰባ ላይ ያንፀባረቀው ሀሳብ ጉባኤውን ለሁለት ከገመሰው ወዲህ እሱ ራሱም ታዳኝ ሆኗል። ዋሽንግተን ነው ሲሉት ዴንቨር እየታየ እስካሁን ያጋበሳቸውን መረጃዎችና ሰነዶች ጠራርጎ ይዞ ሲሸሽ ከርሞ ከሶስት ቀናት በፊት ነው ካሊፎርኒያ ውስጥ አሁን ባለበት ሁኔታ የተያዘው። ሲገቡ በርና መስኮቱን መሰባበር ሲጀምሩ ሽጉጡን ወደ ሽንጡ መልሶ በፍጥነት ሰነዶቹን ጠራርጎ በእሳት አያያዛቸው። ቤቱ በወረቀቶቹ ቃጠሎ ጢስ እንደታፈነ በድምፅና በምስል የተቀዱ መረጃዎችን እየሰባበረ ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው። ባንዲት ብጣቂ ወረቀት ላይ አንድ ቃል ካሰፈረ በሁዋላ መልሶ ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ ደቀነው።.......

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሻጊዝ ገና በልጅነቱ ነበር የተለያዩ ማሽኖችን የመፍታትና የመገጣጠም ፍቅር ያደረበት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ቦንጋ ከቀሩት ጣሊያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ ጀምሮ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በወቅቱ በሩስያውያን በሚተዳደረው የባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ዘርፍ የእርሻ ቴክኖሎጂን አጠና፡፡ ከባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋም በማዕረግ የተመረቀም ሲሆን ውጤቱም በተቋሙ ታሪክ ሁለተኛው ከፍተኛ ውጤት ነው፡፡

በኋላ ደግሞ በኢትዮጵያ የአውቶሞቲቭ ሰርቪስና ሴልስ ኩባንያ የቴክኒካል ዋና አማካሪ ማናጀር በመሆን ለሁለት አመታት ሠርቷል፡፡ በ1964 ዓ.ም በጃፓን ኦቨርሲስ ማህበር ባገኘው ነፃ የትምህርት ዕድል ወደ ጃፓን አመራ፡፡ በጃፓን ሄሮሺማ ዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪና አቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግን አጠና፡፡ በአሳካ ዩኒቨርስቲም የጃፓኖችን የቴክኖሎጂ ምስጢር ለመረዳት ሲል ጃፓንኛ ቋንቋ ለመማር አላቅማማም፡፡ ከጃፓን ወደ አሜሪካ ሲያመራ በጠፈር ምርምር የመሳተፍ ህልሙን እውን ለማድረግ በመቋመጥ ነበር፡፡

አሜሪካም ከጃፓን የመጣውን ባለ ብሩህ አዕምሮ የቴክኖሎጂ ሰው እጁን ስማ ተቀበለችው፡፡ ወደ አሜሪካ ከገባ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የኤሮስፔስ ኩባንያዎች ሲሰራ ቆይቶ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ (NASA) ተቀጠረ፡፡

በናሳ ቆይታው የመንኩራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር በመሆን መንኩራኩሮችን ዲዛይን ማድረግ፣ መሥራትና መገጣጠም፡ መሞከርና ማምጠቅ...ተግባሩ ሆነ፡፡ በዚህ ወቅት ዝናው እየናኘ አውሮፓ ደረሰ፡፡ ለአውሮፓ ስፔስ ኤጀንሲም በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በስፔስ ሲስተም ክፍል የበረራ ዳይናሚክ ሲሙሌተር እና 'ኔክስት ጀነሬሽን' ተብሎ የሚጠራው 'ግሎባል ፖዚሽን ሳተላይት ሲስተም' የፈጠራ ባለቤት ሳይንቲስት ከመሆኑም ባሻገር 'ስታር ዋርስ' ተብሎ የሚጠራውን የመከላከያ ሲስተም ቴክኖሎጂ ለማጎልበት የሳይንቲስቶችና የኢንጂነሮች ቡድን መሪ በመሆን ሠርቷል፡፡

ከእስራኤል አሜሪካዊት ባለቤቱ ሶስት ልጆች ቢወልድም ትዳሩ የሠመረ አልነበረም፡፡ የልጆቹን የአሳዳጊነት መብት ለማግኘት በፍርድ ቤት ለመከራከር ሕግ ማጥናቱ ብዙዎችን አስገርሟል፡፡ ብዙዎች ‹ለያንዳንዱ ችግሩ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የሚማር ብቸኛው ሰው ሻጊዝ እጅጉ ነው› ይላሉ፡፡ በጠፈር ሲስተምና በኤሮኖቲካል ምህንድስና በከፍተኛ ውጤት በዶክትሬት ዲግሪ ከመመረቁም በተጨማሪ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽንም የማስተርስ ዲግሪ አለው፡፡

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ከተቀጠረ በኋላ በአሜሪካ የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ውስጥ ስሙ የገነነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ግን ብዙም ሳይቆይ የልብ በሽተኛ ሆነ፡፡ ከዚያም በየሁለት ወሩ የልብ ቀዶ ጥገና ማድረጉን ቀጠለ፡፡ ከዚህ ቀዶ ጥገና በስተጀርባ ያለውን ምስጢር እሱም ቢሆን በውል አያውቀውም፡፡



በልቡ ህመም ምክንያት ከተወሰነ የአየር ክልል በላይ መውጣትና መብረር ባለመቻሉ የተነሳ እንጂ ጨረቃ ላይ በማረፍ የመደመሪያው ጥቁር መሆን ይችል እንደነበር ሁልጊዜም ይናገራል፡፡

ፊቱን ወደ አፍሪካ ማዞሩና በተለይም የሀገሩን ማዕድንና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት የተማሩ ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ በሳይንሳዊ ጥበብና በተራቀቀ ቴክኖሎጂ አማካኝነት አውጥቶ ሀገሩን ከድህነት አዘቅት ቶሎ መንጥቆ ለማውጣት በተነሳባት በዚህ ወቅት ክትትሉ ከቀን ወደቀን እየጠነከረበት መጥቷል፡፡ ብዙዎች እንደሚሉት ወደዚች ደሀ ሀገሩ ቢሄድ በሌሎች ሀገራት እጅ ላለመውደቁ አሜሪካ ማረጋገጫ የላትም፡፡ እስራኤልም ቢሆን ይህ ሳይንቲስት በአረብ ሀገራትና ፀረ እስራኤልና አሜሪካ አቋም ባላቸው ሀገራት እጅ እንዳይገባ ክትትሏን አጠናክራለች፡፡ ይህ ሰው የዓለማችንን ራዳሮች ሳተላይቶችና የመገናኛ አውታሮች በፈለገው ጊዜ መዝጋት የሚችል አእምሮያለው ሰው ነው፡፡

በፕላኔታችን ሰማይ ላይ የተበተኑት ጥቁር ሳጥን ወይም በምህፃረ ቃል ‹‹ሳሞስ›› በሚል ምስጢራዊ ስም የሚጠሩት ፀረ-ሚሳዬል መመልከቻ ሳተላይት ስልቶችና ሌሎች በየዘጠና ደቂቃው መሬትን እየዞሩ ሃምሳ ሺህ ወታደሮች በዓመት ውስጥ ከሚሰበስቡት መረጃ እጥፍ የሚበልጥ ጉዳይ የሚሰበስቡትን ሳተላይቶች ቢዘጋቸው የሚከተለውን መገመት ቀላል ነው፡፡ ከዚህም በላይ በብሩህ አእምሮው የሰበሰበውን ምስጢር በምንም መልኩ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ቢሰጥ አሜሪካም ሆነች እስራኤል እንኳን ቦንብ የጫነ አውሮፕላን ማንም ተራ ወንበዴ አሸመድምዶ የሚያፈራርሳቸው ተራ መንደሮች እንደሚሆኑ ያውቁታል፡፡ የአሜሪካን የቴክኖሎጂ ምስጢር እንደውሃ የጠጣው ይህ ሳይንቲስት ጠላቶቻቸው ምድርን የሚንጡ ተምዘግዛጊ ሚሳዬሎች ባለቤት በሆኑበት በዚህ ወቅት በጠላቶቻቸው እጅ ቢገባ የሚከፍሉትን ዋጋ ያውቁታል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሳይንቲስት ከጥበቃው ባሻገር ከአሜሪካ የማያስወጣው ቢወጣ እንኳ ከሁለት ወር በኋላ እያጣደፈ የሚያመጣው የልቡ ጉዳይ ነው፡፡ ......................

ዶ/ር ሚራዥ የኮምፒውተሩን ቁልፎች ሲነካካ ከቆየ በኋላ ተመልሶ ወንበሩን ኢንጂነር ሻጊዝ ወደተኛበት አልጋ አስጠግቶ ተቀመጠ፡፡ ኢንጂነር ሻጊዝም አንዳች መላ ያገኘ መስሎት አይኖቹን በልጥጦ አፍ አፉን ተመለከተው፡፡

"ግዴለህም፡፡ ለዚህ ጉዳይ ጊዜ ስጠኝ፡፡ በየጊዜው የደረስኩበትን ሁኔታ ሪፖርት አደርግልሃለሁ፡፡ ጊዜና ጥብቅ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ምስጢር እስከምንጨ ማወቅ ይገባናል" አለ ዶ/ር ሚራዥ አንድ ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ፡፡

“ግን ቶሎ መሆን አለበት። የልቤ ጉዳይ ከተስተካከለ ….” አዕምሮው ወደ አፍሪካ ገሠገሠ…….. ወደ ኢትዮጵያ።

“ሌላ ጥያቄ የሆነብኝ ነገር……” አለ ዶ/ር ሚራዥ አሁንም ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ እያሰላሰለ ብድግ ብሎ። “ጀርባህ ላይ ያለውን ንቅሣት ልብ ብለኸው ታውቃለህ?” ሲል ጠየቀው፡፡ ‹‹ዴርቶጋዳ›› የሚለውን የጀርባው ንቅሣቱን ፅሁፍ ከጀርባው ዞሮ እየተመለከተ፡፡

“ንቅሣት?”

“አዎ…” አለው ሚራዥ። ‹‹ዶርቶጋዳ…..ስለ ሚለው ንቅሳትህ።፡››

“በወጣትነቴ ነው የተነቀሥኩት” አለ ኢንጂነር ሻጊዝ የወጣትነቱን ዘመን እያስታወሰ።

“ማነው የነቀሰህ?”’

“ማን ነበሩ? አዎ፡፡ አለቃ አያሌው ናቸው! አለቃ አያሌው፡፡”

“አለቃ አያሌው ማን ናቸው?” አለ ሚራዥ በጉጉት፡፡

“አያሌውን የማውቃቸው በልጅነቴ ቦንጋ እያለሁ ነው። ቦንጋ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ከተማ ናት…ኢትዮጵያ ውስጥ” ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ እያሌውን በደንብ ለማስታወስ እየጣረ።

“በልጅነቴ አለቃ አያሌው ወደዚያች ከተማ ሲመጡ አስታውሳለሁ። በጣም ጎበዝ ተረትና ታሪክ አዋቂ ነበሩ። እኔ እንዲያውም አባቴ ካስተማሩኝ ተረት በላይ የነገሩኝ አለቃ አያሌው ናቸው። በተለይ በጣሊያን ጊዜ ስለነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ አብጠርጥረው የሚያውቁ ሰው ናቸው። እርሳቸው እንደነገሩኝ ከሆነ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተደባልቀው የውስጥ አርበኛ ሆነው ተዋግተው ነበር። ጣሊያን ሲባረር የንጉሡን መምጣት ተከትሎ ወደ ቦንጋ ከተማ መጡ። ቦንጋ የመጡበትን ምክንያት ማንም በውል የሚያውቅ የለም። ብቻ ቦንጋ ከቀሩ የጣሊያን ቤተሰቦች ጋር የሚኖር አንድ ዲምላ የሚባል ልጃቸውን ለመጠየቅ ከባህር ዳር ከተማ ተነስተው እንደመጡ ነግረውኛል። ጣሊያኖችን ሲያዩ ይደበቁ ነበር። ከልጃቸው ጋር ስለ ማይስማሙ ከእኔ ጋር ነበር ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉት። ታሪክ ማውራት ይወዳሉ። ስለማዳምጣቸውም ይወዱኝ ነበር። በተለይ ከጣሊያኖች ጋር ስለምቀራረብና በኤሌክትሪክ ሱቃቸው ውስጥ እውል ስለነበር የልጃቸውን ሁኔታ እየተከታተልኩ እናግራቸውም ነበር። አባቴም በኢጣሊያ-ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት በፀረ ፋሽሽት ዘመቻ ጀብዱ የሠራ ወታደር ስለነበር ስለጦር ሜዳ ውሎው ይተርክልኝ ነበር። እሳቸውም የአባቴን አይነት ታሪክ ነበር የሚነግሩኝ። በጣም የተማሩ ሰው እንደነበሩ ተረድቻለሁ። የቤተክህነት ትምህርት በጣም ያውቁ ነበር። እንዲያውም የቤተ ክህነት ትምህርት እንድማር ይገፋፉኝም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ



እንዳነብና ከእያንዳንዱ ስራዬ በፊት እግዚአብሔርን እንዳስቀድም ብሩን የከፈቱልኝ እርሳቸው ናቸው። ከጣሊያኖችም ጋር ብዙ ሞያ እንደቀሰሙ ነግረውኛል።” ኢንጂነር ሻጊዝ ለኒህ ሰው ልዩ ፍቅር ነበረው።

“እና ለምን ነበር ንቅሳቱን የነቀሱህ?”

“በህይወትህ ውስጥ ሊጠቅምህ የሚችል ከባድ ነገር ነው ብለው ነበር የነቀሱኝ። ለልጃቸው ማድረግ የፈለጉትን ነገር ከልጃቸው ጋር ስለማይስማሙ ለእኔ አደረጉልኝ። በወቅቱም ተማሪ ስለነበርኩ እንዲያውም ትምህርትን የሚገልፅ መድሃኒት መስሎኝ ነበር።”

“ትርጉሙን አልነገሩህም?”

“ትርጉሙ…” አለቃ አያሌው ትውስ አሉት .. ተናግረው የማይደክማቸው ሰው ነበሩ። ትርጉሙን ነግረውት ነበር። ግን ትኩረቱ ትርጉሙ ላይ አልነበረም። መድኃኒትነቱ ላይ እንጂ። የትምህርት መድኃኒት መስሎት ነበር……ዘኢያገድፍ። የማስታወስ ብቃትን የሚጨምር መድኃኒት።

“….‹ዶርቶጋዳ› ማለት ምን ማለት ነው?” ብሎ ሲጠይቃቸው ፈገግ ብለው “እንዲያ ነው ልጄ። እንዲያ ነው። መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ። ጎበዝ ልጅ! ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቃለህ?” ብለው መልሰው ጠየቁትና “ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቅ ከሆነ በውሃው ላይ ተያይዘው ተያይዘው ይቆማሉ። ጉንዳኖች ተያይዘው በወንዝ ላይ በሚሠሩት መንገድ ሌሎች ብዙ ጉንዳኖች ይሻገራሉ። ተያይዘው ይሻገራሉ። ተደጋግፈው አስፈሪውን ወንዝ ይሻገሩታል። ባይያያዙና ባይደጋገፉ ግን አይቻላቸውም። አንዲት ጠብታ ዝናብ ለአንድ ጉንዳን ውቅያኖስ ብትሆንም ብዙ ጉንዳኖች አንድ ላይ ከተያያዙ ግን ውቅያኖስ መሻገር ይችላሉ። በመሆኑም ዶርቶጋዳ ማለት……” እስከዚህ የነገሩትን ነግሮት ሌላውን ግን ሊነግረው አልፈለገም። ይህን እሱ ብቻ ሊያውቀው የሚፈልገው ጉዳይ ነው።

“ትርጉሙን ሲነግሩኝ በትክክል አላዳመጥኳቸውም መሰለኝ። ትኩረቴ….. አዩህ….. የመሰለኝ የትምህርት መድሃኒት ነበር። ብዙ ነገር የማወቅ ጉጉት ስለነበረኝ መማር ነበር የዛ ወቅት ታላቁ ፍላጎቴ። ለረጅም አመታትም አእምሮዬ ንቅሳቱን በመድኃኒትነት ተቀብሎት ነበር። ልዩ ኃይል አእምሮዬ ውስጥ እንደሚሰራ በማመኔ በራስ መተማመኔን ከፍ አድርጎልኛል። ሁሉን ነገር ማድረግ እችላለሁ ለማለት እዳፈር ነበር። በውስጤ አንድ አጋዥ ኃይል አለ ብዬ በማመኔም በትምህርቱ አለም የተሳካልኝ ሰው እንድሆን አድርጎልኛል። ከባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ከዲፕሎማ ተነስቼ ያለ ማጋነን ለሳተርን…..ለመሬት … ለማርስና

ለጁፒተር ፕላኔቶች ምርምር የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ ለመሆን ችያለሁ። ታላቅ የዳበረ ሥነ ልቦናም ነበረኝ።”

“አሁንም በዚህ ኃይል ታምናለህ?” ዶ/ር ሚራዥ ተገረመ።

“ማመንም አለማመንም አልችልም አሁን። በዚህ ጉዳይ ያደረኩት ሳይንሳዊ ጥናት የለም። በደፈናው ይሄ ነገር ውሸት ነው ማለት ደግሞ ኢሳይንሳዊ ነው። ያረጋገጥኩት ነገር እስከ አሁን የለም። ሥነ - ልቦናዊ ተፅዕኖው ግን ቀላል አልነበረም።” ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ አያሌው ከጀርባው የነቀሱትን ንቅሳት በመስታወት ካልሆነ በቀር ዞሮ ማየት ስለማይቻል ከ1960ዎቹ ወዲህ ብዙም ትኩረት ሰጥቶት አያውቅም። ረስቶታል ማለት ግን አይቻልም።

‘ድግምት አስርቶ ነው ጎበዝ ተማሪ የሆነው’ ላለመባል ብዙ ጊዜ ጀርባውን ለማንም አያሳይም ነበር። እርሱ ግን ‹እኔ በተፈጥሮዬም ጎበዝ ነኝ። ይህ ንቅሳት በርግጥ ልዩ ኃይል ሊያጎናፅፈኝ ይችላል። ሰይጣናዊ ግን ሊሆን አይችልም። ሰይጣን እንዴት እውቀትን ሊገልፅልኝ ይችላል? ሰይጣን የሰውን ልጅ ትንሣኤና ስልጣኔ የሚደግፍ ከሆነ ሰይጣንነቱ ምን ላይ ነው? አእምሮን ብሩህ አድርጎ የሰዎችን የማስታወስ ችሎታ የሚያበለፅግ ሰይጣን ካለ እሱ እንዴት ጠላቴ ሊሆን ይችላል? ይልቅስ ጥበብ የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ጥበቡን ጥበብን ለሚፈልጉት ያድላል። አለቃ አያሌው ደግሞ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሰው ናቸው። እሳቸው የበይጣን ወዳጅ ከሆኑማ እኛ ሰይጣኖች ነን ማለት ነው። ሰው መጠበብ ሲያቅተው ጥበበኞችን ያጥላላል። ክፉ ስምም ይቀባል። ጠንቋይ ይላል። የኛ ሀገር ጥበበኞች ጠንቋይ እየተባሉ ሲወገዙ የፈረንሳይ ብልጣ ብልጦች የኛን ሀገር የጥበብ መፃሕፍት ወስደው በላቦራቶሪ ፈትሸው ዶ/ር ይባላሉ። ሰው መደንቆር ሲጀምር ጆሮውን ትርፍ ነጋ ይላል። ቢሆንም ሰው በራሱ ምሉዕ ነው። እግዚአብሔር እኔን ለድንቁርና አልፈጠረኝም። አለቃ አያሌው በንቅሳት አእምሮ የሚከፍቱውን መድኃኒት ባይነቅሱኝም እኔ ብሩህ አእምሮ የተሰጠኝ ሰው ነኝ። አለቃ አያሌው ይህን ያደረጉልኝ ስለሚወዱኝ ነው። ሰው መደንቆር ሲጀምር ወሬኛና ሁሉንም ነገር ተቺ ይሆናል። ወሬያም ሁሉ!” ይላል ስለንቅሳቱ ሲያስብ። መልሶ ደሞ “ ምን ይሆን?” ይላል።

ዶ/ር ሚራዥ ከኢንጂነር ሻጊዝ ደርባ ላይ ያለውን ንቅሳት ያየው ቀዶ ጥገናውን በሚደረግለት ወቅት ነበር። በጊዜው ልዩ ስሜት ተሰምቶታል። ንቅሳቱን ሲያይ። ረጅም ሰአታት የወሰደው የኢንጂነሩ የልብ ቀዶ ጥገና ከመጀመሩ ከአንድ ደቂቃ በፊት ለምርምራ የቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ ላይ ሲያገላብጠው ነበር ከጀርባው ላይ ካለው ንቅሳት ጋር የተፋጠጠው። ቀዶ ጥገናው ካለቀ በኋላም ስለንቅሳቱ ሲያስብ ነበር። ኢንጂነሩ ከሰመመኑ ሙሉ በሙሉ ነቅቶ እስኪያናግረው ትዕግስቱ ቢያልቅም መጠበቅ ግን ግዴታው ሆኖ



ነበር። አሁን ከኢንጂነሩ ጋር ስለዚህ ጉዳይ መነጋገር ከመጀመሩ በጥቂት ቆይታ ውስጥ መግባባታቸው ስለ ንቅሳቱ ለሚጠይቀው ማንኛውም ጥያቄ መልስ እንደሚሰጠው ተስፋ አድርጓል። ከኢንጂነሩ ጀርባ ላይ ያለው “ዱርቶጋዳ” የሚለው የቆየ ንቅሳት ደብዘዝ ቢልም በደንብ ይለያል። ከጀርባው በኩል ትንሽ ገልበጥ አድርጎ ንቅሳቱን በደምብ ተመለከተው።

“ዱርቶጋዳ” ከሚለው የንቅሳቱ ጽሁፍ መሀል ያለው ‹ቶ› ፊደል በባለ ጉጥ መስቀል ቅርፅ የተሠራ ነው። በ‹ቶ› ፊደል የአናት ቀለበት ውስጥ በቀጭኑ የተፃፉ ቁጥሮች ይታያሉ። $54_4$ $9_5$ $10_6$ $29_{23}$ $77_5$ $30_{456}$ $52_7$ $33_2$ ፬፬፬ $97_5$ ከሚለው ትንሽና ትልቅ ሆኖ ከተፃፈው ቁጥር ቀጥሎ “ኦርያ ኢትዮጵያ” የሚል በቀጭኑ የተቀረፀ ቃል አለ። ከዚሁ ቀለበት ውስጥም $98_{123}$ $9_6$ $10_{67}$ $40_{567}$ $88_{123456}$ የሚል ቁጥር ይታያል። ከባለ ጉጡ መስቀል መስቀልያ ላይ “ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ” የሚል ቃል የተቀረፀበት ሲሆን በክንፍና በክንፉ መጨረሻ የአበባ ዕምቡጥ ከሚመስሉት የመስቀሉ ጫፎች ላይ “ቀጠሮ ቃል” እና “መራራ ክንፍ” የሚሉና ግራ የሚያጋቡ ቃላት ሰፍረዋል። ከታች ከመስቀሉ ግርጌ ደግሞ ቁልፍ ይመስላል። መልህቅ ከሚመስለው ጫፍ ሥር ደሞ “ዱርቶጋዳ” ይላል።

‹‹የእነዚህን ቃላት ትርጉም አላውቅም ነው የምትለኝ ታዲያ ኢንጂነር ሻጊዝ?›› ሚራዥ ተደምሟል፡

“የጥንት ወፍ ጠባቂዎች፤ እረኞች ሰብላቸውን የሚያወድም ግሪሳ አዝመራቸው ላይ ሲያርፍ በወንጭፍ ድንጋይ ከመወርወራቸው በፊት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ‹ኦርያ!› ይሉታል። ድምፃቸውን ሰምቶ ያልተነሳውን ተባይ ይወነጭፉበታል። በድንጋይም ክንፉን ይሰብሩታል። ስለሆነም **ኦርያ** ኢትዮጵያ ማለት ‘የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ’ የሚል የማስጠንቀቂያ ቃል ነው። ‹ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ› የሚለው ደግሞ **‹ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ!›** ማለት ነው። ኦርያ! ...**ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ**..... የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ.... ምርኮ ፈጥኗል...ብዝበዛ ቸኩሏል። ማለት ነው።...ይህ ለምን እኔ ጀርባ ላይ ተነቀሰ? መልሴ አላውቅም ነው። ግን ለምን ይህን ያህል ትኩረት ሰጠኸው? ከዚህ የበለጠ በንቅሣት የሚሾጎረጎሩ ሰዎች በሞሉበት አሜርካ ውስጥ ተቀምጠህ የእኔ የደበዘዘ ቅንሣት እንዴት ይህን ያህል ሳበህ?” ሲል መልሶ ጠየቀው ሻጊዝ።

“የገረመኝ ይሄ አይደል!” አለ ዶ/ር ሚራዥ። “ካንተ ጀርባ ላይ ያለው ንቅሣት በተመሳሳይ መልኩ እኔ ጀርባ ላይም አለ። ተመልከት!” ነጭ ጋወኑን እና ሸሚዙን አውልቆ ጀርባውን አዞረለት። ሻጊዝ በመገረም የሚራዥን ተመሣሣይ ንቅሣት ከጀርባው ላይ አነበበው። “ዱርቶጋዳ...ኦርያ ኢትዮጵያ...ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ።”

“እንዴት ተመሳሳይ ነገር ሊኖረን ቻለ?”

"ከአሁን ቀደም እንተዋወቅ ነበር?" አለ ኢንጂነር ሻጊዝ።

"በፍፁም ከአሁን ቀደም የጋራ ምስጢር እስኪኖረን ድረስ ልንተዋወቅ አንችልም። በፍፁም። በተለያዩ አለማት የኖርን ሰዎች ነን። እኔ ቅድም እንደነገርኩህ የማውቅህ ባነበብኩትና በሰማሁት ነው። በአካል ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁህ ከቀናት በፊት ይህን ቀዶ ጥገና ሳደርግልህ ነው። ከዚህ በተረፈ ግን እኔና አንተን ሊያገናኘን የሚችል አንዳችም መንገድ አልነበረም። አንዳችም መስመር!"

"የት ነው ተወልደህ ያደከው?"

"የተወለድኩበትን አላውቅም። ያደኩት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ጣና ሐይቅ ውስጥ በሚገኝ አንድ ደሴት ላይ።"

"ጣና ሐይቅ ውስጥ ..... የትኛው ደሴት ላይ?"

"ክብራን ደሴት ላይ። ከባህር ዳር ከተማ በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀው ጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙት እንጦንስና ክብራን በመባል በሚታወቁት መንታ ደሴቶች ላይ ነው ያደኩት። እስከጎረምስ የሴቶች ገዳም በሆነው በእንጦንስ ደሴት...ከጎረመስኩ በኋላ ደግሞ የወንዶች ገዳም በሆነው በክብራን ደሴት ላይ ነው ያደኩት አንተ ደግሞ ከፋ!.....ምን አገናኘን?" አለ ዶ/ር ሚራዥ።

ወዲያው በሩ በኃይል ተበርግዶ ሶስት ሰዎች ወደ ክፍሉ ተንደርድረው ገቡ። ሁለቱ ነጭ ጋወን የለበሱ ዶክተሮች ሲሆኑ የአንደኛው ማንነት ግን አይታወቅም።

"ዳይሬክተሩ በአስቸካይ ይፈልጉሃል ዶ/ር ሚራዥ?" አለው አንደኛው ዶክተር። "ባስቸኳይ!" ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀው ሰውዬ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጣቸውንና የኢንጂነር ሻጊዝን የህክምና መረጃ የያዙትን ወረቀቶች ላፕቶፕ ኮምፒውተሩንም አንስቶ ሊወጣ ሲል ሚራዥ ጎትቶ ወለሉ ላይ ዘረገፈው። ሰውዬው በፍጥነት ተነስቶ ፊገግ አለ በደረቁ። "ቀዩ መስመር ውስጥ ከገባህ ቆይተሀል።" ሽጉጡን መዥርጦ ከሚራዥ ጭንቅላት ላይ አነጣጠረበት። "ቀጥል!.....ዲታላ!"

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በሩን በርግደው ተከታትለው ሲገቡ ጭንቅላቱ ላይ የደቀነውን ሽጉጥ ምላጭ ሳበው። ከተቀመጠበት ወንበር ጀርባ ያለው ነጭ ግድግዳ በደሙ ፍንጣቂ ተጨማለቀ። በጢስ በታፈነው ሳሎን ውስጥ እየተጨናበሱና እያሳሉ አይተው ራሱን ባጠፋው ደህንነት በድን ላይ በብሽቀት ጥይት አርከፈከፉበት። አንደኛው ደህንነት ያገኘውን እቃ እየጠለዘ ሲበሳጭ አንደኛው ደግሞ የስነዱን አመድ ዘግኖ በብሽቀት ሳቀ። በመጨረሻ ከጻፈው አንድ ቃል በስተቀር አንዳችም መረጃ አላስቀረም።.......ሁለቱም ብጣቂው ፅሁፍ ላይ አፈጠጡ።.....«ዶርቶጋዳ?.......ምን!?»......ተያዩ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሚራዥ የህክምና ክፍሉን ለቆ ወጥቶ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ከመሄዱ



በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ኢንጂነር ሻጊዝን ፍዝዝ ብሎ ተመለከተው። ሻጊዝም ሚራዥን በዓይኑ አነጋገረው። በቀዶ ህክምናው ክፍል ውስጥ የተተከሉት ስውር ካሜራዎች የሚቀርፁትን ምስልና ድምፅ ኮምፒውተራቸው ላይ የሚከታተሉት የሆስፒታሉ ዳይሬክተር ዶ/ር ሚራዥና ኢንጂነር ሻጊዝ የተነጋገሩአቸውን የአማርኛ ቃላት ወደ እንግሊዘኛ የሚተረጉመውን ማሽን የዘጉት ዶ/ር ሚራዥ ወደ ቢሮአቸው ሲገባ ብቻ ነበር። ምንም ቃል ሳይተነፍሱ አንድ ገፅ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አንስተው ለዶ/ር ሚራዥ ሰጡት። ከሥራ መባረሩን የሚገልፅ። "ለምን?" አለ ዶ/ር ሚራዥ። ምንም ምላሽ አልሰጡትም ዳይሬክተሩ። "ውጣልኝ አሁን ሥራ ላይ ነኝ።"

# ፪

## ቴልአቪብ ፡ እስራኤል

"በውድ ዋጋ ነው አይደል የተገረዝሽው?" አላት አይኖቹን አጥቦ እየተጠጋት። ሲለምናት ቢኖርም ፍንክች ብላለት አታውቅም።

"አትጠጋኝ" አለችው ውስጧ እያረረ።

"በእውነት ያንቺን ያህል እግዚአብሔርን ብለምነው ሶስት መቶ ሚስቶች ሰጥቶ ሰማኒያ እቁባቶች ይመርቀኝ ነበር" አሁንም እየተጠጋት።

"አትጠጋኝ" አለችው አሁንም ወደኋላ እያፈገፈገች። ቋጥኝ የሚያክል ራሱን እንደ ክር የቀጠነ አንገቱ እስኪቀነጠስ በአሉታ ወዘወዘው። የበለጠ ዓይኑን እያጠበበ ተጠጋት። ቤቷ ውስጥ ባይሆን ኖሮ የያዘችውን የብርጭቆ ውሃ ላዩ ላይ ከልሳበት ባስወጣችው ነበር። ደግሞም አብረው የሚያከናውኑት አንድ የጋራ ጉዳይ አላቸው ።

"ደጋግሜ እንደነገርኩህ አጉል ጊዜህን ባታባክን ይሻላል" ንዴቷን ከውሃው ጋር እየዋጠች ዝም አለችው።

ደረቷ ላይ ተጠጋግተው ከተወጠሩትና ቀጥ ቀጥ ብለው እንደ አምባ ተራራ የቆሙ ጡቶቿ ላይ አይኖቹን ተክሎ በምላሱ ከንፈሩን አረጠበ። በጧት በመምጣቱና የሚቋምጥለት አካሏን በውስጥ ልብስ በማየቱ በጧቱ የቀሰቀሰውን መልአክ አመሰገነው። ተራራ የሚያክል ራሱን እንደ ክር በቀጠነ አንገቱ ላይ አንጠልጥሎ ያቀረቀረ መሰለና ገላዋን ወደ ላይ በደፈረሱ ጥቃቅን ዓይኖቹ እንደ ሸንኩርት መላጥ ጀመረ። እንደ ወርቅ የሚያንፀባርቁ የእግር ጥፍሮቿን ቃኝቶ ሽቅብ ቃተተ። የውስጥ ገላዋን በሚያሳይ ነጭ ስስ የሌሊት ልብሷ ውስጥ የቆመለትን ማራኪ ገላዋን በዓይኖቹ ሽቅብ ሲጠባ ፊት ለፊት ገጥመው የሴትነት መለያዋን የሸፈኑ ጭኖቿ ጠሩት። ‹መሀላችን ግባ ዘግተን የያዝነው ልዩ ዕቃ በመካከላችን አለ› አሉት። ከጎን ሰፋ ያለው ዳሌዋ ከቀጭን ወገቧ ሥር ውሏል። የተቀነበበ እምብርቷን አልፎ ደረቷ አልበቃቸው እንዳለ ተጠጋግተው የተኮፈሱ ትላልቅ ጡቶቿ ከአድማስ ጥግ እንደሚታዩ ተራሮች አልታለፍ አሉት። ከመቃ አንገቷ ላይ የማይለየውንና በትልቅ ሀብል ያሰረችውን በ‹ቶ› ቅርፅ የተሠራ ባለጉጥ ግማደ መስቀል ላይ ሲደርስም ይጥገበኝ ብላ



የቆመች ይመስል ስታየው ቆይታ ፈገግ አለች። የጎመራ የወይን ፍሬ የሚመስሉ ከንፍሮቿ መሀል ችምችም ያሉ ነጫጭ ገዳይ ጥርሶቿን እንደምንም ሲያልፍ የወሲብን ቆሌ የሚጠሩ አይኖቿ ጋር ተጋጭቶ ቆመ። አይቷት የማያውቅ አዲስ ፍጡር አዲስ መስላ ታየችው። ቡዝዝ....ፍዝዝ እንዳለ በማያውቀው ኃይል ተገፍትሮ ከንፈሯ ላይ ሊያሳርፍ የላከው ከንፈሩ በፍጥነት ፊቷን ስታዞር ጆሮ ግንዷ ላይ አረፈ። ወዲያው በአይበሉባዋ የሚያቃጥል ጥፊ ስታሳርፍበት ወደኋላ ተንገዳግዶ ቆመ።

የማይታገላት አደገኛ ሴት ሆነችበት እንጂ ከጭኖችዋ መሀል ገብቶ ለዓመታት የቋመጠለትን ሲሳይ በግዳጅም ቢሆን ሊቋደስ ልቡ ቆርጦ ነበር። ግን ብዙዎችን ያንበረከከችና የሞሳድ ባልደረቦቿ ‹‹አቦ ሸማኔዋ›› እያሉ የሚያመካሹአት ሲጳራ ናት።

ለእስራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ በአባልነት የመለመላትም የህክምና ምርመራዋን የሰራውም ራሱ ነው። ከሁሉም በፊት ያጠመደው ውበቷ። እሱም ውበቷንና እሷን ማጥመድ ጀመረ። ዛሬ ደግሞ ለጋራ የሚያጠምዱት ወጥመድ አላቸው። የእስራኤልን አንድ ወጥመድ በጋራ አጥምደው አሽክላቸው ውስጥ የሚገባውን ታዳኝ አንቀው ለእስራኤል መስጠት አለባቸው። ይህ ተልእኮ የወደቀው በነዚህ ሁለት አይሁዶች ጫንቃ ላይ ነው።

ሲጳራ አናንያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየችው ‹‹ዘመቻ ሙሴ›› በተሰኘው እስራኤል የኢትዮጵያ ፈላሻዎችን በሱዳን በኩል አስኮብልላ ወደ እስራኤል በወሰደችበት ጊዜ ነው።

ዶ/ር አናንያ ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሮ የሞሳድ የህክምና ክፍል አባልና ተመራማሪ ሆኖ ሲሰራ አንድም ቀን ስለፍቅሩና ስለግል ህይወቱ መደላደል አስቦ አያውቅም። የፅዮናዊነት መዝሙር ሲያዜም አደገ። አይሁድነት በደሙ ውስጥ ሲዘዋወር ኖረ። የዘወትር ንግግሩ ማሳረጊያ "እስራኤል ለዘለአለም ትኑር!" ሆነ። ሲጳራን ካያት ጊዜ ጀምሮ የግሉ እንደምትሆን እርግጠኛ ሆኖ ኑሮ ነበር። በተለይ በዚህ ወቅት ፍላጎቱ ንሮበታል። አማላይ ገላዋ አቅበዝብዞታል።

ጥፊውን ወደ ውስጡ ውጦ በቀጭን አንገቱ ቋጥኝ የሚያክል ራሱን ከግራ ወደቀኝ ቀጫ አድርጎ በተለሳለሰ መንፈስ ልመናውን እንደገና ሊጀምር ሲል"አናንያ! እኔና አንተ የተወከልነው ለሀገራዊ ተልእኮ ብቻ ነው። ደግሞ ብቻዬንም ቢሆን እንደምወጣው ታውቃለህ። እመነኝ ....የከፈልኩትን ያህል መስዋዕትነት ከፍዬ ኢንጂነር ሻጊዝን አንቄ ለእስራኤል አስረክባታለሁ። እንዲያውም አንተ የመጀመሪያውንና ተገቢውን ሥራ ሰርተህ ጨርሰሃል። የቀረውን ለእኔ ተወው" እያገለለችው ነው። ዶ/ር አናንያ ግን በዚህ ኦፕሬሽን ምክንያት ከእሷ ጋር አብሮ በመስተፉ ግንኙነታቸውን

ተጠቅሞ የግሉ ሊያረጋት ወስኗል። ደሞም ሲበዛ እልከኛ ነው። እስከመጨረሻው ታግሏት ክንዱ ውስጥ ሊያስገባት ቆርጧል።

ጎትታ ወደ አንዲት ጠባብ ክፍል ይዛው ገባች። በካርታዎችና በፎቶዎች ከተሞላችው ክፍል ውስጥ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን አንደኛውን ትልቅ ፎቶ ጠቆመችው። እንደ ልጃገረድ ጡት የተቀሰሩ ሁለት መንታ ደሴቶች በሐይቁ ላይ ይታያሉ።

"እነዚህ ደሴቶች በኢትዮጵያ የጣና ሐይቅ ላይ የሚገኙ ክብራንና እንጦንስ የሚባሉ ደሴቶች ናቸው። እኔ የሴቶች ገዳም በሆነችው በእንጦንስ ደሴት እሱ ደግሞ የወንዶች ገዳም በሆነው በክብራን ነው ያደግነው" አለች ከሁለቱ መንታ ደሴቶች ፎቶ ላይ ዓይኖችዋን ተክላ። ከማትፈልገው ትዝታ ውስጥ ሊዘፍቃት አዕምሮዋ ወደኋላ በፍጥነት ፈጠነባት። "እሱ ነው የልጅነት ፍቅሬ። መቼም ቢሆን የማልረሳው። ሞቼ እንደገና ብፈጠር እንኳ አብሮኝ የሚፈጠረው። ሚ.... ራ! ሚራዥ"

አእምሮዋ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ወደ ኋላ ሸመጠጠባት። ልጓም አልባ ፈረስ ሆኖ ወደ ደሴቶቹ ጋለበባት። የትዝታዋ ፈረስ ኩቴልአቪብ ተነስቶ እየሰገረ ቀይ ባህርን አቋርጦ ከመካከለኛው የኢትዮጵያ መልእክ ምድር መሃል ከታላቁ የጣና ሐይቅ እምብርት ውስጥ ከሁለቱ ደሴቶች መሀል ወስዶ ዘፈቃት።

በጣና ሐይቅ ላይ አርባ ያህል ደሴቶች አሉ። በሃያ ያህሉ ደሴቶች በውድ ቅርሶች የታጨቁ ገዳማትና አድባራት ሲገኙም በሃያዎቹ ግን ከአሞራዎች በቀር ማንም አይኖርባቸውም። ሲጻራ በትዝታ አውታር ተስባ በመካከላቸው የሰጠመችባቸው ክብራንና እንጦንስ ከባህር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በማራኪ ተፈጥሮአዊ ደን የተሸፈኑት ኮረብታማዎቹ መንትያ ደሴቶች መካከል ያለው ርቀት በጣም አጭር ከመሆኑም በላይ በመካከላቸው ያለው መስተጋብር የጠበቀ ነው። ለሴቶች ገዳም ሥርዓተ ቅዳሴ ለማድረስ መነኮሳት የሚመጡት ከወንዶች ገዳም ነው። ሴቶች ግን ለምንም አገልግሎት ወደ ወንዶች ገዳም አይሄዱም። ውጉዝ ነው። "ለሴቶች ማለፍ የተከለከለ ነው" የሚል በጥቁር ቀለም የተፃፈ ማስጠንቀቂያ ገና ከደሴቱ መግቢያ ላይ አለ።

ሲጻራ ግን ወደዚህ የወንዶች ገዳም ደሴት የምትገባበት ጉዳይ ነበራት። አካሏ ቢከለከልም ልቧ ወደ ወንዶች ገዳም ገብታ ፍቅሯን ከደሴቱ መሏጠጥዋ አልቀረም። ደሴቱን በፍቅር ዓይኗ ማየት የጀመረችውም ሚራዥን ካፈቀረች ጊዜ ወዲህ ነበር። «ለምን ግን እንድገባ አይፈቅዱልኝም? እዚሁ አይደል በንፅህና ያደኩት? ለምን እኔንም እንደ ሌላው ሴት ይከለክሉኛል?......የማልፈልገውን ግን አይከለክሉኝም! ....ወይ ልቤ ሞኙ ለምንድነው ግን የከለከሉትን አጥብቆ የሚፈልግ? ባይከለክሉኝ ይሻል ነበር አለዚያ የሚከለክሉኝ



ያበለጠ እንድፈልገው ያደርጉኛል። እኔ እምፈልገው ሁሉ ያለው ደግሞ ከተከለከልኩት ነገሮች ውስጥ ነው......» ትል ነበር ዘወትር ለብቻዋ ስትሆን።

ሲጻራ ወደ ሴቶች ገዳም የገባችው ገና በሶስት አመቷ ነበር። ወደዚች ደሴት አምጥተው ለሴት መናንያኑ ያስረከቧት ከመንትያዎቹ ደሴቶች በጣም ርቆ በሚገኘውና ዳጋ እስጢፋኖስ በሚባለው የወንዶች ገዳም ውስጥ የሚኖሩት አባ ፊንሐስ ነበሩ። አባ ፊንሐስ ለሴት መናንያኑ ሲያስረክቧት ተጥላ አገኘኋት ብለው ቢሆንም ወላጅ አባቷ ናቸው የሚባል ጭምጭምታም ይሰማ ነበር። ነበር። በድሜ ከፍ እያለች እውነትም ስትመጣ አባ ፊንሐስን እዬመሰለች መጣች።

ሲጻራ ወደሴቶች ገዳም በገባችበት ወቅት በሴት መናንያኑ እንክብካቤ የሚያድግ በሁለት አመት የሚበልጣት ወንድ ህፃን ነበር። የገዳሙ ማህበር ተሰባስበው «አብረው ይደጉ። አብረው መዋላቸው ለሁለቱም ሥነ-ልቦና ይጠቅማል። በዚያውም ግብረ ሕፃናትን ይለማመዱ" ተብሎ በመወሰኑ አብረው ማደግ ጀመሩ።

ህፃኑ ሚራዥም ከየት እንደመጣ አይታወቅም። አባ ዝንበሩ የሚባሉ መነኩሴ እመንገድ ተጥሎ አገኘሁት ብለው ነበር ወደ ሴቶች ገዳም ያመጡት። "እኛም ከየት እንደመጣን አናውቅም። ከየትም ይምጣ ከየት ዋናው የሰው ልጅ መሆኑ ነው። እንዴ እግዚአብሔር ፈጥሮታል። በዝሙትም ይወለድ በጋብቻ ወንጀለኞች ወልደው የጣሉት እንጂ ተጥሎ የተገኘው ልጅ አይደለም። በቤቱ ውስጥ ያድግ ዘንድ አምላክ ሲጠራው እኛ ወደየት እንጥለዋለን?" ብለው ነበር የሴቶች ገዳም እመምኔት እማሆይ ወለተ ኪሮስ አቅፈው ያሳደጉት።

ሚራዥን እማሆይ ወለተ ኪሮስ ፀሎት ሲያደርሱም ሆነ ሲሰግዱ አቅፈውት ነው። መሬትላይ ያስቀመጡት እንደሆነ ወይባ የሚባለውን የምነና ልብሳቸውን ጨምድዶ እንደጠጣ እየተንጠላጠለ እላያቸው ላይ ይወጣል። በኋላ አባ ፊንሐስ ሲጻራን ይዘው የመጡ ጊዜ እሷን እንደጉድ ትክ ብሎ እየተመለከተና እየነካካ አብሯት መጫወት ሲጀምር እማሆይ ወለተ ኪሮስን ረሳቸው። ሲጻራም ዝምተኛው ሚራዥን እንደ አሻንጉሊት እየነካካች ከሱ ጋር በመጫወት አብረው በትንሿ ደሴት ላይ ድክድክ እያሉ አደጉ።

ሚራዥና ሲጻራ ባንድ ላይ ፊደል ቆጥረው የዘወትር ፀሎትን፣ ውዳሴ ማርያምንና ዜማን....በሌሊት፣ ወንጌላትንና መዝሙረ ዳዊትን፣ ከመፅሐፍ ቅዱስም ብሉያትንና ሐዲሳትን እየተማሩ ወደላቀ ደረጃ ተሸጋገሩ። ቀን ቀን እየመጡ ዋርካው ሥር ከሚያስተምሩአቸው አባ ዝንበሩ ከሚባሉትና ሚራዥን ካመጡት መነኩሴ ቅኔም ቆጠሩ።

ሚራኸ ክህነት ተሰጥቶት ቤተ መቅደስ ገብቶ መቀደስ ጀመረ። ሲጻራ ግን ሲያምራት ቀረ። ሲጻራ በንዴት ብትቃጠልም ብቻዋን ከማጉረምረም አልፋ ለማንም አልተናገረችም። «ለፍቼ ለፍቼ ... በሌሊት እንቅልፌን እያቋረጥኩ ተምሬ እንዲህ ጉድ ይሰሩኝ?....ቆይ...እመብርሃን ድንግል ማርያም ሴት አይደለች? በቤተ መቅደስ ውስጥ አይደለም ያደገችው? .....ወይ ፈጣሪዬ ይቅር በለኝ! ...እኔ ደካማዋ ጌታ ኢየሱስን ከወለደችው ከእመብርሃን ጋር ራሴን ስላስተካከልኩ ይቅር በለኝ! ላያስገቡኝ ዝም ብዬ ነው የምወሸከት። ፈጣሪዬ ....ግን እኮ በመቅደሱ ውስጥ ላገለግልህ በመፈለጌ ነው። ምን ሐጢአት አለው እስኪ? አሃ......ለካ እመቤታችን በቤተ መቅደስ የቆየችው አሥራ አምስት አመት እስኪሞላት ነው። እኔም ለካ አስራ አምስት አመት ሞላኝ። ይቅር በለኝ አምላኬ አስራ አምስት ሞልቶኝ ቤተ መቅደስ ለመግባት በመመኘቴ። ውይ! ይቅርታ» ደረቷ ላይ ያጎጠጎጡ ጡቶቿን ስታያቸው ታላቅ ሀጢአት እንደሰራች ጉብጥ ትላለች አፍራ..... ልትደብቅ። በለበሰችው ወይባ አቡጀዲ ሽፍንፍን አድርጋ ምኞቷን ሁሉ ዋጠችው ።

ጡቶቿ ከደረቷ የበለጠ አፈንግጠው ስላጋለጧት አፈረችባቸው። አሽቻቸው እንደሉሚ ሉክሉከው የሚጠፉ መስሏት። የውስጣቸው እንቁር እያመማትም ፈተገቻቸው። እንደ ቡግንጅ ፈርጠው ወይም እንደ ጆሮ ደግፍ ሟሙተው ከደረቷ እንዲጠፉ ተሳለች። ነገር ግን የበለጠ እያሞጠሞጡ እያጎጠጎጡ ቅል ቅል አከሉባት። ውበቱ እንዲጠፋ አፈር በሚመስል ቀለም ተነክሮ በተቀለመ መነከሳቱ ሁሉ በሚለብሱት ልብስ በመሸፈኑ የዳሌዋ መሞናደል ከእሷ በቀር ማንንም አላሳሰበም። ግን ይሞቃታል። የማታውቀው ስሜት ይወስውሳታል። ሰውነቷ ሲሞቃት በፀሎትና በስግደት ለመቅጣት ከተፈጥሮ ጋር ውጊያትጀምራለች። ግን አላሸነፈችም። እየፆመች እየራባትም ዳሌዋ ወደኋላ ጡቷ ወደፊት ይጎትታታል። ልቧም ሚራኸን ሲያይ ከበሮውን መደለቅ ጀምሯል።

በዚህ ወቅት በሁለቱም ገዳማት ማህበራት አንድ ትዕዛዝ ወጣ። "ልጆቹ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ስለደረሱ አብረው እንዳይውሉ" የሚል። ሚራኸ ወደ ወንዶች ገዳም ወደ ክብራን ተወሰደ። የህፃንነቷን ጊዜ ናፈቀች። ከሚራኸ ጋር መዋል ቀርቶ አብራ ቆማ እንኳ ማውራት አትችልም። የእድሜዋ እኩያ ካለእሱ ማንም የለም። ዘወር ስትል የምታየው የጨረጨሱ አሮጊቶችን ቀና ስትል የጠራ ሰማይን ስታቀረቅር የጣና ሐይቅን ነው። ከዚህም ካለፈ በጥቋቁር ፍሬ የጠመሙትን የጣና ዳር የዶቅማ ዛፎች። ወይም የማይናገሩና የማያዩ ዓይናማ አለቶችን።



በተለይ ስለ ሚራኸ የምትሰማው ፍቅሯን የበለጠ አጋጋመው። በአሮጊቶች አፍ ብዙ ይወራለታል። ከሁሉም እማሆይ ወለተ ኪሮስ ድሮም ስለሚወዱት ከአፋቸው አይለዩትም።

ከሚራኸ ጋር መገናኘት ያልቻለችባቸው ጊዜያት ረዘሙ። የማይመሹ ቀኖች! የማይነጉ ሌሊቶች አስቃዩአት። ተረኛ ሆኖ ለአገልግሎት ወደ ሴቶች ገዳም መጥቶ ሲቀድስና ኪዳን ሲያደርስ ብቻ ነበር በቅርብ ርቀት የምታየው። አብረው እንዳያወሩም ክህነቱን እንዳታስፈርሰው ሲባል ‹እንዳታሰናክይው› ተብላለች። ከሐሜትና ከሰይጣን ፈተናም ለመራቅ ጭምር ሲሉ ቢገናኙ እንኳ ሰላም አይባባሉም። "ሁሁ! ለምን አሰናክለዋለሁ! ......ግን ምን መንፈስ ነው ወደሱ የሚጎትተኝ? ለምንድነው ሰውነቴ የሚፈትነኝ? ለምንድነው ነፍሴ እሱን የምትጠማው? ርኩስ መንፈስ ይሆን እንዲህ የሚያደርገኝ! አዎ ዲያብሎስ እየተፈታተነኝ ነው። ሳጥናኤል አሽከላውን እያጠመደብኝ ነው። መቼስ ሰይጣን ጓዙን ጠቅሎ ገዳም ውስጥ አይደል የሰፈረው? በዓለም ማንን ሊፈትን? በዓለምማ ሁሉስ በሐጢአት የወደቀ አይደል! ማንን ይፈትናል? ሁሉስ ሳይፈተን የወደቀ አይደል! እዚህ ነው እንጂ ገዳም ውስጥ ሰይጣን ጦርነት ያለበት። መቼስ መልካም በሌለበት ክፉ የለ! .......ቢኖርስ መኖሩ በምን ይታወቃል? ሰይጣንስ መንፈስ ቅዱስ ባለበት ከሌለ መኖሩ በምን ይረጋገጣል። በርኩስ መንፈስና በቅዱስ መንፈስ መካከል ብዋከብስ እኔ ማነኝ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ የተፈተነው በቆሮንቶስ ተራራ ገዳም አርባ ቀን ሊፀልይ በሄደበት ወቅት አይደል? ኢየሱስን ደፍሮ የፈተነ ሰይጣን እኔንማ ምን ጭንቁ! ይልቅስ ንቆ በተወኝ። የጋለ ገላ የሞቀ ሰውነት ይዤ እንዴት እቋቋመዋለሁ?..... አልችልም።እግዚአብሔር ሆይ እንዳላሰናክለው ከፈለግህ አገልጋይህን ጠብቅ። እንኳን ሰይጣን መልአክ የሚቀናበትን ልጅህን ያዝልኝ። እኔ ግን ተሸንፌአለሁ። እወደዋለሁ። ወድጄን ነው? ጥለህብኝ እንጂ!" ወዲያው ደሞ መኃልዩ መኃልይ ዘሰለሞንን የሚለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ትገልጣለች። "በአፉ መሳምን ይሳመኝ" ይላታል። "ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ መልካም ነው" የልቧን ይነግራታል።

"እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ! እኔ ጥቁር ነኝ፣ ነገር ግን ውብ ነኝ። እንደ ቄዳር ድንኳኖች እንደ ሰሎሞንም መጋረጃዎች።....... ነፍሴ የወደደችህ አንተ ንገረኝ፣ ወዴት ታሰማራለህ፣ በቀትርስ ጊዜ ወዴት ትመስጋለህ?" ይህን ስታነብ ሚራኸ መልሶ "ከዶቅማው ጥላ ሥር በጣና ዳር ዓይናማ አለቶች ጠብቂኝ እመስጋለሁ" ያላት ይመስላታል፡፡

"ከጥላው በታች እጅግ ወድጄ ተቀመጥኩ፡፡ ፍሬውም ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፡፡ ......... ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የእሱ ነኝ፣........ ውዴ ሆይ ቀኑ እስኪነፍስ ጥላውም እስኪሸሽ ድረስ

ተመለስ፤......በቅመም ተራራ ላይ ሚዳቋውን ወይም የዋለው እምቦሳ ምሰል፡፡...... ሌሊት በምንጣፌ ላይ ነፍሴ የወደደችውን ፈለግሁት፤ፈለግሁት አላገኘሁም፡፡........" የሰሎሞን መፅሐፍ ባይኖር ኖሮ መፅሐፍ ቅዱስን አትገልጠውም ነበር፡፡

እነዚህን ጣፋጭ የፍቅር መዝሙሮች ስታነብ ሰውነቷ ይግላል፡፡ ልቧ ነጋሪቱን ይወግራል፡፡ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል፡፡ በጭኖቿ መካከል ቅዝቃዜ ይሰማታል፤ ታማትብና ራዕዩ ዮሐንስ የሚለውን የመፅሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ መፅሐፍ ታነባለች፡፡ ማብረጃዋ እሱ ነው፡፡ ራዕዩ ዮሐንስ.....ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት የፃፈው አስፈሪ መፅሐፍ ለደሴቷ ጉብል የግለቷ መቀዝቀዣ ነው፡፡ እሱ ነው የሚያበርድላት፡፡ ....የመጨረሻው ሰዓት፡፡ ....ዘንዶው፡፡.... አውሬው፡፡ "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፤ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም የነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር..." *ይህ ነው የሚያሰክንላት፡፡* የመጨረሻው ሰዓት፡፡ የአስፈሪው ጊዜ ትንቢት፡፡ ወይም ደግሞ አንቀፀ ንሥሐ የሚባለውን የንስሐ መፅሐፍ አውጥታ ታነባለች፡፡ በንስሐ አለንጋ ራሷን ትገርፋለች፡፡ ወይም ‹‹መንገደ ሰማይ›› የሚባለውን አንዲት ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ ስለምታደርገው አስፈሪ ጉዞ ታነባለች፡፡ መላእክተ ፅልመትና መላእክተ ብርሃን ነፍሷን ሲቃሙ፡፡ መላእክተ ፅልመት ሰይፋቸውን መዘው ከአጋንንቱ ጋር ሲፋለሙ ይታያታል፡፡ ትሰናከናለች፡፡ ጡዳሴ ማርያም ትደግማለች፡፡ እያማተበች ትነሳለች፡፡

መልሳ ደሞ ስለ ሚራዥ ማሰላሰል ትጀምራለች፡፡ ወደሴቶች ገዳም የሚመጣው በተራ ነው፡፡ ሰኞነኛ ሲሆን ብቻ ወር ሲገባ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሳምንታት ሰኞነኛ አገልጋይ ነው፡፡ ቀሪዎቹን ሁለት ሳምንታት ደግሞ በናፍቆት እየተወቀጠች ታሳልፋቸዋለች፡፡ «እዚህኛው ደሴት ሆነሽ እዛኛው ደሴት ድረስ ተጣሪ፡ሁለት ሳምንታት ሳታይው መቆየት ለአንቺ አይቻልሽም» የሚል ሹክሹክታ ይሰማታል፡፡ ትላልቅ አይኖቹን ሙዝዝ ብላ ማየት ያምራታል፡፡

አንድ ቀን ሌሊት መተኛት አቃታት፡፡ እንቅልፍ በዓይኗ አልዞር አለ፡፡ በጨለማው ድባብ ውስጥ እየተደናበረች ከደሴቷ ወደብ ወርዳ አለቱ ላይ ቁጭ አለች፡፡ የጣና ሐይቅ ማዕበል ከአለቱ ጋር ሲጋጭ በሚፈጥረው ፍንጣቂ በውሃ ስትበሰብስ እንኳ አልታወቃትም፡፡ ቆይቶም ሰማዩ በመብረቅ እየታረሰ በጉርምርምታ የታጀበ የዝናብ ዶፍ እዛ የተንጣለለ ሐይቅ ላይ ሲወርድ ከተቀመጠችበት አለት አልተነሳችም፡፡ ወደ ወንዶች ገዳም አሻግራ ማዶ ማዶ እያየች ሌሊቱን እዛው አድራ ጠዋት የኪዳኑ ደወል እስኪደወል አለቱ ላይ ተቀምጣ አነጋች፡፡



በቀጣዩ ሌሊት በስዕለ ቅዱሳን ከተዋበች ጎጆዋ ከገባች በኋላ የመቅረዙን የዘይት ክር ለኮሰችው፡፡ ልታነብ የዘረጋችው መፅሐፍ አፉን እንደከፈተ ነበር፡፡ ራቁቷን ነጭ አቡጀዲ ከላይ የኖረ ሐምራዊ ግምጃ ከሥር ከተነጠፈባት መደቧ ላይ ተኝታ መቅረዙ ላይ አፈጠጠች፡፡ ስቅስቅ ብላ ማልቀሷን ነጩ አንሶላ ላይ የነጠበው የዕንባዋ ጠብታ ነገራት፡፡ ልትፅፍለት ወሰነች የሆነውን ሁሉ፡፡ ፅሁፍ እንድትለማመድበት የመቃ ብዕርና ከተቆሉ አዝርዕትና የተቀመመ ጥቁር ቀለም ነበራት፡፡ ወረቀት ግን መፃህፍት ቤቱ ውስጥ ነበር፡፡ ‹ዛሬ መፃፍ አለብኝ....በቅጠልም ላይ ቢሆን ጭንቄን ተገላግዬ ጠዋት ከኪዳን መልስ እጠብቀዋለሁ ከዛም ሰጥቼው ሹልክ....› ወዲያው አንድ ብልሐት ተከሰተላት፡፡ ከነጩ አቡጀዴ ላይ ቀዳ መፅሐፉ ላይ አስደገፈችና በመቃ-ብዕሯ ከጥቁሩ ቀለም እየነከረች ፃፈችለት፡፡

ጠዋት....የኪዳኑ ፀሎት ረዘመባት፡፡ ትልቁ ደወል ተደውሎ የኪዳኑ ፀሎት እንደተጠናቀቀ በምሥራቁ በር ቆማ ጠበቀችው፡፡ በምስራቁ በር ሴት መቆም ይቅርና ማለፍ አይፈቀድላትም.....እሷ ግን አማራጭ አልነበራትም፡፡ የምሥራቁ በር ተከፍቶ ሚራዥ ነጭ አቡጀዲ ትዕምርተ መስቀል ተላብሶ ብቅ ሲል ወኔዋ ተነነ፡፡ በቆመችበት ተብረከረከች፡፡ ወደወንዶች ገዳም ለመሄድ በቀጭኗ መንገድ ደሴቷን መውረድ ሲጀምር ደንግዛ ቆማ በዓይኑዋ ብቻ ተከተለችው፡፡

ከራሷ ጋር ታግላ የልብ ልብ ከገዛች በኋላ ደሴቷን በሩጫ ወረደችና ከወደቡ ወደ ጀልባዋ ሊገባ ሲል ደረሰችበት፡፡ አብረውት ሁለት ተረኛ ኪዳን አድራሽ መነኩሳትም ነበሩ፡፡ "ሚ....ሚራዥ....?" ጥርሷን ነክሳ ጠራችው፡፡ ከጀልባዋ ወርዶ ወደ እሷ መጣ፡፡ የተጠቀለለ ነጭ አቡጀዲ ጨርቅ በፍጥነት ሰጠችውና "ለማንም እንዳታሳይ!" ብላው እየተንቀጠቀጠች ወደ ጎጆዋ ተመለሰች፡፡ ሚራዥ ከጀልባዋ ወርዶ የክብራንን የወንዶች ገዳም መሬት ከረገጠ በኋላ የደሴቱን ከረብታ በሩጫ ወጥቶ ትልቁ የዶቅማ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ነጩን ቅዳጅ አቡጀዲ ጨርቅ ገለጠው፡፡

*«ሚራዥ በጣም ተጨንቄያለሁ፡፡ ራሴን ለመግዛት ሞክሬ ነበር፡፡ ከማላውቀው ወጥመድ ውስጥ መግባቴን ከአንተ ውጪ ለሌላ ለማንም ብናገር ንስሐ ግቢ ከማለት በቀር ሁነኛ መፍትሔ እንደማይሰጡኝ አውቃለሁ፡፡ የሰይጣን ፈተና ነው ብዬ ለብዙ ቀናት ሰውነቴን በፆም ቀጣሁት፡፡ የሚሰጠኝን መቁነን በድብቅ ለወፎች እየበተንኩ ሳልበላ ለብዙ ቀናት ቆየሁ፡፡ መልክአ ኢየሱስን፣ ድርሳናትን፣ መስጥመ አጋንንትን፣ ገድለ አቡነ ዘዮሐንስን ሁሉ እየደገምኩ በሱባዔ ለብዙ ሳምንታት*

*አሳለለፍኩ፡፡ እመ ምኔታችን እማሆይ ወለተ ኪርስ ስቅበጠበጥ አይተው በሽንቁሩ ግንድ አሰረውኝ ስፀልይ ለነበትኩ፡፡ ልድን ግን አልቻልኩም፡፡ ፈተናዬ የሀሊና ዕረፍት ነሰቶኛል፡፡ ከእግዚአብሔር ቤት አስወጥተው አጋንንት በደስታ ሲስቁብኝ በጆሮዬ ይሰማኛል፡፡...ሚራዥ እባክህ ድረስልኝ፡፡ ደግሞ እውነቱን ሳልደብቅ ልንገርህ፡፡ በየደቂቃው አንተን ማዬት ያሰኘኛል፡፡ለምንድን ነው?.......... ሚራዥ....... ሰይጣናት ጥለው ሲዘባበቁብኝ ማየት ትፈልጋለህ? .....እንግዲያውስ ዛሬ ማታ በታንኳም ቢሆን መጥተህ ችግሬን ካልፈታህልኝ የመጨረሻ አማራጬ ራሴን ወደዚህ ሐይቅ ወርውሬ ለሰይጣናቱና ለአጋሮቻቸው እጄን መስጠት ነው፡፡ መቼም ከዚህ በላይ ስቃይ አይኖርı ዛሬ ማታ ከደሴቱ ወደብ ትልቁ አለት ላይ እጠብቅሀለሁ፡፡ እንባበህ ስትጨርስ አጥበህ ጣለው ካለቀቀልህ አቃጥለው፡፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡ »*

ሚራዥ ደብዳቤውን አንብቦ ሲጨርስ ተነስቶ በደስታ ዘለለ፡፡ በእሱ ውስጥ መከራ ሲያሳየው የኖረው ስሜት በእሷም ውስጥ በመኖሩ ሐሴት አደረገ፡፡ «ሲጳ... እኔ አንቺ ያለሽበትን ደሴት አሻግሬ እያየሁ ትልቁ ዛፍ ላይ ወጥቼ እንደምውል ማን በነገረሽ?..... ይምሽ እንጂ በዋናም ቢሆን አልቀርም፡፡» ሳይታወቀው እየለፈለፈ ነበር፡፡

ቀኑ አልመሸለት አለ፡፡ እንደ ሁልጊዜው መኃልዬ መኃልይ ዘሰሎሞንን ደግሞ ደጋግሞ አነበበው፡፡ «አስተማሰልኩኪ አንተ ሃቤዬ ጥቀ አዳም መላትሕኪ ከመ ማዕነቅ ወክሣድኪ ከመ እርማስቆስ፡፡ አምሳለ ወርቅ ይግበሩ ለኪ ኮሰኮሰ ዘብሩር .» እሱዋ ደግሞ ከማዶ «ውዴ ሆይ ቀኑ እስኪነፍስ ጥላውም እስኪሸሽ ድረስ ተመለስ» ብላ የመለሰችለት መሰለው፡፡

«የለም ቀኑ አልመሸልኝም፡፡ ከማይመሽ ቀን የማይነጋ ሌሊት ይሻላል» አለ እየተንጠራራ፡፡ «ኲለንታኪ ሰናይት አንተ ሃቤዬ፡፡ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ፡፡ ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ፡፡» የሚሉ የሰሎሞንን መኃልያት ሲመላልስ ለእብደት ሊዳርጉት እንደሚችሉ ፈርቶ ተነስቶ ለጉብኝት ከመጡት ፈረንጆች ጋር ወደ ዕቃ ቤት አመራ፡፡ ከምንጊዜውም በበለጠ በዛ ሙዚየም የሚገኙትን ቅርሳቅርሶች በሙሉ ከሰፊ ማብራሪያ ጋር ሲሰጥ ዋለ፡፡ በአስተርጓሚ፡፡

"ቤተ ክርስቲያኑ የተሰራው በተጠረቡ ቀይ ድንጋዮች ነው፡፡ እነዚህ በመቅደሱ ዙሪያ የምታዩአቸው ከጥርብ ከድንጋይ የተሰሩ አስራ ሁለት አምዶች ናቸው፡፡..... ከመቅደሱ ግድግዳ ጋር ተያይዞ የተሰራው ሕንፃ የገዳሙ መስራች የአቡነ ዘዮሐንስ መቃብር ነው፡፡..... ይህ ቤተክርስቲያን እንደምታዩት በደሴቱ እናት ላይ ነው የተሠራው፡፡.... ይህ የድንጋይ ደወል ነው፡፡..... በዚህ ዕቃ ቤት



ውስጥ ከአስደናቂ ቅርሶች አንዱ ይህቺ በወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በራሱ እጅ የተሳለችው የቅድስት ማርያም ስዕል ናት፡፡ ..............ይህ ከብረት የተሰራው የአቡነ ዘዮሐንስ የፀሎት ልብስ ነው፡፡....ወደዚህ ገዳም መግባት የሚችሉት ወንዶች ብቻ መሆናቸው ለየት ያደርገዋል፡፡ በዳጋና በአንዳንድ የጣና ገዳማት ሴቶች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡ ......እዚህ ቀጥሎ ካለው ደሴት ደግሞ ሴቶች ብቻ የሚኖሩበት ገዳም አለ» እያለ ያልጠየቁትን ሁሉ ሲለፈልፍ ትዝ አለችው፡፡ ሲጳራ፡፡ ሳይሰናበታቸው ወጥቶ ሄደ፡፡ ሌላ ሰው ተጠርቶ አስጎበኛቸው፡፡

ሲጳራ በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ አለቱ ላይ ቁጭ ብላ ሚራዥን ስትጠብቅ መንፈቀ ሌሊት አለፈ፡፡ አላስችል አላት፡፡ ልብሷን አወላልቃ ወደ ጣና ተወረወረች፡፡ ወደ ወንዶች ደሴት መዋኘት ጀመረች፡፡ እየመጣም ከሆነ እዛው ሐይቁ ውስጥ አገኘዋለሁ፡፡ሊያጋጥማት የሚችለው ዓዞና ጉማሬ አላስጨነቃትም፡፡ በሀፃንነቷ ስትዋኝ አትደክምም ነበር፡፡ አሁን ግን በፍርሃት የሚርድ ሰውነቷ አልንሳፈፍ አላት፡፡

የሚዋኝ ሰው እየቀረባት መጣ፡፡ "ሲጳራ!" አላት የለሆሳስ ድምፅ፡፡ የምታውቀው ድምፅ፡፡ ራሷን ብቅ አድርጋ "ወዬ" አለችው፡፡

"ምነው?" አላት በድንጋጤ፡፡

"ቆየህብኝ::"

"እሺ ተመለሽ ወደመጣሽበት ዋኚ"

"ደክሞኛል፡፡ አልቻልኩም::"

"አይዞሽ::"

"እያቃተኝ ነው ሚራዥ" እያቃተኝ ነው ስትል ደበልጥ አቃታት፡፡ ተጠግቶ ደገፍ አደረጋት፡፡ ሰውነቷ ይፋጃል፡፡ ሰውነቱን ነዘረው፡፡ ትንፋሿ ለመጠጠው፡፡

"አይዞሽ እየደረስን ነው፡፡" የልብ ምቱ ሲፈጥንበት ታወቀው፡፡ ውሃው ውስጥ ሆኖም አቃጠለችው፡፡ እሷንም እያቃጠላት ነው፡፡ ከሐይቁ ዳር ሲደርሱ አለቱ ላይ የጣለችውን ልብሷን ለበሰች፡፡

ሚራዥ በዋና ሲመጣ ራሱ ላይ የደገለለውን ልብሱን ፈትቶ ለብሶ ሁለቱም አለቱ ላይ ተቀምጠው በፀጥታ ተዋጡ፡፡ አብረው ሲያድጉ ከእፍ እየተቀማሙ ይጫወቱት የነበረው ሁሉ ዛሬ ውሃ በላው፡፡ የሁለቱም አንደበት ተሳሰረ፡፡

«ሚራዥ..... በጣም በረደኝ!...» አለችው ጥርሶቿን እያፋጨች፡፡

"ምን ይሻላል?"

"ለምን ወደኔ ጎጆ አንሄድም?" ስትፈራ ስትቸር ጠየቀችው፡፡

"እንዴ! ......እሱማ ከባድ ነገር ነው፡፡"

"እንዴት?"

"ሰ.... ሰው ቢያየንስ?"

"እና ምን ተሻለን?"

"እሺ ከገዳሙ ውጭ ካለው ቆርቆሮ......" ድፍረቷ ገረማት።

"እመቃብር ቤቱ ዘንድ?"

"እም። ለብርዱ እዛ........"

"እሺ። እንሂድ" ሚራዥ እደገኛውን ነገር እያደረገ መሆኑ ቢሰማውም አላቅማማም።

እመቃብር ቤቱ ውስጥ ገብተው ከውስጥ ቀረቀሩት። የመቃብር ቤቱ ወለል አፈር እስከቁርጭምችሚታቸው ዋጣቸው። ከምንም አልጣፋት። ሚራዥ ከግድግዳው ላይ የተሰካውን ደረቅ ሣር አውርዶ ጎዝጉዘውና ተቀመጡ። ዝምታ።

«...እማሆይ ወለተ ኪሮስ እየተሻላቸው ነው?» አላት ዝምታቸውን ለመስበር ያህል።

«የለም እየባሰባቸው ነው።ሐኪም ቤት ሊወስዱ ሲለምኑ ‹የሚያድንም የሚገድልም እግዚአብሔር ብቻ ነው› ብለው እምቢ አሉ።እርጅናውም እየተጋፋቸው ነው።»

"ምን ነበር ያስጨነቀሽ?" አምጦ ጠየቃት።

"እኔ እንጃ!" የምትለው ጠፋባት።

"እንዴት?" ገብቶታል። ግን.........

"ብቻ አንተን ........." መናገር አልቻለችም። ‹ምን አይነት ገመና ነው? ለምን ይጠይቀኛል? ዝም ብሎ እንደ እኔ.....› በውስጧ ተብሰለሰለች።

"ሚራ... በቃ...የሆነ ነገር አስኝቶህ ያውቃል አይደል?" አለችው የግዷን።

"አዎ.....አንዳንድ ነገሮች ያሰኙኛል። አንዳንዶችን ላገኛቸው ስችል ሌሎች ደግሞ የማላገኛቸው ናቸው።"

"እኔን ደግሞ የሚያሰኘኝ ......የሚያሰኘኝ ... በቃ.......አንተ አሰኝተኸኛል። አሰኘኸኝ።" ተገላገለችው።

"ማለት......."

"አሰኘኸኛ በቃ ውህ!" ሌላ ጥያቄ እንዳይጠይቃት ፀለየች።

"እኔንም አሰኝተሽኛል።....... ማለቴ..." እንገቷ ውስጥ ተሸጎጠ።ትንፋሿና ትንፋሹ በፍጥነት ተዋሃዱ። የማያውቁት መግነጢሳዊ ኃይል አዋሃዳቸው። ከንፈር ለከንፈር ሲያያዙ ምን እያደረጉ እንደሆነአላወቁም።............... ብቻ ሁለቱም ከሰሎሞን የመዝሙር መፅሐፍ ውስጥ ያነበቡአቸው በዕዝነ ህሊናዎቻቸው ተደመጡአቸው።......ሳይታወቃቸው የንጋቱ ደወል በሁለቱም ደሴቶች ላይ ተሰማ። ሁለቱም የንጋቱን ደወል በልባቸው ሳይረግሙት አልቀሩም።



የመቃብር ቤቱን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት በትልቅ ሰንሰለት የታሰረ በ ‹ቶ› ቅርፅ የተሰራ ግማደ መስቀል ከአንገቱ አውልቆ አሰረላት።

"አመሰግናለሁ ..... መስቀሉ በጣም ያምራል ....መስቀሉን ሳይ አንተ ከእኔ ጋር እንደሆንክ እያሰብኩ....." መስቀሉን ጭብጥ አድርጋ። "..... መቼ ነው ተመልሰህ የምትመጣ?" አለችው። ተመልሰው የሚገናኙበት ጊዜ እንደ አድማስ ጥግ ርቋት።

"ተነግ ወዲያ ማታ እዚሁ መቃብር ቤት ውስጥ እንገናኛለን"

"እስከ ነገ ወዲያ!.... ሩቅ ነው። ግን እጠብቅሃለሁ።.... እንዳትቀር እሺ?"

"..... አልቀርም። ይልቅስ አንቺ እንዳትቀሪ" ወደ ወደቡ በጫካው ውስጥ ለውስጥ እየጣሰ ወረደ። ከወዲያኛው ማዶ የወንዶች ደሴት እየዋኘ እስኪደርስ ሐይቁ ዳር አለቱ ላይ ተቀምጣ በዓይኗ ሸኘችው። እዛኛው ማዶ ወደብ ሲደርስ እጁን አውለበለበላት።እሷም ከተቀመጠችበት አለት ተስፈንጥራ ተነስታ ሁለት እጆችዋን አወናጨፈቻቸው።

ከሶስት ቀናት በኋላ እንደገና መቃብር ቤቱ ውስጥ ተገናኙ።....... ከሌሊቱ አጋማሽ ላይ ላይ እሪታ ከሴቶች ገዳም ተሰማ። መቃብር ቤቱ ውስጥ ባሉበት በድንጋጤ ድርቅ አሉ። የሴት መበለቶች ድምፅና ኡኡታ እየበዛ እሪታው እየበረከተ መጣ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አካፋና ዶማ የያዙ መቃብር ቆፋሪዎች ወደ መቃብር ቤቱ ከንፈራቸውን እየመጠጡ መጡ። ሲጻራ በፍርሃት የሚራዥን ክንድ አጥብቃ ያዘችው። "ከውጭ ነው የምንቆፍረው ከውስጥ?" ሲል አንዱ ወደ መጡበት ድምፁን ከፍ አርጎ ጠየቀ።

"ወይኔ ሰው ሞቶ የመቃብር ጉድጓድ ሊቆፍሩ ነው እንዴ?" በጆሮው አንሾካሾከች። ክው አሉ።

"የታመመ ሰው አለ እንዴ ?"

"እማሆይ ወለተኪሮስ ሞቱ ማለት ነው። ሌላ የታመመ የለም።"

"የኛ መጨረሻ ይሄ ነው?.... ወይኔ እግዚአብሔር ተጋለጥን። ምናለ........."

"ምን ዓይነት ፈተና ነው............" አፏ መረራት።

"እሽ ወጥተን.........."

"እንዴ በር ላይ እኮ ናቸው!"

"ቆይ እንዴት መጡ?"

"በታንኳ መጥተው ይሆናል!"

"ምን ሰራሁ እመብርሃን! ውይ..."

መልሱን ይዞ የመጣው ሰውዬ "ከውስጥ ይቆፈር ብለዋል" አለ እየተንፋነፈ፡፡

"ከውስጥ ከሆነማ መብራት ይዘህ ና እንጂ! ዱሮስ እማሆይ ወለተ ኪሮስን ያክል እናት ሜዳ ላይ ይቀበራሉ?" በሩን እያንቋቋ ከፈተው፡፡

".....ሰው አለ እንዴ?" አለ እስከ ዓይናቸው አስግጎ፡፡ የተቀመጡበት መሬት ተከፍቶ ሲውጣቸው በወደዱ፡፡

"እንተ አባ ፊንሐስ ?! እረ ሰው ነው! .....እስኪ ጧፉን አምጡት!" አለ ወደፊታቸው ይበልጥ አይኑን እያፈጠጠ፡፡፡ የጧፉ ብርሃን ከሁለቱ ዓለም ሰዎች ላይ መጥፎ ፀዳሉን ጣለ፡፡ ለሁለቱም ያ የጧፍ ብርሃን ከጨለማ የባሰ ርጉም ነበር፡፡

"ኧረ የእስራኤል አምላክ ምኑን አሳየኸኝ!?" አባ ፊንሐስ ፊታቸውን አዞሩ፡፡ ከዳጋ እስጢፋኖስ የመጡት የእማሆይ ወለተ ኪሮስ በጠና መታመም ሰምተው ቢሆንም ከሲጳራ ጋር የሚነጋገሩበት ጉዳይም ነበራቸው፡፡

"ኧረ ጉ.....ድ! ኧረ!... ኧረ !.....ስአሊ ለነ ቅድስት!..... የግሸኗ እመቤት! .....ፍጡነ ረድኤት! " ሁለተኛው ቆፋሪ መነኩሴ አባ ማቴዎስ ራሳቸው አፍረው ዓይኖቻቸውን በእጆቻቸው ጋረዱ፡፡

"ሚራዥ.... ምነዋ የኔ ልጅ.... ሙዳሴ ማርያም መድገም ተውክ እንዴ? ምነዋ ሰይጣንን በፀሎት ብትዋጋው!? " አባ ፊንሐስ ያልጠበቁት ዱብ እዳ ነበር የገጠማቸው፡፡

"ምነዋ ልጆቼ ........ ጉድ! ጉድ!.... ጉድ ነው፡፡" አባ ፊንሐስ ከአንድ ቀን በፊት ከዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መጥተው ለሲጳራ መንፈሳዊ ብርታት የሚሰጥ ያሉትን ቀኖና እና ስግደት ሰጥተዋት ተመልሰው ነበር፡፡ ወደሴቶች ገዳም የመጡት የሴቶች ገዳም እመምኔት የሆኑት እማሆይ ወለተ ኪሮስ መድከማቸውን ምክንያት በማድረግ ቢሆንም ከሲጳራ የሚፈልጉት አንድ ታላቅ ጉዳይ ነበራቸው፡፡ ሲጳራን እየዞሩ የሴቶች ገዳም ውስጥ ሲፈልጉም ነበር፡፡

ሚራዥ እፉ ተሳሰረ፡፡ ሲጳራ እንዳትደነግጥ ሲል የራሱን መሸማቀቅ ወደ ውስጡ አመቀው። "አይዞሽ......" እጇን ይዟት ከመቃብር ቤቱ ወጡ፡፡

እሱም ተጨንቋል፡፡ ነገር ግን ምንም ያልተሰማው መስሎ እያፅናና ይዟት ወደ ወደቡ ወረደ፡፡ ከወደቡ የተጠጋ ታንኳና ጀልባ ሲያይ ወደታንኳው እየመራ

"ተከተይኝ" አላት፡፡ "አብረን እንሄዳለን፡፡"

"ወዴት መሄድ እንችላለን?"



"ወደየትም ይሁን፡፡ ብቻ ከዚህ መውጣት አለብን፡፡ ከአሁን በኋላ ተእነዚህ ገዳማት ውስጥ መኖር ለእኔና ለአንቺ የማይቻል ነገር ነው፡፡.... እንኳን በአንድ ቤት ውስጥ ጨለማ ለብሰን አግኝተውን ቆመን እንዳናወራ መከልከላችንን መዘንጋት የለብሽም፡፡"

"ተረድቼሃለሁ ሚራ........ ግን ......... ወዴት ብለን እንሄዳለን?" ከመንታወቹ ገዳማውያን ደሴቶች ውጭ የሚያውቁት ዓለም እንደሌለ ታውቃለች ሲጳራ፡፡

"ጉዞውን እንጀምረዋለን.... መድረሻችንን አካሄዳችን ይወስነዋል፡፡ አትፍሪ፡፡ ወደየትም ይሁን ብቻ እግራችን ወደሚወስደን ቦታ እንሂድ...."

«እሺ. ታንኳ ጋር ልሁን እንጂ ብቻ የትም ይሁን እንሂድ»

ከታንኳው ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እጇን ጥብቅ አድርጎ ይዟት ቆመ፡፡ በከፊል ደመና የተሸፈነችው ጨረቃ በምትረጨው ቀዝቃዛ ብርሃን ደረቷ ላይ ያሰረላት ግማደ መስቀል ሲፈልቅ የውስጧ የፍቅር ነሀብራቅ ልቡ ላይም ፈለቀ፡፡ ያሰረላትን መስቀል ጥብቅ አድርጋ ይዛ "መቼም አልጥለውም እሺ.....ስጦታህን እድሜየን በሙሉ ይገናው እኖራለሁ፡፡..... ትናንት አባ ፊንሐስ ያሰርከልኝን መስቀል ‹ስጭኝ › ብለው ለምነውኝ ነበር፡፡ እምቢ አልኳቸዋ" ከዓይኖቹ ውስጥ የወጣ የማትቆጣጠረው ኃይል አስፈንጥሮ ደረቱ ላይ አላጠቃት፡፡ ተብሰክስካ ከንፈሮቹን ጎረሰችው፡፡ እሱም ተንገብግቦ ጎረሳት፡፡

ወዲያው ከኋላዋ እጅዋን ለቀም አድርጎ አንድ ሰው ሲጨብጣት በድንጋጤ ጮኸች፡፡ አባ ፊንሐስ ናቸው፡፡ ምንም ሳይናገሩ በፍጥነት ሞተሩን አስነስቶ ከሚያጓራው ጀልባ ውስጥ ጎትተው ከተቷት። ጀልባውን የሚነዱት መነኩሴ አባ ማቴዎስ ናቸው። የሞተሩ ድምፅ ይበልጥ ጨመረና ኃይቁን በሐይል ቀዝፎ ይዟት ጉዞ ሲጀምር ሲጳራ እሪታዋን አቀለጠችው።

በተለይም ጀልባው እሷን ብቻ ይዞ ባህሩን እየሰነጠቀ ሲሄድ ኡኡታዋን አቀለጠችው። አባ ፊንሐስና ጀልባውን የሚነዱት መነኩሴ አባ ማቴዎስ አንድም ቃል ሳይተነፍሱ ዝም አሏት። በዋና ወደ ሚራዥ ልትሄድ ወደ ሐይቁ ተወረወረች። አባ ፊንሐስ እጆቿን ይዘው እንደ ገና መልሰው ጀልባው ላይ ጭነው ይዘዋት ከነፉ። የሚራዥ ደምፅ ከሩቅ ይሰማታል ሲጠራት የህልም ጥሪ ሆነባት። ድምፁ እየራቃት ሄደ። የሞተሩ ድምፅና የጣና ማዕበል ድምፁን ዋጡባት። ሁለቱን መንትያ ደሴቶች ወደኋላ እያየቻቸው እንደህልም አለም እየራቋት ከእይታዋ ውጭ ሆኑ።

ሚራዥ ዘሎ ሐይቁ ውስጥ ገብቶ በዋና ጀልባውን መከተል ጀመረ፡፡ በጀልባውና በእሱ መካከል ያለው ርቀት የአድማስ ዳርቻ ያህል ሲርቀው ሆዱን ባር ባር ብሎት ዕንባ ባነቀው ድምፅ ለመጨረሻ ጊዜ ተጣራ፡፡ "ሲጻራ…ሲጻ……ሲ……ሲ……ሲ….." ተስፋ የከዳው የሰለለ ድምፁ ለእሱም አልሰማው አለ፡፡ የእሷም ድምፅ እየሰለለ እየመነመነ በጣና ማዕበል ተዋጠ፡፡ ውሃውን ጨብጦ ወደ ሄደችበት በትኖ እየተነፋረቀ በሁለቱ ደሴቶች መካከል ፈዞ ቀረ፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በኋላ አራት መነኮሳት ሚራዥን ይዘውት ወደ ገዳሙ ጀልባ ከተቱትና ወደ ነበረበት ክብራን የወንዶች ገዳም አሻገሩት፡፡ ሁሉም በሀዘን ተውጠዋል፡፡ እማሆይ ወለተ ኪሮስ በመሞታቸው ብቻም ሳይሆን በሚራዥ መውደቅ ምክንያት፡፡ በሚራዥና በሲጻራ መካከል ስለተፈጠረው ነገር ብዙዎች መነኮሳት የሰሙት ሚራዥ ወደነበረበት ወደ ክብራን የወንዶች ገዳም ከተመለሰ በኋላ ነበር፡፡ ከእማሆይ ወለተ ኪሮስ ሥጋዊ ሞት በላይ አሳዛኝ የሆነው የሚራዥ የቁም ሞት ነበር፡፡ መነኮሳቱ ለስንት ነገር ይደርሳል ያሉት ብላቴና የቤተክርስቲያን አገልጋይ በሰይጣን ወጥመድ ገብቶባቸዋልና አዘኑ፡፡

በተለይ የክብራን ገዳም አበምኔት የሚሉት ጠፍቶባቸው ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ "መታሰር አለብህ፡፡ ሰይጣንን ልትዋጋው ይገባል" ብለው መነኩሴ ሲተላለፍ እንደሚደረገው ሁለት ቀዳዳዎች ባሉት ግዙፍ ግንድ ሁለት እግሮቹን በቀዳዳዎቹ ውስጥ አሾልከው በእግረ ሙቅ አሰሩት፡፡ የእግረሙቁን ቁልፍ ማህደራቸው ውስጥ ከተው እየተበሳጩ ሳያናግሩት ባዶው ቤት ውስጥ ጥለውት ሄዱ፡፡

ከሰዓታት ቆይታ በኋላ መለፍለፍ ጀመረ፡፡ "ፍቱኝ! ..አትለዩኝ!….. ሰይጣን አይደለም….." ማንም የሚመልስለት የለም፡፡

ሁሉም መነኮሳት በደንጋዩ ደወል ተጠርተው ከተሰበሰቡ በኋላ እንዲፀልዩለት አበምኔቱ አሳስበው አስናበቱአቸው፡፡ በክብራን ገዳም ውስጥ ሁለት የድንጋይ ደወሎች አሉ፡፡ ትልቁ የድንጋይ ደወል መነኮሳቱን መሰብሰቢያ ሲሆን ትንሹ ደግሞ ስብሰባውን መበተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በትልቁ የድንጋይ ደወል የተሰበሰቡት መነኮሳት በትንሹ የድንጋይ ደወል ድምፅ ሲበተኑ ጀምረው ሁሉም ለሚራዥ ፀሎት ማድረስ ጀመሩ፡፡

"እናንተ ሽማግሌዎች! የማታውቁትን ለምን ታደርጋላችሁ? ፍቅርንና ሰይጣንን ለይታችሁ ማወቅ ለምን ተሳናችሁ?…. ፍቱኝ! …አላበዛችሁትም? …..ጥላኝ ሄደች!…. ፍቱኝ…..አፍነው ወሰዷት፡፡ ላስጥላት ፍቱኝ፡፡ ስለራሳችሁ ፀልዩ፡፡ እኔ ጤነኛ ነኝ፡፡ ጤና ያጣችሁ እናንተ ናችሁ፡፡……." ሚራዥን የሚያዳምጥ ጆሮ ግን አልነበረም፡፡



አርባ ቀን ሙሉ ታስሮ ሲለፈልፍ ከረመ፡፡ አልተሻለውም፡፡ መለፍለፉ ሲታገስለት የተመለሰ መስሏቸው በፈቱት ማግስት በአሮጌ ታንኳ እየቀዘፈ ሁለቱን መንታ ደሴቶችና ገዳማት ጥሏቸው ሸሸ፡፡

ባህርዳር ከተማ ሲደርስ ሁሉም ነገር ተደነጋገረው፡፡ የማያውቀው ዓለም፡፡…. መኪና፡፡ ……ግርግር፡፡ ……ሱሪ ያጠለቁና ዳሌያቸውን የሚወዘውዙ ሴቶች፡፡ ጭናቸውንና እምብርታቸውን የሚያሳዩ ልብሶች የለበሱ ልጃገረዶች፡፡ ስንቷን ሴት እያየ ሲጻራ መሆን አለመሆንዋን መለየት ይቻላል? አፍጥጦ ሲያያቸው "እህ! ይህ ደሞ ምኑ ባላገር ነው ከእብዶች ሆስፒታል የተለቀቀ መሆን አለበት፡፡ ምን እንደ ቡዳ አፍጦ ያያል? …" እያሉ ገላምጠውት ይሄዳሉ፡፡ እሱ ግን ሲጻራን ከዚህ ሁሉ ሴት መሀል እንደማያጣት እርግጠኛ ነበር፡፡ አቅጣጫ እንደሳተ የተገለጠለት ቆይቶ ነው፡፡

በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰላሰለ ከባህር ዳር ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በረንዳ ላይ እየተኛ ሲዋትት ሰነበተ፡፡

አንድ ቀን ከተኛበት በረንዳ አንድ ሰው ሲቀሰቅሰው ተሰማው፡፡ ቀና ሲል ሞተሩን ያላጠፋ የጭነት መኪና ቆሞ ሸራው ውስጥ ሰዎች እየገቡ ተመለከተ፡፡ ሁለት ኮማንዶዎች ወርደው ክንድና ክንዱን ይዘው መኪናው ውስጥ ጫኑት፡፡ ከብዙ ጉዞ በኋላ ለውትድርና ከታፈሱት ሰዎች ጋር አንድ በረሀ ውስጥ አብሮ ተራገፈ፡፡ "ግራ ቀኝ፣…ቀኝ ግራ፣…..ወደኋላ ዙር! ….ወደፊት! …እናት ሀገር" ምናምን፡፡ ጊዜው ወታደራዊዉ የደርግ መንግስት የሞት ሽረት ትግል በሰሜኑ አካባቢ የሚያደርግበት ወቅት በመሆኑ የዚህ ጦርነት ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ያገኘውና የሰሜኑን ጦር የተቀላቀለው ከአድካሚ ስልጠና በኋላ ነበር፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

እነ ሲጻራ ሲነጋጋ ጎርጎራ ወደብ ደረሱ፡፡ ጀልባዋን እዛው ትተው ወደ ሰሜኑ አቅጣጫ ረጅም የእግር ጉዞ ካደረጉ በኋላ አንድ ቀጥቃጮችና እንጥረኞች ከበዙበት መንደር ደረሱ፡፡ ማንም አይነጋገርም፡፡ ዝም ብሎ መጓዝ፡፡ ከዚህ መንደርም ብዙ ሰዎች ጓዛቸውን እየጠቀለሉ ተከተሏቸው፡፡

ከቀናት ጉዞ በኋላ የጎንደርን ከተማ ወደጎን ትተው ወደ ሰሜን ተራራ ተጓዙ፡፡ ተጓዦችም እየበረከቱ መጡ፡፡ ከሚያገኙት መንደር ሁሉ የሚጨመር ተጓዥ አለ፡፡

"ቆይ…. ወደየት እየተጓዝን ነው?" አለች ሲጻራ አንድ ትልቅ ዋርካ ሥር ለእረፍት እንደተቀመጡ፡፡

"ወደ ተቀደሰችዋ ምድር" አሉ አባ ፊንሐስ የሰሜንን ተራራ እንጋጠው እያዩ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያናግሯት ነው፡፡

"ማን ናት የተቀደሰችዋ ምድር?" እሷም በላዩ ላይ ባዘቶ የመሰለ ጉም የሸፈነውን የራስ ዳሽንን ተራራ አሻቅባ እያየች አባፊንሐስን መልሳ ጠየቀቻቸው።

"የተቀደሰችዋ ምድርማ እግዚያብሔር ለአባቶቻችን ቃል ኪዳን የገባላቸው እስራኤል ናት- ኢየሩሳሌም"አሏት:: ስለ ኢየሩሳሌም ታውቃለች። በመፅሐፍ ቅዱስ።

አባ ማቴዎስ ፊንጠር ብሎ ከሚገኘው ጉብታ ላይ አርባጣ አፈር እየቆፈሩ ከማህደራቸው ሲከቱ ሌሎች ከሩቅ ይሳሳቀባቸዋል።

አባ ፊንሐስ.....ቀጠሉ...እየተልጎመጎሙ...እተቁነጠነጡ..."አየሽ ልጄ ሲጳራ.... አንቺ የማታውቂው ብዙ ነገር አለ። በመጀመሪያ ...አባትሽ እኔ መሆኔን ልነግርሽ እወዳለሁ።"

ካቀረቀረችበት ቀና አለች ግራ ተጋብታ። "ምን?!" ቅንድቧን በጥያቄ መልክ ሸብሽባ።

"አዎ ልጄ። ወደ ሴቶች ገዳም ያስገባሁሽ ወድጄ አይደለም። ደኽየሁ። እናትሽንም ሞት ነጠቀኝ። አዝዬሽ በልመና ላሳድግሽ ተንከራተትኩ" የለበሱትን ወይባ አቡጀዴ ሰብስበው ግራ እጃቸውን ገልጠው አሳዩአት። ክንዳቸው በጥይት ተቦትርፎ በተለበለበ ግንድ መስሏል። "እዩውልሽ ልጄ። እኔ አባ ዠንበሩና አባ ዲዲሞስ አንድ የጋራ ጉዳይ ስላለን..... ተይው ይህን ሌላ ቀን ነው የምነግርሽ። ጣና ሐይቅ ላይ በጣሊያን ጊዜ የመርከብ..... ለካ ሌላ ቀን እነግርሻለሁ ብያለሁ። አሁን አይደለም።»

ሚራዥ ካሰረላት በ"ቶ" ቅርፅ ከተሰራው ባለ ጉጥ መስቀል ላይ አይናቸውን አልነቀሉም። ለምን ይህን ያህል ገዜ አፍጥጠው እንደሚያዩት ግን አልገባትም። ባለፈው እንድትሰጣቸው ጠይቀዋት እምቢ ብላቸው ነበር።

«እየውልሽ ልጄ....» አገጫቸውን አሹለው ወደ ሰሜን ተራራዎ ሲያዩ እሷም ተራራዎችን ተመለከተቻቸው። "ከምታይው ተራራ ግርጌ ነበር እኔና እናትሽ በአንጥረኝነትና ብረት በመቀጥቀጥ ስንተዳደር የነበር። ማረሻ ሸጠን የምናገኘው ገቢ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ሆኖም ተስፋ ያስቆረጠኝ የምወዳት እናትሽ አንቺንና እኔን ጥላ ስትሞትብኝ ነበር። እዚህ አስቸጋሪ ቦታ ላይ አንቺን ማሳደግ ተሳነኝ። ቤተ እስራኤላዊና የአይሁድ እምነት ተከታይ ብሆንም ቀን እስኪወጣ ብዬ እምነቴን በልቤ እንደያዝኩ አንቺን ላሳድግ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ገባሁ። አንቺን በእንጦንስ ደሴት ለሴቶች ገዳም ሰጥቼ እኔ ደሞ በዳጋ እስጢፋኖስ የወንዶች ገዳም ውስጥ መኖር ጀመርኩ። አሁን ግን ዘመዶቻችን ሊወስዱን መጡ።"

ከተንዥች መሃል በአህያ ላይ ተጭኖ የሚጓዘውንና ፊቱን በጥቁር የዋልካ ጭቃ ቀብቶ ከሐበሻ ጥቁር አይሁዶች ጋር የተመሳሰለውን ፈረንጅ እያሳዩአት።



ፊቱን በዋልካ ጭቃ የተለቀለቀው ፈረንጅ ፎቶ ያነሳል፤ ቪዲዮ ይቀርፃል፤ አባ ፊንሐስንም ቃለ መጠይቅ አድርጎ ቃላቸውን በቴፕ ሲቀርፅና ፎቶም ሲያነሳቸው አይታ ነበር። እሱዋንም ትኩር ብሎ ይመለከታታል። ዓይኑዋን ካልሰበረች ዓይኑን አይሰብርም። ከሁዋላ ስትቀር ወደሁዋላ ይዞራል። ከፊት ስታልፍ እየገሰገሰ ይደርስባታል።

"...ይሄ ነው ዘመዳችን?.... .ነጩ ሰውዬ? .....እንዴት ሆኖ?" ግራ ገባት። "እነማን ናቸው ዘመዶቻችን?" ራሱን ተላጭቶ ፊቱን የዋልካ ጭቃ ተለቅልቆ ከሽማግሌዎች ጋር ቆሞ የሚነጋገረውን ወዘ ልውጥ እያየች።

"እስራኤላውያን ናቸው ወገኖቻችን። ከዚህ የመከራ ኑሮ ሊያላቅቁን መጥተዋል። አንገታችን ደፍተን፣ አፈር ለብሰን ነበር። አሁን ግን ደረሱልን። እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ወደገባላቸው ማርና ወተት ወደምታፈሰው ከነአን ሊወስዱን መጡ" ልቧን አማለው ሚራዥራን ሊያስረሷት መስሏቸው ነበር። የእሷ ልብ ግን ከሚራዥ ጋር እንደተቀራኘ ነበር።

"እና ምነ ሚራዥ አብሮን ቢሄድ? ለምን ጥላችሁብኝ መጣችሁ? አባ... እሱን እኮ አሁን እያሰቃዩት ነው የሚሆን! ክህነቱን ቃፈረሰ ይመስላቸዋል እኮ!...... ግን ምንም አላደረግንም አባ.... እባክዎ ሂደን እናምጣው?" ዓይናቸው ላይ እየተቁለጨለጨች ተማፀነቻቸው።

"ይሄማ የማይሆን ነገር ነው። እየውልሽ ልጄ የማታውቂው ይህንን ነው። እኛ ቤተ እስራኤላውያን ነን። የእግዚያብሔር ህዝቦች ። በእግዚያብሔር የተመረጠውን ዘር ከሌላ ዘር እንደባልቅም።"

"እንዴ! ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አግብቶ የለ? እኤስ ለምን......" አቋረጧት።

"እነዚህ የሚወስዱን ሰዎች ሁሉን ነገር አጥንተው ጨርሰዋል። እስራኤላዊ ያልሆነን ማንንም አይወስዱም" አሉ ወደ ጠጉረ ልውጡ ሰውዬ እያማተሩ።

"እኔ ግን እሱን ትቼ ንቅንቅ አልልም" አለች ወደ መጣችበት አቅጣጫ ፊቷን አዙራ። አልመለሱላትም። ሦእረፍት ሰዓት ሰላቢቃ ሁሉም ጓዙን እየጠቀለለ ተነሳ። በቀኝ እጃቸው እጇን ይዘው እየጎተቱ ከሚጥመለመለው ተጓዥ ጋር ተደባለቁ።

ከትከሻቸው ዱላ ቅል ቃንቁራቸውን ሰካክተው ያንጠለጠሉ፣ ማረሻ ማጭድ፣ ጉራዴ፣ ሰይፍ፣ ጦር፣ አንካሴ፣ መቆፈሪያ፣ መጥረቢያ፣ አካፋ፣ ዶማ እና ሌሎችም ዝከንትሎችን አንጠልጥለው ይጓዛሉ። ከወዘ ልውጡ ሰውዬ ጋር በእብራይስጥ ቋንቋ ከሚነጋገሩት ሽማግሌዎች ጋር ህፃናት፣ ጓዝ የተጫኑና በድርቁ

የሚቀምሱት አጥተው በአጥንታቸው የሚሄዱ አህዮች ይጋፋሉ። ይጓዛሉ።

ከጎንደርና አካባቢዋ፣ ከወለቃ፣ ከሩፋኤል፣ ከሲልቀት፣ ከጎርጎራ፣ ከጭልጋ፣ ከቋራ፣ ከጃኖራ፣ ከእንክኮሻሸሊት፣ ከአርማጭሆ፣ ከብልባሆ፣ ከጠዳ፣ ከደንቀዝ እየመጡ ጉዞውን ተቀላቀሉ። ከወገራ አውራጃ ዳግሞ ከዳባት፣ ከሰላምጌ፣ ከጉራሬ፣ ከዋርዋ፣ ከብራ ኢየሱስ፣ ከአምባ ጊዮርጊስ፣ ከደርጋጅ፣ ከጫርቢጣ እየመጡ ተደባለቁ። ሲደባለቁ የሚያወጡት አንድ ቃል ብቻ ነው። «ሻሎም።»

ከጎጃም ደግሞ ከባህር ዳር፣ ከቡሬ፣ ከደብረማርቆስ፣ ከዲማ፣ ከይስማላ ጎዮርጊስ፣ ከአዴት፣ ከዱር ቤቴ፣ ከቁንዝላ፣ ከግብግቢት ቀድመው ደርሰዋል። ከበጌ ምድርም ከወረታ፣ ከሐሙሲት፣ ከፎገራ፣ ከደብረታቦር፣ ከአፈረዋናት፣ ከእስቴ፣ ከፋርጣ፣ ከውዶ፣ ከኩርያ ማርያም፣ ከመነጉዘር፣ ከአሞራ ገደል የመጡትም ከኋላ ደረሱባቸው። ከደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ከምእራብ ኢትዮጵያ፣ ከምስራቅ ኢትዮጵያም መጥተዋል።

ወቅቱ ኢትዮጵያ በእርስ በእርስ ጦርነት የምትታመስበት በመሆኑ ሁሉም ባተሌ ነበር። በሽምቅ ተዋጊዎች ጦር በአራቱም አቅጣጫ የሚንቦጀቦጀው የደርግ መንግስት በጦርነት በመማገዱና የሚይዝ የሚጨብጠውን በማጣቱ ቤተ እስራኤላውያኑን ወደ እስራኤል ለማጓጓዝ «ዘመቻ ሙሴ» ለተሰኘው የእስራኤል ኦፐሬሽን ተፈፃሚነት አመቺ ወቅት ነበር። በሱዳን በኩል ሰርገው ለገቡትና ለዓመታት ለሰለጠኑት የእስራኤል ሰላዮችም ወርቃማ ጊዜ ነበር።

ቤተ እስራኤላዊያን በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜን ምዕራብ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተበታትነው ሲኖሩ ለሁለት ምዕት አመታት ያህል ወደ እስራኤል ለመመለስ ምኞት የነበራቸው ቢሆንም ይሁዲ መሆናቸው የተረጋገጠው ከረጅም ጥናት በሁዋላ "ፈላሻዎች በማያጠራጥር ሁኔታ የዳን ነገዶች ናቸው" ተብሎ በመታወጁና ይህም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዛሬው ደቡባዊ የአረቢያ ልሳነ ምድር ይኖሩ እንደነበር ተረጋግጧል በመባሉ ነው።

የእስራኤሉ የስለላ ድርጅት ሞሳድ ፈላሻዎችን ከኢትዮጵያ በምስጢር ለማስኮብለል የተሳካለት ወቅትም ኢትዮጵያ በጦርነት ውዥንብር ውስጥ በገባችበት ወቅት ነበር። ፈላሻዎችን የማጓጓዙ ተግባር በቀጠለበት በዚህ ወቅትም የወቅቱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስተር ሺሞን ፔሬዝ "ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከኢትዮጵያ በደህና ወደ ሀገራቸው እስኪመለሱ ድረስ ዕረፍት አይኖረንም" ያሉት የረሃብተኛ ፈላሻዎች ሁኔታ በተባባሰበት በነፋሻማው የፀደይ ወቅት ነበር።



ጉዞው ቀጥሏል ። ጥምልምሉ። በኋላ ጉዞው ከቀን ወደ ሌሊት ተዛወረ። በእውራ ጎዳናዎች የሚነጉደውን ረጅም ተጓዥ በመቆራረጥ በየጥሻው በድብቅ ማስጓዝ ነበር አዋጭ ሆኖ የተገኘው።

ሲጻራ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገችውን ረጅም ጉዞ መቋቋም አልቻለችም። ጭብጥ ከምታህል ድንክየ ደሴት ነው ያደገችው። ልቧን እስኪደክማት እንኳ ሮጣ አታውቅም። በጣና ሐይቅ ላይ ግን ልቧን እስኪደክማት ዋኝታ ታውቃለች። አሁን ደም የባሰ ልቧ ወደኋላ በፍቅር ገመድ እየተጎተተ ነው። በአካል ተገዳ ብትጓዝም በመንፈሷ ከሚራዥ ጋር ቀርታለች። እግሮቿ ደም በደም ሆነዋል። የጭኗ ጠባብቅ ተገሽላልጧል። ከንፈሮቿ ተቆራርሰዋል። ውበቷ ጠውልጓል። ከአያሌ ቀናት ጉዞ በኋላ የደባርቅን ከተማ አለፉ። ከጎንደር ከተማ በኋላ ከመቶ ሀላሣ ሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘዋል። ወደተራራው አንጋጣ አስገራሚውን ትርኢት ጨለፈችው።

የሾሉ ተራሮች.... የምድር ቀንዶች መስለው ቆመዋል። ተፈጥሮ በአለቶች ላይ ያነፀቻቸው እነዚህ ተራሮች ቆመው እንደጅረት የሚፈሰውን ትውልድ ይታዘባሉ። በተራሮች ጫፍ ላይ አስገራሚው ትርዒት ይታያል....ቲያትር። የሚደባደቡ ዝንጀሮዎች። የሚባዝኑ ወፎች። የሚያላዝኑ ቀበሮዎች። ከረጃጅም አለቶች ላይ ፈልቀው በአለቶች ላይ በቀጭኑ ብትን ብለው ለሚወርዱት ፏፏቴዎች ከሁሉም ተራራዎች በላይ ሰማዩን እየቡዋጠጠ የተኮፈሰው ራስ ዳሽን ተራራ ይቀኝላቸዋል።

ሲጻራ ራስዳሽንን ወደላይ አንጋጣ አይታ ጫፉ ላይ እግዚአብሔር የተቀመጠበት መሰላት። በራስ ዳሽን እናት ላይ የሚጥመለመለው ዳመናና ጉም የጠመጠመ የቅኔ መርጌታ አስመስሎታል። መርጌታ ራስዳሽን ወደ ሰማይ ተጠግቶ ለእግዚአብሔር በጆሮው ይቀኝለታል። መወድሱን ያወርድለታል። እግዚአብሔርም ለመርጌታ ራስ ዳሽን የደመና ጥምጣም የደመና ኩታ ይሸልመዋል። ከተራሮች ሁሉ መርጦ ራስ ዳሽንን እድሚ ስላደለው የበረዶ ሽበት ጣል ጣል አድርጎበታል-ከደመና ጥምጣሙ ሥር። ራስ ዳሽንን ያዩ ጤና ያጣ ካልሆነ በቀር ተራራ ነው አይልም። ግዑዝ የድንጋዮችና የአለቶች ጥርቅም አይመስለውም። ነገር ያረገዘ ህያው አካል ይመስላል እንጂ። የሰሜን ተራሮች ከስሩ ጉባዔ ቃና እየተቀኙ በያሬድ ዜማ ያሸበሽቡለታል። ራስ ዳሽን ከላይ ተኮፍሶ ያዳምጣቸዋል።

በዘጠኝ ሺህ ጫማ ከፍታ ቁመቱ ልክ ቆሞ ሰማዩን ይጠባል - ራስ ዳሽን። ይንን ተራራ ቤተ እስራኤላውያን ሙጭጭ ያሉበት ምክንያት ግልፅ ነው። በንጉስ ሀብታህ ዘመን ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በ2300 ዓመተ ዓለም አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ

እንደገቡ የሚነገርላቸው ቤተእስራኤውያን የአገሩን ውበትና አቀማመጡን አይተው በጣም ስለተደሰቱ ታማኝና ታዛዥ ዜጎች ሆነው በዚህ ተራራ ላይ ለመኖር፡፡ ንጉሡን ጠይቀው በመጀመሪያ ቢያቅማማም ብርዳማና ተራራማ ከሆነው ክፍል መሬት እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት በራስ ዳሸንና በቅርቡ ከሚገኙት ተራራማ ሥፍራዎች መሬት ተሰጣቸውና መኖር ጀመሩ፡፡ አንዳንዶቹ በቀዝቃዛው አየር ምክንያት ቢሞቱም የቀሩት ግን ተራራውን ተጣብቀው ብርዱን ተቋቁመው ኖሩ፡፡

ተራራውንም በልዩ ልዩ ሥም ይጠሩት ነበር፡፡ ሰሜን፣ አሜርጋ፣ አምባራስ፣ አቤር እያሉ፡፡ አቤር ማለት እምላካዊ በር ማለት ነው፡፡ ተራራውን ለስግደትም ይጠቀሙበት ስለበር ነው፡፡ በዘመነ አሪት በየዓመቱ ምዕመናኑ ተራራ ላይ ወጥተው መፀለይ ልማዳቸው ሥለ ነበር፡፡

የሰሜን ተራራ ለቤተ እስራኤላውያን ብዙ ጠቀሜታ የነበረው ሥፍራ ነበር፡፡ ተራራው ላይ ወጥቶ በዙሪያው ያለውን ምድር ቁልጭ አድርጎ በአራቱም ማዕዘን ያሉትን ቦታዎች ያሳያል፡፡ ታላቅ ከፍታ ያለውና ለውጊያም አመቺ በመሆኑ ይህንን ተራራ መመኘታቸው ለምን እንደነበር መገመት ቀላል ነው፡፡ ብዙ ጦርነቶችን ድል አድርገውበታል፡፡ የጠላት ኃይል ሲያይልባቸው ከዋሻዎቹ ውስጥ ገብተው እየተደበቁ ያመልጡ ነበር፡፡ በኋላም ራሳቸውን ያደራጁና ከዋሻው ወጥተው አለት ደንጊያ እያንከባለሉ ጠላቶቻቸውን ያጠቁ ነበር፡፡

"የኩሽ ልጅ ሬሙስ፣ዩዳ እና ሳቢሳ የተባሉ ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩት" ይላሉ ወግ ነጋሪ የቤተ እስራኤላውያን ሽማግሌዎች፡፡ "ዩዳ በኢትዮጵያ ያለነው ቤተ እስራኤላውያን አባት ነው" ይላሉ ደክሟቸው ጥላ ሥር ሲያርፉ፡፡ ሲጻራም ታዳምጣለች፡፡ ከየትም ይምጡ ከዩት ግድ የላትም፡፡ አንድ ልቧ ወደኋላ ቀርቷል፡፡ ሌላኛው ልቧ በሰሜን ተራሮች አናት ላይ ተመስጎ የራስ ዳሸንን የተፈጥሮ ትርዒት አብሮ ይተውናል፡፡

ከተራሮች ወረድ ብለው ከተበታተኑት መንደሮች ደረሱ፡፡ የከብት በረቶችና የእርሻ ማሳዎች በኮሳሳ ጎጆዎች ዙሪያ ይታያሉ ፡፡ መንደሩ ውስጥ ከየሳር ቤቶች አናት ላይ የዳዊት ኮከብ ምስል ተሰቅሎ ተመልክታ ግራ ተጋባች፡፡

ከነዚህ የፈላሻ መንደሮች የጎበጡ አሮጊቶች፣ በረሃብ የጠወለጉ ህፃናትና ሽማግሌዎች እየወጡ "ሻሎም" እያሉ ተጥመልምለው የመጣውን ነገደ ፈላሻ ዝዙን እየተቀበሉ እግሩን እያጠቡ ተቀበሉት፡፡ ተጓዡ የደረሰው ከመሸ ነበር፡፡ በወናፍ የከሰሉን እሳት ግልጥጥ የሚያደርጉት አንጥሮኞችና ቀጥቃጮች የጀመሩትን



ማረሻና ጎራዴ ሠርተው ለመጨረስ ፍም የመሰለውን ብረት በመዶሻ በህብረት ይቀጠቅጣሉ፡፡ በጉዞ ወቅት ሽጠው ለመጠቀም፡፡

አባ ፊንሐስ የሲጻራን እጅ እየጎተቱ የዳዊት ኮከብ ምልክት ካላበት ምኩራብ ውስጥ ይዘዋት ገቡ፡፡ ቆባቸውን አውልቀው ከምኩራቡ በር ላይ ካለው የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሲጨምሩት በድንጋጤ ደነዘዘች፡፡ አንገቷ ላይ ዓይናቸውን አሳርፈው ማተቧንና ያሰረችውን ባለጉጥ መስቀል ሊያወልቁ እጃቸውን ሲሰዱ ማተቧንና ሚራዥ የሠጣትን መስቀል ጨምድዳ "እንዴ! እረ በስመ አብ ይበሉ! .......ማተቤን?" አለች ክው ብላ፡፡

"ከአሁን በኋላ አያስፈልግሽም፡፡"

"እንዴት ነው የማያስፈልገኝ? መስቀሉን ደግሞ ይልቀቁት ሚራዥ የሰጠኝ ነው፡፡ .......ይልቀቁት፡፡ እርስዎ ሰጥተውኛል? ...."

"እዚህ ቦታ ላይ አያስፈልግም አልኩሽ፡፡ ከአሁን በኋላ አያስፈልግሽም፡፡ ከ'..ሁን በኋላ የአባቶቻችን አምላክ ታመልኪያለሽ፡፡"

"ሊያሰልሙኝ ነው?"

"አይደለም ልጄ፡፡ የእስራኤልን አምላክ አዶናይን እንድታመልኪ ነው፡፡ ከአሁን በኋላ አይሁድ ነሽ፡፡ የዳዊት ዘር! የነአብርሃምን የነያዕቆብን አምላክ ታመልኪያለሽ፡፡"

"እኔም እኮ የማመልከው እሱን ነው፡፡ ሰይፍ በአንገቴ ቢያልፍ ተዋህዶ እምነቴን አልክድም፡፡ ማተቤን አልፈታም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን አልክድም፡፡ እርስዎ አላሳደጉኝም፡፡ ኢየሱስ አባቴ ማርያም እናቴ ሆነው ነው ያሳደጉኝ፡፡" እንባዋ መጣ፡፡

"ባላሳድግሽም ወልጄሻለሁ፡፡ አባትሽ እኮ ነኝ ልጄ፡፡ እንዴት ልጄን እንድትሳሳች እመክርሻለሁ?" አሏት ቆባቸው የኖረበትን ነጭ ሽበታቸው ዳር ዳር የዞረበትን መላጣቸውን እያሹ፡፡

ማተቧን ጥብቅ አርጋ ይዛ ሲከራከሩ፡፡ አይሁዶች የሚደፏትን ትንሽ ብጣቂ ቆብ እናታቸው ላይ ጣል ያደረጉ ሽማግሌ የአይሁድ ካህን የምሽቱን ጸሎት በእብራይስጥ ቋንቋ ማሰማት ሲጀምሩ ሁሉም መድረኩ ላይ ወደ ቆሙት ካህን አማተሩ፡፡ ፀጥታ ሰፍኖ የእሳቸው ድምጽ ብቻ ማስገምገም ጀመረ፡፡

የምሽቱ ፀሎት ዘወትር ማታ ማታ ፀሐይ በምትጠልቅበት ሰዓት የሚያደርሱት ፀሎት ነው፡፡ ሽማግሌው ካህን በሚርገበገብ ድምፃቸው ጸሎቱን ጀመሩ፡፡ "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል፣ አምላክ ያዕቆብ፣ አምላክ ሙሴ ወዓሮን፣ አምላክ ዳዊት ወሰሎሞን፡፡ በሠርክ ወበነግህ በኩሉ ጊዜ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘነብረ ግቢየ ወመንክረ በህቲቱ ቅዱስ፡፡ ወደምላዕ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ኩሉ ዓለመ፡፡ ይትባረክ ወይትቀደስ ስመ ስብሐቲሁ፡፡ ቅዱስ ኃያል ወቡሩክ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም አለም፡፡

አሜን" እስከዚህ ያለው ፀሎት ግዕዝ ስለሚመስል ገባት። "አምላካችን የተባረከ ነው። የአብርሃም አምላክ፣ የዳዊትና የሰሎሞን አምላክ። ለአምክ ምስጋና ይሁን ዘወትር፤ ጠዋትም ማታም። ታላላቅና አስደናቂ ነገሮችን ሰርቷል። ብቻውን። ቅዱስ እሱ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ታላቅነት መላውን ዓለም ይሞላዋል። ታላቅ ስሙ የተባረከና የተቀደሰ ነው። እርሱ ቅዱስ ነው። ታላቅ ነው። ለዘለአለሙ የተባረከ ነው።" ማለት መሆኑ ገባት።

ቀጥለው የፀለዩት ግን አልፎ አልፎ ጣል ጣል ካሉት የግዕዝ ቃላት በቀር አልሰማት አለ። "ሄርዝጋ ዲርሚጋ ሰሁንቴጋ ወሬዛ በኃይሉ ወወሬዛ በምኩናኑ እደረሽ ወሴጋ ይዝምዝ። ሰሐር ሰሀአርስጋ ንጉሥ በላዕለ ኩሉ ለሊክ ኒጋሂ ድርሚሊ ነገዛ ሰናር የደራ አዶናይ ምዜናን። አዶናይ ዘሃሎ ወይሄሉ ገርግሻው አዶናይ። ዲርማ ግርግሻው ይትአየን መልአከ እግዚአብሔር አውዶሙ ለእለ ይፈርህወ። እንኮቶን ከሽንጋው አዲሪጋው ናሁ መልአክየ የሐውር ቅዳሜየ እግዚኦ በሰማይ ሳህልከ እግዚኦ ዋው ይምጻእ ምህረትከ። እግዚኦ ሳማይሊ ሰማውሶ ኪሳሁሊ አነደገሊገመሰ ........." ሽማግሌው ካህን ትንፋሽ አጥሯቸው የሚወድቁ መሰላት። እሳቸው ያለማቋረጥ በተንተገተገ እሷን ደከማት።

ግራ ስትጋባ ያዩአት አባቷ አባ ፊንሐስ በሹክሹክታ እየተረጎሙላት ነው። "የነበረውና ያለው አዶናይ፤ታላቁ አዶናይ። ለሚፈሩት መጠጊያቸው ነው። እንደዚህም ይላል ‹ አዩት መልአኬ ከፊታችሁ ሆኖ ይመራችኋል።› ጌታ ሆይ፤ ፍቅር የተመላው ደግነትህ በሰማይ ይገኛል። አምላክ ሆይ ምህረትህ ይወርድልን ዘንድ እንማፀንሃለን። የነበርኸውና ያለኸው አዶናይ፣የአብርሃም አባት፤የይስሃቅ አባት፣ የያዕቆብ አባት፣ የእራኤል አባት፣ አባታችን፤እምነታችን በአንተ ላይ ነው። የነበርኸውና ያለኸው አዶናይ፤መላእክትህ ቀን ቀን አያርፉም፤ሌሊት ሌሊት አይተኙም።.........የእግዚአብሔር ስም ምስጢራዊ ነው፤ቃሉም የተቀደሰ ነው፤የእሱ ቃል ለነፍስ የደስታ ምንጭ ነው፤ለሥጋም መድኃኒት ነው። አምላክ እንዲህ ይላል፤ ልጄ የበኩር ልጄ እስራኤል፤ ልጄ እሱ ነው።› ....በእርግጥም እስራኤልን የፈጠርኸው ለክብር ነው። ጥሬ ሥጋ አይበላም፤የፍየል ደምም አይጠጣም.........." ካህኑ አይደክመውም። አባ ፊንሐስም ከጆሮዋ ጥግ በረጅም ጢማቸው ከተደፈነው አፋቸው ውስጥ ትርጉሙን ያፈልቁላታል። ፀሎቱን በቃላቸው ስለሚያውቁት የሰውየውን ድምፅ አያዳምጡም። አፍንጫቸውን የተያዙ ይመስል እየተነፋነፉ ነው የሚተረጉሙላት። እሷ ግን የምኩራቡን ውስጥ እየቃኘች ነው። ወዲያው ፀሎቱ አብቅቶ ሽማግሌው ንግግር አደረጉ። "የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። በቤተ እስራኤላውያን ዘንድ ቅዱስ



ከሆኑት ተራሮች የመጣችሁ ከዳሽን ቅዱስ ተራራ፣ ከምድራሮ ቅዱስ ተራራ፣ ከጃኒ ፈንቃራ ቅዱስ ተራራ የመጣችሁ የእስራኤል ቅዱሳን አባቶች እንኳን ደህና መጣችሁ። ሻሎም" አሉ ሁለት እጃቸውን ከፍ አድርገው። ሁሉም ባንድ ላይ "ሻሎም።" አሉ እጆቻቸውን እንደ ካህኑ ከፍ አድርገው።

በየዓመቱ የቤተ እስራኤላውያን ካህናት ከሚፀልዩባቸው ቅዱሳን ተራራዎች የመጡት ሽማግሌዎች በተለይ የተቀደሰችዋን ምድር ከነአንን በአይናቸው ሲያዩ ጊዜው በመቅረቡ ተደስተዋል። በየአመቱ ቅዱሳን ተራራዎች ላይ እየወጡ ይፀልዩ ነበር። በጭልጋ አውራጃ ከሚገኘው ዳሽን ተራራ ላይ፤በደንቢያ አውራጃ ከሚገኘው ምድራሮ ተራራ ላይ፤በጎንደር አውራጃ ከሚገኘው ጃኒፈንቃራ ተራሮች ላይ እየወጡ የሙታን ዘመዶቻቸውን ስም እየጠሩ ‹‹እሚያን›› ይቆነጥሩላቸዋል። ‹‹እሚያን›› ማለት በልብሳቸው ጫፍ የሚቋጥሩት ትንሽ ጥሬ ጤፍ ነው። እሚያኑን ቆንጥረው አለት ላይ ይበትኑታል። ይህን ሲያደርጉ የሙታኑ ነፍሳት ዕረፍት ያገኛሉ ብለው ያምናሉ። ስለዚህም ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የሚቆነጥሩት እሚያን ጤፍ ይዘዋል።

ሲጻራ የምኩራቡን ውስጣዊ ዝባዝንኬ በዓይኗ ትዳስሳለች። ምኩራቡ ከእስራኤል በመጡ ትርኪ ምርኪ ቁሳቁሶች ተሞልቶአል። ከቴልአቪቭ የመጣው ‹‹ቶራ›› የተባለው የእብራውያን ቅዱስ መፅሐፍ ከጥግ ካለው ሰፊ አትሮንስ ላይ ተቀምጧል። የዳዊት ኮከብ ምስል የተቀረፀባቸው ሽክላዎችና የጌጥ እቃዎች ዙሪያውን ተሽኮትኩተዋል ።

የፀሎቱ ጊዜ አብቅቶ ሁሉም ያለውን ተቃምሶ አጥንት ሰብሮ የሚገባው የዳሽን ብርድ እያንዘፈዘፈው ግማሹ ከውጭ ቦታ ያገኘውም ቤት ውስጥ በየወለሉ ላይና በየመደቡ ተኮራምቶ ተኛ።

ሲጻራ ከአባ ፊንሐስና አብረዋቸው ጀልባውን ሲነዱ ከነበሩት ከአባ ማቴዎስ መሃል ተኛች። እንቅልፍ ሲጥላቸው እንዳታመልጥ አንድ እጇ በገመድ ከግንድ ጋር ታስሯል። እኩለ ሌሊት አካባቢ ከጭኖቿ መሃል ቅዝቃዜ ተሰማት። "የፈጣሪ ያለህ!" አለች። የወር አበባዋ ነው። ትንሽ ገድቦ የሚያስቀርላት የውስጥ ሱሪ እንኳ አልለበሰችም። በርግጥ የውስጥ ሱሪ ለብሳ አታውቅም። የለበሰችው ከላይ እስከታች የተንቦረሰሰ የወይባ አቡጀዲ ቀሚስ ነው። ወገቡዋ ላይ ብቻ ሰፊቀበቶ የሚመስል ቅናት የሚባለውን የገዳማውያኑን መታጠቂያ ታጥቃለች። እማሆይ ወለተ ኪሮስ የወር አበባዋ ሲመጣ የምትጠቀመውን ዘዴ አስተምረዋት ነበር። ነገር ግን ጉዝጉዝዋ ውስጥ የደም ጨርቅ ስላልያዘች ዘዴውን ለመጠቀም አልቻለችም። የነበራት ብቸኛ አማራጭ ማልቀስ ነው። ማነፍረቅ።

ጠዋት በሰሜን ተራሮች ጫፍ ፀሐይ እግሯን ስትሰድ ሳትረግማት አልቀረችም፡፡ ቀሚሷ በደም ተዘፍዝፏል፡፡ የተኛችበት ምድር ተከፍቶ ቢውጣት መርጣ ነበር፡፡

አባፊንሐስ ተነስተው ልጃቸው ላይ ሲያማትሩ በድንጋጤ ታቅፈው አነሷትና እጇን ፈትተው በቅርብ ወደሚገኘው ወንዝ ይዘዋት ወረዱ፡፡ ወንዙ ውስጥ እስከልብሷ ገብታ ልብሷን ሳይዋ ላይ አጥባ ብትወጣም ከጥቂት ቆይታ በኋላ መልሶ ተጨማለቀ፡፡

ማታ የምሽት ፀሎቱን የመሩት ሽማግሌ የአይሁድ ካህን እየተጣደፉ መጡና በቁጣ "እንዴት የአባቶቻችንን ሥርዓት ትጥሳላችሁ? እንዴትስ ሰባት ቀን ሳይሞላት የመንፃት ሥርዓት ታደርጋላችሁ፡፡ እናንተ ቤተ እስራኤላውያን ነን አላላችሁም? ከሆናችሁ እንዴት የመርገም ጎጆ ያለበትን አትጠይቁነም......" ሊገባት አልቻለም፡፡

"በይ ተነሺ!......."

ወደ አንዲት ከመንደሩ ርቃ ወዳለች ደሳሳ ጎጆ ቤት ይዘዋት ሄዱና "ግቢ! ከሰባት ቀን በኋላ የመንፃት ሥርዓት ይደረግልሻል" ብለዋት ጎጆዋን ከውጭ ዘግተውባት ወደመጡበት መንደር ተመለሱ፡፡

አባ ፊንሐስም ከጎጆዋ በር ላይ ተቀምጠው አቀርቅረው ከቆዩ በኋላ ወደ ወንዙ ወርደው በመታጠብ የመንፃት ሥርዓት አደረጉ፡፡ መርገሟ የመጣባትን ሴት ስለነኩ፡፡

እምነቱን አጅግ አጥባቂ የሆነው ቤተ እስራኤላዊ አይሁድ ገበያ ወጥቶ ሲመለስ እንኳ ከቤቱ ከመግባቱ በፊት ወንዝ ወርዶ ታጥቦ መንፃት አለበት፡፡ የቤተ እስራኤላውያን ወገን የሆነ ሰው ከክርስቲያኖች ወይም ከሙስሊሞች ጋር እህል አብሮ ቢቀምስ ወይም አብሮ ከጠጣ በድርጊቱ ተፀፅቶ ንስሐ ገብቶ ለተወሰነ ጊዜ የመንፃት ሥርዓት ካልፈፀመ በስተቀር ወደ ቤተ እስራኤላውያን የስግደት ቦታ እንዳይገባ ይከላከላል፡፡ የመንፃቱን ሥርዓት የሚፈፅም ሰው ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠመ ለሰባት ቀናት መፆም አለበት፡፡ የፆሙ ጊዜ ሲያበቃ የንሥሐ ፀሎት ከዳዊት መዝሙር ተደግሞ ፀጉሩን ተላጭቶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት፡፡

አባ ፊንሐስም ከማህደራቸው የዳዊትን የመዝሙር መፅሐፍ አውጥተው ‹ተሰአለኒ እግዚኦ› የሚለውን ደግመው ከወንዙ ውሃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ካሉ በኋላ የመንፃት ሥርዓቱን ፈፅመው ወጡ፡፡

ሲጻራ አንዲት ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ቤተ እስራኤላዊት ልጃገረድ የወር አበባዋ በሚታያት ጊዜ እንደምታደርገው ለሰባት ቀናት ከመርገሟ ጎጆ ከሰነበተች በኋላ ወደ ወንዝ ወርዳ ሰባት ጊዜ ወንዙ ውስጥ ጠልማ ወጣች፡፡ በዚህ አላበቃችም፡፡ የፀሐይ



መጥለቂያ ሰዓት ደርሶ ጭልምልም እስከሚል እዚያው መዋል ነበረባት፡፡

በዚህ ጥብቅ ሥርዓት ውስጥ እንዴት መኖር እንደምትችል ግራ ገብቷታል፡፡ ለሁሉም ነገር የመንፃት ሥርዓት አይቀሬ ነው፡፡ ከቤተ እስራኤላውያን አንዱ ገበያ ወጥቶ የቤተ እስራኤላውያን ወገን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ሲገበያይ ቢነካካ ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት ወንዝ ወርዶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት፡፡ በገበያው ውስጥ የተጠቀመባቸውን ቁሳቁሶች፤አቁማዳ፣መጫኛ፤ አጎዛ፣ ጀንዲ፣ ቁርበት እንኳ ማጠብ አለበት፡፡

ሲጻራ ወንድ ልጅም ብትሆን ኖሮ የመንፃቱ ሥርዓት አይቀርላትም ነበር፡፡ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሌሊት በህልሙ ከብልቱ ነባዘር ቢፈስበት ማለዳ ሲነሳ የተኛበትን ምንጣፍና የለበሰውን ልብስ ጠቅልሎ ወንዝ ወርዶ ማጠብ አለበት፡፡ ይህ በሚደርስበት ጊዜ በቋራኛ ቋንቋ "ሰርክ ተነካ" ይባላል፡፡ ሰውነቱንም ወንዝ ውስጥ በመጥለም ማንፃት አለበት፡፡ እድሜው ሃያ አመት ሲሞላም ሚስት ማግባት ግዴታው ነው፡፡ ከሚስቱ ጋር ሌሊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈፀሙም በበነጋታው ከሚስቱ ጋር ወንዝ ወርደው ሁለቱም ተጣጥበው መንፃት አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ እስራኤላውያን ይህን ሥርዓታቸውን ከቅድመ አሪት ጀምረው ጠብቀው የኖሩበትን ምድር ለቀው ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ በአውራ ጣታቸው ከቆሙ ሰነበቱ፡፡ እስራኤል ሀገር ውስጥ ካላቸው የምኩራብ ቁጥር በላይ ምኩራቦች የሰሩባትን ምድር ኢትዮጵያን ለቀው ለመሄድ ከመላው ኢትዮጵያ ተጠራርተው ነቅለው ወጥተዋል፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከቀናት በኋላ ጉዞው ተጀመረ.....................ወደ ሱዳን፡፡ ተጓዦቹ ጓዛቸውን በአህያና በትከሻቸው ጭነዋል፡፡ በማዳበሪያና በአቁማዳ፣ በስልቻና በሸክላ ራሳቸው ላይ አቁረው የበረሃውን ጉዞ ተያያዙት፡፡

ሱዳን በረሃ ከመድረሳቸው ብዙዎች ህፃናትና አዛውንቶች የበረሃ ሲሳይ ሆኑ፡፡ በረሃብና በውሃ ጥም እየተሰቃዩ አለቁ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ያሳደጉን መሬት ይብላን ብለው ወደ ነበሩበት ተመለሱ፡፡

በእባብና በጊንጥ እየተነደፉ በሱዳን በረሃ ውስጥ የወደቁትም ብዙ ናቸው፡፡ ሲጻራ በዚህ ጉዞ ያየችውን ስቃይ ገሃነም ውስጥ ብትገባ እንኳ የምታገኘው አልመሰላትም፡፡ ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ ለመድረስ ከሁለት ወራት በላይ አስቸጋሪና አድካሚ የእግር ጉዞ አደረገች፡፡

ከሱዳን የስደተኞች መጠለያ ለመድረስ ሁለት ማይልስ ርቀት ሲቀራቸው ደግሞ አባ ፊንሐስ በእባብ ተነድፈው ወደቁ፡፡ የእባቡ መርዝ በሰውነታቸው ለመሰራጨት አፍታ አልፈጀበትም፡፡ አባ ማቴዎስ የዕባቡን መርዝ የሚያረክስ መድሃኒት የሚቀመሙባቸው እፅዋቶችን ፍለጋ ቢንከራተቱም ዝቅ ሲሉ አሸዋ ቀና ሲሉ የሚያቃጥል ሰማይ በሚታይበት የሱዳን በረሀ ውስጥ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

አባ ፊንሐስ በጣረ ሞት እየተንዘፈዘፉ ሲጻራ ያሰረችውን ባለጉጥ መስቀል ጨምድደው ይዘው «ል....ጄ እ....አሁን ወደሁዋላ እንዳትመለሽ ከጊዜ በሁዋላ ግን በዚህ መስቀል.........» ያሉት ሳይገባት ሁሉ ነገር ተጠናቀቀ፡፡ ሲጻራ ስቅስቅ ብላ እንድታለቅስ ያደረጋት አባትነታቸው ሳይሆን ከስደተኞች ጣቢያ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው በመሞታቸው ነበር፡፡ ግን አንድ የተናገሯት ቃል በጆሮዋ ደጋግሞ አቃጨለባት፡፡ "ወደኋላ እንዳትመለሽ!!......ወደኋላ እንዳትመለሽ............."

"እምን! ከእንግዴህማ ልመለስ ብልስ በየት ብየ እመለሳለሁ? በቃ ይሄበህይወቴ ሊያጋጥመኝ የታቀደ ነገር ነው፡፡" አለች በልቧ፡፡ "ወደ ኋላ አልመለስም፡፡"

እለቱ ዕለተ ሰንበት በመሆኑ አባ ፊንሐስ አልተቀበሩም፡፡ በአይሁዳውያን ሥርዓት መሠረት በዕለተ ሰንበት፣ በቅዳሜ ቀን የሞተ ሰው አይቀበርም፡፡ የተቀበሩት በነጋታው ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ አቅራቢያ ባለ አሸዋማ ቦታነው፡፡ እንደ ትክክለኛው የአይሁድ ሥርዓት ከሆነ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ጥቁር አይሁድ ሥርዓት የአባፊንሐስ የመቃብር ጉድጓድ አራት ማዕዘን ተደርጎ በአምስት ሜትር ጥልቀት መቆፈር ነበረበት፡፡ የአስከሬኑ እራስና እግር በሚያርፍበት ወገን "መርገብ" የሚባለው ጠፍጣፋ ድንጋይም መጣል ነበረበት፡፡ ጉድጓዱ ተቆፍሮ ሲያልቅና "መርገቡ" ከሥፍራው ሲደረግ ከበላይም ከበታችም ባዶ ይሆናል፡፡ መርገቡ በሁለት በኩል በጫፍና በጫፉ ብቻ ጉድጋዱ መካከል ተይዞ ይንጠለጠላል፡፡ ይህ የሚደረገው በድንኑን የያዘው ሬሳ ሳጥንም ሆነ ሌላ መጠቅለያ መሬቷን ነክቶ እንዳያረክሳት ነው፡፡ አስከሬኑ ወደ መጨረሻ ማረፊያው ከመግባቱ በፊትም ካህናቱ መቃብሩን እያጠኑ ይኸው ‹‹ቤትህ፤ ከእንግዴህ ከዚህ መመለስ የለም›› ብለው መሰናበት ነበረባቸው፡፡ በሶስተኛውም ቀን ጠጉሯ፣ ቀንዶቿና ጥፍሮቿ ባካሏ ሁሉ ትክክል የሆነች እንከን የሌላት ቀይ ጊደር ታርዳ ደምዋና የተቆራረጠ አካሏ በወይራ ወይም በግራር ፍልጥ በሚነድ እሳት ተቃጥሎ አመዱን በአዲስ ሸክላ እቃ ካህናቱ መከፋፈል ነበረባቸው፡፡ አመዱም በውሃ ተበጥብጦ ሬሳ በነካውና በቀረበው ሰው ላይ ሁሉ መረጨት ነበረበት፡፡ የጊደሩቱ



አመድ እርኩስ ነገር የነካ ሰውን ያነፃል ተብሎ ስለሚታመን፡፡ ለአባ ፊንሐስ ግን ከዚህ ሁሉ ሥርዓት አንዱም አልተፈፀመም፡፡

ሲጻራ በዚህ የሱዳን ስደተኞች ካምፕ ከአባ ማቴዎስ ጋር እየተዘዋወረች አሰቃቂውን ጉስቁልና ተመልክታለች፡፡ በረሃብ የሞገጉት ህፃናትና አዛውንቶች አጥንታቸው ይቆጠራል፡፡ የተቦተራረፈ ጋቢ የለበሱ በሽተኞች ሞት ሞት ከሚሸቱት ከቀይ መስቀል ድንኳኖች ውስጥ እየሞቱ ይወጣሉ፡፡ ነጫጭ ጋወን የለበሱት ነጫጭ ዶክተሮች በሽተኛ የሚወጉበት መርፌ በመልእክ ሞት የተሞላ ይመስል የሚያክሙት ሁሉ እጃቸው ላይ ይሞታል፡፡

ጠኔ ካነጠፋቸው ስደተኞች መሃል አንዲት ጠና ያለች ሴት ከኢትዮጵያ ቋጥራ ያመጣቺውን አርባጫ አፈር ስትበላ ስለታየች ሌሎችም ለመካፈል ከበቧት፡፡ ሌላኛው ሽማግሌ ደግሞ ለእሚያን የቋጠሩትን ጤፍ ሲቅሙ ታዩ፡፡

ቀድሞም ምንም ስንቅ ያልያዙት አባ ማቴዎስና ሲጻራ ለመጨረሻ ጊዜ ያገኟትን ቁራሽ የበቆሎ ቂጣ ተገላገሉባት፡፡

"አባ እርስዎ ይብሏት አትበቃንም፡፡ "

"ልጄ አንቺ ብያት አትበቃንም፡፡"

"አይሆንም አባ እርስዎ ይጉረሷት፡፡"

"ልጄ እባክሽ አንቺ ብይልኝ እኔማ ባይሆን እችለዋለሁ፡፡ ብበላውም ጥፍር እንጂ ሰውነት አይሆነኝም፡፡"

ሲገላገሉ አንድ በልቶ የማያውቅ የሚመስል አጥንቱ የገጠጠ ሰው ቁራሿን ቂጣ አንስቶ ከአፉ አደረጋት፡፡

«እርፍ!» አለች ሲጻራ «ግልግል!»

አባ ማቴዎስ ወደ አንዲት የማሽላ ገንፎ ወደ ምታገነፋ ሴት ሲጻራን ይዘው ሄደው "እባክዎ ልጄ ረሃቡን አልቻለችውም" አሏት፡፡

"ታዲያ እኔ የኒሴፍ ነኝ? ለራሴ ልጄ ደሜን እየጠባ እያዩኝ፡፡ ይበሉ ወደመጡበት፡፡ ቀልደኛ ኖት?"

"ምን ተሻለኝ ልጄ?!" ተሽማቀቁ፡፡ ዙሪያ ገባውን ሲያማትሩ ቂጣዋን ከሰለቀጣት ሞጋጋ ሰውዬ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ፡፡ መልስልኝ አልለው ነገር! አሉ በሆዳቸው፡፡

"ልጄ ቆይ እስከ ነገ የሚበላ እንፈልጋለን፡፡ ብናጣ ብናጣ ተነገ ወዲያ አናጣም፡፡" ተስፋ እየሰጧት ነበር፡፡ እሷ ግን ለደቂቃ የምትቆይም አልመሰላትም፡፡ ከረሃቡ ውሃ ጥሙ ባሰባት፡፡

ትዋኝበት የነበረው የጣና ሐይቅ ትዝ አላት፡፡ እየሳቀች የምትንቦራጨቅበት ቀዝቃዛ ውሃ፡፡ በሃሳብ ሃይቁ ውስጥ መዋኘት ጀመረች፡፡ በሁለቱ መንታ ደሴቶች መሃል ስትዋኝ ታያት፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ሚራዥን አየችው፡፡ እየዋኘ መጥቶ በጨለማው ውስጥ አለቱ ላይ ተቀምጠው ጨረቃዋን እያዩ ስለፍቅር ሲዘምሩ፡፡ መቃብር ቤቱ

ውስጥ ገብተው ፍቅርን ሲጎራረሱ። መቃብር ቆፋሪዎች መጥተው ሲያስወጧቸው። አባ ፊንሐስ ከሚራኸ ለይተው ጀልባዋ ውስጥ ሲከቷት..........ወይኔ! ብላ ከሐሳቧ አለም ነቃች። ብዙ ደቂቃዎችን በሐሳቧ በመቆየቷ ረሃብና ጥሟን ረስታው ነበር።

አባ ማቴዎስ ፈገግ አሉ። ከማህደራቸው የከተቱት አርባጫ አፈር ትዝ ሲላቸው። አርባጫውን አፈር ከማህደራቸው ዘግነው እንደትበላ ለመኑዋት። «እባክሽ ልጄ ባይሆንለነፍስሽ መያዣ ይሆናል።»

ወዲያው ህፃን ልጇ የሞተባት ሴት ኡኡታዋን ስታቀልጠው ወደ ሴቷ ዞረች። ገንፎ የከለከለቻት ሴት ነበረች። ለልጇ ገንፎውን በስሱ ሳታበላው ሞተ። ጠሙን በባዶ አንጀቱ ፈጅሙን የመንገደ ሰማይ ጉዞ ያለሥንቅ ተያያዘው። ብዙም ሳይቆይ ከድንኳኖቹ ራቅ አድርገው አሸዋውን ቁፍር ቁፍር አርገው ቀበሩላት።

ሴትዮዋ ልጅዋን ቀብራ ስትመለስ ገንፎዋ ተበልቶ ጠበቃት።- "ማነው ገንፎየን የበላብኝ?!" አንባረቀች በሌለ አንጀቷ። እየተመናቀረች መጥታ ሲጻራ ላይ አፈጠጠችባት። ካንገትዋ ሥር የተገታተረው ጅማትዋ ከሩቅ ይቆጠራል።

"አንቺ ነሽ?!" አለቻት። "አሁን ልጠፍጥፍሽ?"

"አረ እኔ አይደለሁም! ማርያምን!" እመቤቴ ቅንጥስ ታርገኝ!" አለች ሲጻራ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ። አፍዋ በሙሉ ጭቃ ሆኖአል። የምታላምጠው አርባጫ አፈር በከንፈርዋ ዳርዳር ተዝረክርኮአል።

"እሽሽሽ......" አሉ አባ ማቴዎስ የሲጻራን አፍ እፍነው።

"ማርያምን አትጥሪ። አይሁድ ካልሆንሽ አይወስዱሽም"

"አይውሰዱኛ! አላበዙትም? ደግሞ እመቤቴን ማለት አልችልም? እሷን ጠልተው ማንን ሊወዱ ነው?"

"እየውልሽ.... ለእነሱ እኮ ኢየሱስ ገና አልተወለደም። እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንጂ አንድም ሦስትም ነው ብለው በስላሴ አያምኑም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከማርያም የተወለደ የእግዚያብሔር ልጅ ነው የሚለውን አይቀበሉም። ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ተሰቅሎ፤ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ፣ከሞት በተነሳ በዓርባኛው ቀን ወደ ሰማይ አረገ የሚለውን ትምህርት አይቀበሉትም፤አያምኑበትም። መሲሑ ገና ከእስራኤል ወገን እንደሚወለድ ነው የሚያምኑት። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና አይወልድም፤አይወለድም፤አይሞትም፤ይገድላል እንጂ።ብለው በፅናት ያምናሉ" አሏት አባ ማቴዎስ ሰው እንዳይሰማቸው በለሆሳሰ።

"ለእኔ ግን ኢየሱስ ተወልዶአል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳም ንዶታል። ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን መካከል ተነስቶ በአርባኛው ቀን አርጓል።..... አላዩም?!



......ይህ ሲሆን በስፍራው ያልነበረነው እኛ ስናምን ለምን እነሱ ያዩት አላመኑም?" ጥያቄዋ አይጣል ነው ድሮም።

"...‹ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው › ተብሎ ተፅፏል ልጄ። ራሱ ኢየሱስም ‹ነቢይ በሀገሩ አይከበርም› ብሏል።"

"እሱማ ልክ ልካቸውን ነግሯቸው ነበር።"

"በቃ ዝም በይ። እሱ ራሱ ያልመለሳቸውን!" ደንቋቸው ፈገግ አሉ። "በቃ ልጄ ዝም በይ። ባካባቢያችን ያሉት ከሰሙን ያቃጥሩብናል። እዚህ በረሃ ውስጥ ጥለውን ከሄዱ ደግሞ መድረሻ የለንም ሀገራችንንም ጥለናት መጥተናል። ተይ! ‹ጅብ እስኪይዝ ያነክስ› ብለዋል አበው። ብቻ ኢየሩሳሌም እግባ እንጂ በስሌሆም ወንዝ አቅራቢያ ከሚገኘው ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ከተናዘዘላት የርስት ቦታ ላይ ካለው ዴር ሡልጣን ገዳማችን ገብተን እንቀመጣለን። እስከዚያ ግን የልብሽን በልብሽ ያዥው"

አባ ማቴዎስ ምንም እንኳዋ እስራኤላዊ ባይሆኑም ኢየሱስ የተመላለሰባቸውን ቦታዎች ሁሉ ተሳልመው ዴር ሱልጣን ገዳም የመግባት ህልማቸውን እውን ለማድረግ ጉዋጉተዋል። ለዚህም ሲሉ የምንኩስና ቆባቸውን ከራሳቸው አውርደው ልባቸውላይ ደፍተውታል።

ገንፎዋ የተበላባት ሴት የልጇን ሞት ረስታ ረሃቧን ልታስታግስ ከጠረጠረችው ጋር ሀሉ ስትሟገት ሲጻራና አባ ማቴዎስ እየተመለከቱ ምሽቱ እየገፋ ሄደ።

በድንገት በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ ሸራ የለበሱ የጭነት መኪናዎች መብራታቸውን እያንቦገቦጉ መጥተው ሲቆሙ የታጠቁ ኮማንዶዎች ከመኪናዎች ወርደው በፍጥነት አካባቢውን ተቆጣጠሩት። በየድንኳኑና በውጭ አሸዋ ላይ የፈሰሱት ፈላሻዎች እየተጋፉ፣ እየተዋከቡ ወደ መኪናዎች ተጫኑ። ፈላሻ ያልሆኑትም ስማቸውን ‹ሙሴ፤ያዕቆብ፣ይስሐቅ› እያሉ እየተመዘገቡ ተጫኑ። አሸዋው ላይ እንቅልፍ እንደ ስጦ ያሰጣቸውም ዓይኖቻቸውን እየሞዠቁ ተነስተው ሰልፉ ውስጥ ተቀላቀሉ።

ሞሳድ ለዘመቻ ሙሴ ያዘጋጃቸው እነዚህ መኪናዎች በአንድ ጊዜ መቶ ሰው ብቻ መጫን የሚችሉ ቢሆንም መኪናው ላይ የሚወጡት ግን ከእጥፍ በላይ ነበሩ። በምግብ እጦትና በበሽታ ሲሰቃዩ በመኖራቸው እንኳንስ በመኪና በሰይጣናት ፈረሶች ላይ ተፈናጠውም ቢሆን ከዚህ ምድራዊ ገሃነም ማምለጥ ይፈልጋሉ።

ፈላሻዎቹ በተዘጋጀላቸው አውሮፕላን ወደ ቴልአቪቭ ለመብረር ገና በበረሃው ውስጥ በሞሳድ ወደተዘጋጀው አውሮፕላን ማረፊያ ለመድረስ የስድስት ሰዓት የመኪና ጉዞ ማድረግ አለባቸው።

ሲጻራ ሰልፉ ውስጥ ያለውን ግፊ አልፋ መኪናው ውስጥ ልትገባ ስትል አባ ማቴዎስ ስለጠፉባት ተመልሳ ፍለጋ ስትጀምር

ኢትዮጵያ ውስጥ ራሱን ተላጭቶና ለመመሳሰል ፊቱን የዋልካ ጭቃ ተቀብቶ የነበረው ነጭ ሰውዬ እጇን ይዞ እየጎተተ መኪነው ላይ አስወጣቿት ‹‹ይመታል፤የራስህን ተንዝ፤ይመታል፤›› ብሏት ሄደ። መኪናው ውስጥ አፏን ከፍታ ቀረች። አማርኛውን አወላግዶ በመናገሩ ሳይሆን በአባ ማቴምስ መጥፋት።

አውሮፕላኑ ማረፊያ እስኪደርሱ ተፋፍነው ከቆሙት ሰዎች መሃል ብዙዎቹ ለዘለአለሙ አንቀላፉ። መውደቂያ ቦታ ስለሌለ በቁማቸው ሞተው ከመኪናው እስኪራገፉ በቁም ሸክም ሆነው ቆዩ። ከመኪናው ከወረዱ በኋላ በረሀው ውስጥ ታጉረው ቆሙ። ሲጳራ በውዥንብሩና በግርግሩ መሃል እየተዘዋወረች አባ ማቴምስን ብትፈልግም ልታገኛቸው አልቻለችም።

አስፈሪው አውሮፕላን እያስገመገመ ሲያርፍ የበረሃውን አሸዋ በሙሉ ዓይኗ ውስጥ የከተተው ይመስል ማየት አቃታት።

በነፋሱ ተገፍትራ ከወደቀችበት ስትነሳ ብዙ ፈላሻዎች አይተውት በማያውቁት አውሮፕላን ተደናግጠው ወደ በረሃው እየተሯሯጡ ተበታተኑ። እሷ ግን ገሃነም ቢመጣም ላትንቀሳቀስ ወስናለች። አውሮፕላኑ ውስጥ ቀድማ የገባች እሷ ነበረች።

ከዚያ በረሃ ተነስቶ ቴልአቪብ እስኪደርስ አውሮፕላኑ ውስጥም ብዙዎች ሳይመለሱ ሲያሸልቡ አይታለች። አሁን ሞትን ለምዳዋለች። ፍርሃቷ ሁሉ ተሟጦ አልቋል።

ቴልአቪብ ሲደርሱ ቤተ እስራኤላውያኑ እየወደቁ እየተነሱ አስፋልቱን ሲስሙ ቆማ እያየች ነበር። "የተቀደሰው ምድር ይሄ ነው በቃ? ወይ ቅዱስ እግዚአብሔር!" ብቻዋን አጉተመተመች። አባቷን አጣች። አሁን ደግሞ ከአባ ማቴምስ ተነጣጠለች። ደርቃ ቀረች። «ያለ እኔ ማንም ለእኔ የለኝም በቃ። እግዚያብሔርም ፊቱን አዙሮብኛል። ያዙርብኝ እንጂ! ገዳሜንና ፍቅሬን ጥዬ የመጣሁ ከሃዲ አይደለሁ! ግን እኮ እግዚያብሔር ባይተወኝ ኖሮ እኔ ጥያቸው ላለመምጣት ታግዬ ነበር እግዚያብሔር ሲረዳኝ ስላልፈለገ ነው በቃ። እራሴን ማዳን አለብኝ። ለንስሐ ሞት እንድበቃ። ባልበቃስ! ምናባቱ ከዚህ በላይ ገሃነም አለ?» በውስጧ ስትብላላ አንዲት አሮጊት ከጥጓ ተዝለፍልፋ ወደቀች። ሌላ ህፃንም ልንቁስቁስ ብሎ ተከተላት። ሞት በረከተ። አባ ማቴምስን ብትፈልግም ልታገኛቸው አልቻለችም። «ሞቱ? ምናለ ቂጣዋን ቢበሏት ኑሮ! እኔና! ....እኔ አፈር ልብላ! ....እኔ ነኝ ስግደረደር ያስወሰድኳቸው!...ለኔ ብቻ አበሉኝ እንጂ አርባጫውን አፈር ቢቀምሱ ኖሮ እንደኔ ነፍሳቸውን ያቆዩአት ነበር።....... አሁን በየት ብየ ነው የምሄደው? ጼር ሱልጣን የሚባለው ገዳምስ በየት በኩል ይሆን?» እያለች ስታውጠነጥን ኢትዮጵያ ውስጥ ፊቱን በዋልካ ጭቃ ተለቅልቆ



ያየችው ፈረንጅ መጥቶ "አንተ? ና! ተከተለኝ! ማቴምስ ሞቷል!" ሲላት ድርቅ ብላ ቀረች።

"ሞቱ?" አለች። "እኔ አፈር ልብላ።"

ክንዷን ይዟት መኪና ውስጥ አስገባትና ተፈተለከ። «አናንያ እባላለሁ።» አላት እዬከነፈ። አልመለሰችለትም። እየዞረ ያያታል።

ከአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ሲያስገባት ስፍር ቁጥር የሌለው ፈላሻ ስሙን እየተመዘገበ ነበር። ስሟን አናንያ አስመዝግቧት በአዳራሹ ውስጥ ሰፊ ንግግር ከተደረገ በኋላ ሁሉም ሰው ትልቅ የመታጠቢያ ቦታ ሂዶ ታጥቦ የፈላሻዎቹ ልብስ ተሰብስቦ ሲቃጠል የእሷም ገዳም ውስጥ ለብሳው ያደገችው ወይባ ቀሚስና መደረቢያው ተቃጠለባት። በምትኩ ሰውነት የሚያጣብቅ ሱሪና ከላይ ደግሞ ሹራብ ተሰጣትና በግዷ ለበሰች። «ቻው ቻው ኢትዮጵያ........... ሻሎም ቴልአቪብ... ሻሎም -ኢዝራኤሊያ! ........ ሻሎም - ኢየሩሳሌም-ሰላም አሌኩም።» .........

ከወራት በኋላ በአንድ ከቴልአቪብ አቅራቢያ በሚገኝ አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ራሷን አገኘችው።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከአመታት በኋላ ደግሞ ሁሉም እስራኤላዊ ተማሪ እንደሚያደርገው ለወታደራዊ ግዳጅ ወታደራዊ ሥልጠና ሰለጠነች። እብራይስጥ ቋንቋ አቀላጥፋ መናገር ከመቻሏም በላይ በወታደራዊ ቅልጥፍናዋ ትደነቃለች። ፅዮናዊነት በደሟ ውስጥ መቀላቀል ጀምሮ "እስራኤል ለዘለአለም ትኑር!" ማለትም ከጀመረች አመታት አልፈዋል።

እስራኤል ባደረገቻቸው በስለላ የተቀመሩ ጦርነቶች ላይ ተሳትፋ የፈፀመችው ጀግንነት ሲታወሳት ለእሷም ይደንቃታል። በዚህ ወቅት ነበር አናንያ ለሞሳድ የመለመላት። ሞሳድ ማንን መመልመል እንዳለበት ያውቃል። እሷ እንደሆነች የምትጨነቅለት ቤተሰብ የላትም። አባቷም ሱዳን ውስጥ የጊንጥና የእባብ ሲሳይ ሆነው ሲወድቁ አይቷል አደገኛው ኣናንያ - አጥማጁ ሞሳድ። ማንን ብላ ከግዳጇ ወደኋላ ትላለች? ለማን ብላ በጥቅም ትደለላለች?

አጥማጁ አናንያ አጥማጇን አቦ ሸማኔ በማጥመዱ በኩል እንደተሳካለት ሁሌም ይናገራል። የፍቅር አዙሪቱ ውስጥ ለመክተት ሲል ደሞ አሁንም ድረስ ከጥጓ ነው።

ሲጳራ በትዝታ ተስባ ያደገችበትን የታሪኳን ደም ስትጠባ ለሰአታት መቆየቷን ያወቀችው ዶ/ር አናንያ "እና ከዚያ ወዲህ አግኝተሽው አታውቂም?" ብሎ በጥያቄ አሁን ወዳለችበት ዓለም ሲመልሳት ነበር።

“ማንን?” አለች ለሰአታት ስትመለከተው ከነበረው የመንታ ደሴቶች ፎቶ ላይ ዓይኗን ነቅላ።

“ሚራኛን”

“በጭራሽ! ወደ ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ሄጄ ፈልጌዋለሁ። ወዳደግንበት ገዳም በድብቅ ተመላልሼም አጠያይቄ ነበር። ነገር ግን ላገኘው አልቻልኩም። በንስሐ እንዲመለስ ለአርባ ቀናት ታስሮ ከቆዩ በኋላ ሲፈታ ከገዳሙ ወጥቶ እንዳመለጠ ሰምቻለሁ። የት እንደ ደረሰ እግዚያብሔር ይወቀው።”

“እና ከዚህ በላይ መፈለግ አለብሽ?”

“መጨረሻ እስከሚባለው እፈልገዋለሁ።”

“ይሄማ ቂልነት ነው። ሙች ሲጻራ ይሄ እብደት ነው። ይሄኔ እሱ በህይወት ላይኖርም ይችላል። ካለም ይሄኔ ከአንዷ ጋር ትዳር ይዞ ሊሆን ይችላል። ወንዶች እንደሽንኩርት የሚላላጥ ልብ ነው ያላቸው። ይልቅ አሁን የፍለጋሽ መጨረሻ ደርሷል። አሁን እኔ ከጥግሽ አለሁልሽ” እንደገና እየተሟዘዘባት ነው። መልሶ አበሸቃት።

“ሞዛዛ! አታውቅበትም ደግሞ።”

“ባውቅበት እሺ ትይኝ ነበር?”

“ብሽቅ! ሁለተኛ ይህን ጥያቄ እንዳታነሳብኝ። ወደማልፈልገው ትዝታ ውስጥ ከተኸኝ አዘናግተ'ኸኛል ደሞ” ሰአቷን ተመለከተች። በሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ውስጥ ለስብሰባ የተጠሩበት ሰዓት እየደረሰ ነው። በሻጊዝ ጉዳይ።

“በል እንፍጠን” መኪናዋ ውስጥ ተከታትለው ገቡ። መኪናዋን ኮለኮለቻት።



# ፫

## ሎሳንጀለስ ፡ አሜሪካ

ዶ/ር ሚራኘ በሎሳንጀለስ ከተማ ደቡባዊ ምዕራብ ሜፍ ከ101ኛ ጎዳና ገባ ብሎ በሚገኝ ጥንታዊ አፓርታማ ውስጥ መኖር ከጀመረ ሶስት ዓመት ከመንፈቅ አልፎታል። ብዙም ግርግር አይበዛበትም። አፓርታማው ጥንታዊ ቢሆንም የመዋኛ ገንዳውና የመኪና ማቆሚያው በቅርቡ በመታደሱ የዘመናዊነት ይዘት ተላብሷል። በዚህ አፓርታማ የሚኖሩት ሰዎች አብዛኛዎቹ እድሜ ጠገቦች ናቸው።

የዶ/ር ሚራኘ መኖሪያ ቤት በዚህ አፓርታማ ስምንተኛፎቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን ፀጥታ የሰፈነበትም ነው። ከሥራ ተመልሶ አንዳንዴ መስኮቱን ሲከፍተው ከፓስፊክ ውቅያኖስ በሚነሳው የነፋስ ሽውታ ከሚውለበለበው ነጭ የመስኮት መጋረጃ ውጭ ሌላ የሚታይ እንቅስቃሴ የለም። በቤቱም ውስጥ በብዛት ሲገባ የሚታየው ዶ/ር ሚራኘ ብቻ ነው።

ቤቱ ውስጥ ከመሠረታዊ ቁሳቁሶች ውጭ የቅንጦት እቃዎች የሉም። መኝታ ቤቱ ውስጥ ዘመናዊ አልጋ ቢኖርም እሱ ግን የሚተኛው መሬት ላይ በተነጠፈ ፍራሽ ነው። ኩሽና ውስጥ አንድ ትልቅ ብረት ድስት፣ ሌላ አነስተኛ ብረት ድስት፣ መጥበሻ፣ መክተፊያ፣ ቢላዋዎች፣ ሴንኬሎና ሌሎች ትንሽ ቅራቅንቦ እቃዎች በጥቂቱ አሉ። ሳሎኑ ውስጥ ቴሌቭዥንን፣ ኮምፒውተሮች፣ ሶፋና ወንበሮች ሲኖሩ በዚህ ሳሎን ብዙውን ቦታ የያዙት የመፃሕፍት መደርደሪያዎች ናቸው።

እነዚህ ትላልቅ የመፃሕፍት መደርደሪያዎች አንዳንዶቹ ግድግዳውን ተደግፈው ሲቆሙ ሌሎቹ ደግሞ መሃል ላይ በመፃሕፍት ጢቅ ብለው ሞልተዋል። ቤቱም ቤተ መፃሕፍት እንጂ መኖሪያ ቤት አይመስልም። መፃህፍቱ በየፈርጃቸው የተከፋፈሉ ናቸው። የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የህክምና፣ የሳይንስ፣ ወዘተርፈ ተብለው በየሼልፉ አናት ላይ ተዕርባቸዋል። የሐይማኖት መፃሕፍትም እንደዛው። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት፣ የቡድሐ ዝምና የሌሎች ሃይማኖቶች መፃሕፍትም ለየብቻ ተደርድረዋል። በሌላ መደርደሪያ ደግሞ የጥናትና የምርምር ጥራዞች ታጭቀዋል። የተለያዩ ዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያሳትሟቸው ጆርናሎች፣ መፅሔቶችና ጋዜጦችም በየፈርጃቸው የተካተቱበት መደርደሪያ አለ።

መሃል ለመሃል ሳሎኑ ውስጥ የተጋደመው ረጅም ጠረጴዛ ላይ የተከመሩ ወረቀቶች በኮምፒውተሮች መሀል አሉ። ከሳሎኑ በአንድ ጥግ የተነጠፈ ፍራሽ ሲኖር በራስጌ በኩል የማይጠፋው ጊታርም አለ። ዶ/ር ሚራኘ በንባብና በሌሎች ነገሮች ተወጥሮ

ከቆየ በኋላ ራሱን የሚያዝናናው በዚህ ጊታር ነው:: አንዳንዴ ጊታሩን ሲጫዎት ምንም አይነት የከንፈር እንቅስቃሴ አያሳይም:: ትራሱን ጨፍኖ ለረጅም ሰዓታት በጊታሩ ድምፅ ተመስጦ ይቆያል:: በፓስፊቅ ውቅያኖስ ዳርቻ በተለይ ጀንበር ልትጠልቅ አቅራቢያ ጊታሩን ሲጫወት በጥልቅ ይመሰጣል:: በተመሰጠው ውስጥ ግን የጊታሩን ድምፅ ይረሳና የሚያሰበውን የሃሳብ ጅረት ተከትሎ ይነጠቃል:: ሥራዎቹን የሠራቸውም በዚህ ሥልት ነው በጊታሩ የሙዚቃ ቃና ተመስጦ ውስጥ ሆኖ::

ዶ/ር ሚራዥ ቁመቱ መካከለኛ ነው:: ተክለ ሰውነቱ ጠንካራ ወታደር ያስመስለዋል:: አረማመዱና አቋቋሙም የወታደር ቅጥ ነው:: ጥርት ያሉ አይኖቹ ለጠይም ፊቱ ድምቀት አልብሰውታል:: ዓይኖቹም የሚያስፈሩ ሳይሆን የሚጣሩ አይነት ናቸው:: ብዙ ጊዜ ፈገግ አይልም እንጂ ጥርሶቹ ክርችም ብለው ተጠጋግተው በጉራማይሌ ድዱ ላይ የበቀሉና የሚያማምሩ መሆናቸው ከስንት አንዴ ሲስቅ ይታያል:: የሚስቅም ሰዎች እንባቸውን እያንዠቀዠቁ በሚስቁበት ነገር ሳይሆን አንድም ሰው በማይስቅበት ነገር ነው:: አንዳንዴ ሳቅ እንደ ውሃ በወረፋ የሚቀዳ ይመስል ሁሉም ሰው ስቆ ከጨረሰ በኋላ ይስቃል:: ሰዎች ስቀው ሲጨርሱ ሲስቅ ሰዎችን ባሳቃቸው ነገር ሳይሆን ሰዎች በመሳቃቸው የሚስቅ ይመስላል::

ሚራዥ ዝምታው ውቅያኖስ ነው:: ነገር ሲጀምርም እንደ ጅረት:: ብዙዎቹ የሚወዱት ብዙ ስለሚያዳምጣቸው ነው:: ዝም ብሎ አዳምጦ የሱን ሃሳብ ጣል የሚያደርግ ሳይታሰብ ነው:: ብዙ ጊዜ ሲያወራ የሚታየውም በእድሜ ገፋ ካሉ ሰዎች ጋር ነው:: ምናልባትም በገዳሙ ውስጥ ሲያይ ያደገው ሽማግሌዎችን ስለሆነ ይሆናል:: የልጅነት ህልሙም እንደ ዳጋ እስጢፋኖሱ መነኩሴ እንደ አባ ዠምበሩ ትልቅ ጢም እንዲኖረው ነበር:: አሁንም ቢሆን በጆሮ ግንዱ በኩል ቀጠን ብሎ ወርዶ አገጩ ሲደርስ ሰፋ ብሎ ችምችም ያለ ጥቁር ጢም አለው::

አንዳንድ የሥራ ባልደረባዎቹም ችምችም ያለ ረጅም ጥቁር ጢሙን በማጣቀስ አሽባሪው ይሉታል:: ከጢሙ ይልቅ ዝምታው ያሸብራል:: ጢሙ በአጠቃላይ ውብ ፊቱን ክብብ አድርጎ የሚጠብቅ አጥር ይመስላል:: ፀጉሩ ሳሣ በመሆኑ ቢጎፍርም አያስጠላበትም::

ዶ/ር ሚራዥ ድምፁ ወፈር ያለና በውስጡ ብዙ ደስ የሚል ቅላፄ ያለው ነው:: የገዳሙ ዲያቆን እያለ ብዙዎች ሲዘምርና ሲቀድስ ይመሰጡ ነበር:: አሁን ግን በእረፍት ሰዓቱ ከአንድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ባጠናው የጊታር መሳሪያ ድምፅ እንጂ የሱ ድምፅ አይሰማም:: ሲነጋገር ግን የሚያስገመግም የነጐድጓድ ድምፅ ያለው ሰው ነው::

በቤቱ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በማንነቱ ላይ ብዙ ለውጥ አምጥተዋል::ሲያነብአይመርጥም::የሚያምንበትንም የማያምንበትንም



ያነባል:: በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ሆኖ ብዙ የማይመሹ ቀኖችንና የማይነጉ ሌቶችን አሳልፏል:: ከእነዚህ መጻሕፍቱ በቀር ሌላ ዘመድ የለውም:: የሚያገኘው ገቢ በብዛት መጽሐፍ ለመግዣ ይውላል:: ዘመዶቹን አያውቅም:: እናት፣ አባት፣ አጐት፣ አክስት፣ የሚባሉ ነገሮች በአእምሮው መጥተው አያውቁም:: ትዝ የሚሉት የጣና ሐይቅ ደሴቶችና የዛፎች ጥላ ብቻ ናቸው::

ከዚህም ጋር በየቀኑ ትዝ ሳትለው የማታልፈው ግን ሲጻራ ናት:: በሁለቱ ደሴቶች መካከል ያሳለፉት የፍቅር ጊዜ ትዝ ይለዋል:: ከትዝታው ለመላቀቅም መጻሕፍቱ አይነተኛ አማራጮቹ ናቸው:: ከሰዎች ጋር ተቀላቅሎ ብዙ መጫወት አይችልም:: ያደገበት የገዳም ህይወት በሰዎች መካከል ገዳማዊ አድርጎታል:: ሥራውን ግን በአግባቡ ይሠራል:: በጥንቃቄ:: በእሱ ስህተት ሰው እንዲጎዳ አይፈልግም:: ለበሽተኞችና ጤና ላጡ ሰዎች እጅጉን ያዝናል:: ይጠነቀቅላቸዋልም:: «ዶክተሮች የእግዚአብሔር እጆች ናቸው:: እግዚአብሔር ለበሽተኞች ፈውስን የሚሰጣቸው ዶክተሮችን ተጠቅሞ ነው» ብሎ ያምናል::

አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤቱ መጥታ ዝምታውን የምትሰብርለት ማሮዳ ናት:: ማሮዳ እሱ ቤት ስትመጣ መቶ ሰው የሚያወራ ነው የሚመስለው:: መፃሕፍቱን በሚመለከት «ቤትህ እኮ የደራሲ ቤት ነው የሚመስለው» ስትለው

«እኔ የሚታየውንና የሚጨበጠውን አካል ቀድጄ ስሰፋ መፃህፍት ደግሞ የማይታየውን አካሌን ቀድደው ይሰፉልኛል:: ሐኪሞች በሽተኞችን ብቻ ሲያክሙ ደራስያን ደግሞ ሐኪሞችንና በሽተኞችን ያክማሉ:: ደራስያን እንደ መላእክት ናቸው:: መላእክት የሰውን ወደ እግዚአብሔር የእግዚአበሔርን ወደ ሰው ሲያደርሱ ደራስያን ደግሞ የሕዝቡን ወደ መንግሥት የመንግሥትን ወደ ሕዝብ ያደርሳሉ:: እውነተኞች ደራስያን የሕዝብን ወደ መንግሥት አድርሰው መንግሥት ካልሰማ የመላእክትን ተግባር በማገዝ የሕዝብን ወደ እግዚአብሔርም ያደርሳሉ:: እውነተኞቹ ደራስያን በህዝብና በመንግሥት፡ በመንግሥትና በመንግሥት፣ በህዝብና በህዝብም መካከል የሚኖሩ የማይሰበሩ ድልድዮች ናቸው:: እውነተኞቹ መልእክቱን በወቅቱ ሲያደርሱ ሐሰተኞቹ ደራስያን ደግሞ የነበረው ሥርዓት ካለፈ በኋላ ከምናምን ዓመት በፊት የሣፍኩት ያኔ ፈርቼ ያላሳተምኩት ብለው ህዝብን ያቆስላሉ:: አንድ ሥርዓት ካለፈ በኋላ ተራ ሰውም ቢሆን ያንን ሥርዓት ቢሳደብ አይታሰርም::ስላለፈው ስርዓት አስቀያሚነት በወቅቱ አስቀያሚነቱን መዋጋት ፈርቶ ካለፈ በኋላ ህዝቡን የሚሸነግል ደራሲ እሱ ከሐሜተኞቹና ጅብ ካለፈ ከሚጮሁት ውሾች ተራ ይመደባል:: ያለፈውን ስርዓት የሚከስ ደራሲ የሞተ ውሻን ከሚደበድብ ሰው አይሻልም:: የነበረበትን ሥርዓት እንዲሻሻል የሕዝብን ጩኸት ያላስተጋባ ደራሲ ሥርዓቱ ካለፈ በኋላ ቢንተገተግ እሱ የሞተ ውሻን ከሚደበድብ ቂል በምን ይሻላል? የህዝብን ብሶት ወደ መንግሥት

የማያደርሱ ደራስያን የመንግሥትና የህዝብ ጠላቶች ናቸው:: መንግሥትንም ህዝብንም ያሳስታሉና:: መታተም ባለበት ዘመን ያልታተመ ድርሰትና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ አንድ ናቸው..» እያለ ይመልስላታል::

ሜሮዳ ይህን ነገሩን ስታይ «በእውነት ደራሲ ብትሆን ሳይሻል አይቀርም»ʻትለዋለች::

እሱም «ደራሲ ልሁን ተብሎ አይከንም:: ግን ያደከብት ቦታ ለድርሰት ሥራ አመቺ ነበር:: ገዳሙ ውስጥ ያነበብኳቸው ገድላትና ተአምራት ከሃይማኖታዊ ገፅታቸው ጀርባ የረቀቁ የሥነ ፅሑፍ ሥራዎችም ናቸው:: እነዚህ …….. የኢትዮጵያ ገድላትና ተዓምራት የፈጠራ ሥራዎች ከሆኑ የፃፏቸው ሰዎች የኖቤል ተሸላሚዎች መሆን ይገባቸዋል:: በልብወለዳዊ ዓይን ካየናቸው እነዚህን መጽሐፍት የፃፏቸው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶች የኖቤል የሥነ ፅሁፍ ሽልማትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን መጠራረግ ይገባቸዋል» ይላታል::

ሚራዥ ታፍሶ የሰሜኑን ጦር ከተቀላቀለ በሁዋላ በሁለት አውደ ውጊያዎች ተሳትፏል:: በሰሜኑ ጦርነት ወደ ሰንጠቅ ብርጌድ በመጨረሻ ከተቀላቀሉት ጓዶች ውስጥ አንድ ጥሩ ሥነ ምግባር የተላበሰ ወታደር ጓደኛ በማግኘቱ በህይወቱ ላይ ብዙ ለውጥ ያመጣለት እሱ ነው:: ወታደሩ አስገራሚ ሆኖ አገኘው:: ይህን ወታደር በማሰልጠኛ ጣቢያ ውስጥም አይቶት ነበር:: እንዲያውም አንድ የተናገረው ቃል ትዝ ሲለው ይኖራል:: በጀርባቸው አሸዋ ተሸክመው ጫንጫን እየተነፈሱ ወታደራዊ ሥልጠና በሚሰለጥኑበት ወቅት «በሥልጠናው ብዙም አትማረርበት:: የሰላም ጊዜ ልምምድ ለክፉ ቀን ያገለግላል:: ብትችል ሀገርህን ከገንጣዮች ትታደግበታለህ:: ባትችል ራስህን ታስመልጥበታለህ»ነበር ያለው:: ይህ ወታደር ከጀርባው ከተሸከመው ወታደራዊ ትጥቅ በተጨማሪ አንድ ሻንጣ ሙሉ መጻሕፍትም ተሸክሞ ይዋጋ ነበር:: ጦርነቱ ጋብ ሲል መፅሐፉን ከሻንጣው አውጥቶ ማንበቡ ይጀምራል:: የክፍል ጓደኞቹ «ሌኒን» ብለው ሲጠሩት «እኔ ሌኒን አይደለሁም! እኔ ራሴ ነኝ ዶ/ር ዣንጊዳ!» ይላቸዋል::

«እየቀለድክ ነው?» አለው ሚራዥ አንድ ቀን:: «ዶክተር ነህ በርግጥ?»

«አዎን» አለው ዣንጊዳ:: «በህክምና ተመርቄ ከቤተሰቦቼ ጋር በደስታ የምርቃት በአሌን ስናከብር የቀበሌ ሹሞች አፈሱኝ»

«ስንት ጦር ቀስለኛ ሆኖ የሚያክመው አጥቶ ወየው እናቴ እያለ ሲሞት ዶ/ሩን ነው ተራ ወታደር ያደረጉህ?»

«የሚያደርጉትን አያውቁምና አትፍረድባቸው::»

«ወይ ጉድ!» ብሎ ዝም አለ ሚራዥ::

በዚህ ጦር ሠራዊት ውስጥ ዶ/ር ዣንጊዳን በማግኘቱ ከመፅናናቱም በላይ በድብቅ መጽሐፍ እየዋሰው ማንበብ ጀመረ::



የልብ ወለድ፣ የፍልስፍና፣ የታሪክ ፣ የሥነ ልቦና መጻህፍትን ከዶ/ር ዣንጊዳ እየተዋሰ አነበበ:: መጻህፍቱን ሽፋንና ርዕሶቻቸውን ገንጥለው ያቃጥሏቸው ነበር:: ምክንያቱም ከሌኒንዝም- ማርክሲዝም ፍልስፍና ውጪ ሌላ ሀሳብ የያዙ መፃሕፍትን ሲያነቡ ቢያዙ «የኢምፔሪያሊዝም አቀንቃኞችና የሲ.አይ.ኤ ሰርጎ ገቦች» ተብለው የሚደርስባቸውን አደጋ በመፍራት ነው::

መፅሐፍቱን ይገነጥሉና በሌላ ካርቶን ከለበዷቸው በኋላ አዲስ ርዕስ ይሰጧቸዋል:: «የወዝ አደሮች ትግል»፣ «ማርኪሲዝም»፣ «ሌኒንዝም»፣ ወይም «የሠራተኛው መደብ ትግልና የበዝባዦች ውድቀት» ብለው ይሰይሙታል::

ሚራዥ ለዶ/ር ዣንገዳ የህይወቱን ታሪክ አጫውቶታል:: በጦር ሰፈራቸው ውስጥም በአንድ ክፍል ውስጥ ከሌሎች ስድስት ወታደሮች ጋር ስምንት ሆነው ሲኖሩ በጣም ተቀራርበው የሚያወሩት ሚራዥና ዶ/ር ዣንጊዳ ነበሩ::

ሚራዥ በገዳም ውስጥ ያደገ መሆኑን ከነገረው ጊዜ ጀምሮ ዶ/ር ዣንጊዳ «ገዳማዊው» ብሎ ነው የሚጠራው::

«ገዳማዊው!» ይለዋል:: ዶ/ር ዣንጊዳ::

«ወዬ!»

«ውዳሴ ማርያም አስተምረኝ:: እኔ ደግሞ እንግሊዘኛ አስተምርሃለሁ::»

«ምን ገዶኝ» ይላል ሚራዥ:: «ግን ምን ያደርግልሃል ውዳሴ ማርያም? ክላሽንኮቭና ውዳሴ ማርያም አይጣጣሙም::»

ዣንጊዳ...የሚራዥን የትምህርት አቀባበል ሲያይ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ቢገባ ባጭር ጊዜ ውስጥ ታላቅ ሰው እንደሚሆን ነግሮት ከወታደራዊ ካምፑ ካመለጠ ትምህርት ቤት እንደ ሚያስገባው ቃል ገብቶለታል:: መውጫ ቀዳዳ አጥተው ነው እንጂ ውስጥ ውስጡን ሁለቱም ከወታደራዊ ካምፑ ለመጥፋት ካቀዱ ሰንብተዋል::

በጦር ሰፈሩ ስምንት ሆነው በሚኖሩባት መጠለያ ውስጥ የተንጠለጠለው ፋኖስ ድቅድቁን ጨለማ ወደ ውጭ በሚጋፋበት አንድ ምሽት እንደቀድሞው ሚራዥና ዣንጊዳ አፍ ላፍ ገጥመው ያወራሉ:: ሌሎቹ ወጥ ቤቱዋን በጋራ ስለመወሰብ እቅድ ይነድፋሉ:: ከዚህ ቀደምም የአንድ ገበሬ ሚስት በመድፈራቸው ከባድ ቅጣት ከተቀጡ ሳምንት አልሆናቸውም::

ሚራዥና ዣንጊዳ በአንድ መፅሐፍ ይዘት ዙሪያ እየተነጋገሩ ቢሆንም ጆሮአቸው ግን ስለወሲብ ከሚያወሩት ወታደሮች የሚመጣውን ድምፅ እየተቀበለ ነበር:: በዚህ ቅጽበት ከስድስቱ አንደኛው ወታደር ከውጭ እየተንደረደረ አንዲት ሴት ተሸክሞ ገባ:: አፏ በአረንጓዴ ቅዳጅ ልብስ ተለጉሟል:: ታልጐመጉማለች:: ምን እንደምትል ግን አትሰማም:: ሰውነቷ

ደልደል ያለና ለወሲብም የምትጋብዝ አይነት ናት:: ስድስቱ ወታደሮች ሊፈራረቁባት ካቀዱ ቆይተዋል:: ወጥ ቤቷ ሜሮዳን::

«እኔ እጀምርና ሌሎቻችሁ ትቀጥላላችሁ:: ....አንተ ከኔ ትቀጥላለህ.... ከዛ አንተ ... አንተ ... አንተ ... አንተ ... ሌላም የሚፈልግ ካለ መቀጠል ይችላል:: ግን ሁላችሁም ሃምሳ ሃምሳ ብር ለመያዛችሁ እርግጠኛ መሆን አለባችሁ:: አለቀ በቃ::» ብሎ እየተጣደፈ ሱሪውን ዝቅ አድርጐ ላይዋ ላይ ተከመረባት:: ሊሎቹ መጀመሪያ ባይሆኑ እንኳ ሁለተኛ ባለተራ ለመሆን እየተጉሻሸሙ ነው:: ባለፈው እንዲሁ አንድ መንደር ውስጥ የያዙአትን የአንድ ገበሬ ሚስት ሲፈራረቁባት ገና ሶስተኛው ሰው ላይ ነበር በድን የሆነችው:: ይህችም ሳትዝለፈለፍ በትክክሉ ለማግኘት እየተገፋፉ ነው::

ሚራኸና ሆንጊዳ የሚያዩትን ትርኢት ማመን አቅቷቸዋል:: ሚራኸ በተለይ ይህ አይነት ትዕይንት የመጀመሪያው ነው:: ስለ ወሲብና ዝሙት አንብቦ ቢያውቅ እንጂ በገሃድ አይቶ አያውቅም:: ልቡ በድንጋጤ እየመታ እያለ «ገዳማዊው ሃምሳ ብር ከሌለህ ላበድርህ እችላለሁ» አለው ላይዋ ላይ ተከምሮ የሚጋልባት ወታደር::

«አፈር ብላ! ልቀቃት አሁን»

«ኧረ እባክህ!»

«ልቀቃት ብዬሀለሁ ጀርባህን በጥይት ሳልበሳው::» ክላሽንኮቩን አቀባብሎ ቆመ ሚራኸ::

«አይ የመነኩሴ ነገር! ወይ ዲያቆን መሆን! ይልቅ ና! ዛሬ አይነጥላህን ግለጥ:: ሌላ ጊዜ የምታፈርስበትን ዕድል ላታገኝ ትችላለህ:: ስላልቀመስከ ምንም ላይመስልህ ይችላል:: ግን ይህን በመሰለ መልካም ማዕድ ላይ ምላጭ መሳብ ገሃነም ነው የሚከትህ::»

«ገሃነም ግባ!» አለ ሚራኸ ጠመንጃውን ለሆንጊዳ ሰጥቶ ክናዱን እየሰበሰበ::

«አትለቃትም?» አንገቱን ይዞ ከላይዋ አንስቶ አፍንጫውን በቦክስ ነረተው::

«ሌሎቻችሁ እነቃነቃለሁ ብትሉ ይህን ጥይት ነው የማርከፈክፍባችሁ» አለ ሆንጊዳ ሚራኸ ያቀበለውን ክላሽንኮቭ ከኋላቸው ወድሮ:: «ውሾች»

ሴቷ ላይ ተከምሮባት የነበረው ወታደር ፈርጣማ ስለነበር ሚራኸን መንጋጭላውን በቦክስ ሲነርተው ራሱን አዙሮት ተንገዳግዶ ቆመ:: ሚራኸም መልሶ በደምፍላት አገጩን ሲያጣምመው ወታደሩ በቁሙ ተዘረረ::

ሴቷ እየተንከባለለች ወደ ሆንጊዳ ተጠጋች:: ሚራኸ ወታደሩ እንደወደቀ በክስክስ ጫማ ጭንቅላቱን ከመሬቱ ጋር አጣብቆ ደፈጠጠው::



ሴቷ አዲስ የወጥ ቤት ሠራተኛ መሆኗን ያወቁት ወዲያው ነው:: ሆንጊዳ ጠመንጃውን እንደ ወደረ ሻንጣውንና ጓዛቸውን እንዲይዝ ለሚራኸ ነግሮት ጓዛቸውን
ጠቅልለው ከሴቷ ጋር ክፍሉን ለቀው ወጡ::

ጥይት ተኩሰው ራሳቸው ርምጃ መውሰድ አይችሉም:: ያላቸው አማራጭ ክፍሉን ለቀው መውጣት ነበር::

«እኔ......» አለ ሆንጊዳ ከወጡ በኋላ:: «ከዚህ ሠራዊት ጋር ከእንግዲህ አንዲትም ጥይት በጠላት ላይ አልተኩስም::..... ሚራኸ ማምለጥ አለብን::»

«አዎን:: እኔም ይህን እያሰብኩ ነበር::» አለ ሚራኸ:: ሴቷ እየተንቀጠቀጠች ነበር የቆመችው::

«ግን እንዴት ማምለጥ እንችላለን?» አለ ሚራኸ

«ዋርድያዎችን አውቃቸዋለሁ:: እኔ ሄጄ እነሱን ሳዋራቸው አንተ ተከትለኸኝ ትመጣለህ:: የሚቀጥለውን ደግሞ የሚያመቻችልን ይሄ ነው» ብሎ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጥ ሰጠው::

«ከኔ ጀርባ ትሆንና ሁሉንም በቅልጥፍና ትመታቸዋለህ::»

«የት አገኘኸው?» አለ ሚራኸ ማፈኛ የተገጠመለትን ድምፁ ሳይሰማ የሚተኩሰውን ሽጉጥ እያገላበጠ::

«ውጊያ ውስጥ ከወደቀ ጄነራል ላይ የወሰድኩት ነው::» አለው ሆንጊዳ::

«ግን ቀልጣፋ መሆን አለብህ አለበለዚያ ጭቃ ነው ሚያረጉን::»

«እንዴ ጠብቁኝ::» ብላ እየፈጠነች ወደ ወጥ ቤት ሄደች:: ወጥ ቤቷ ሜሮዳ::

«የምናመልጥበትን ጊዜ ለምን አናዘገየውም?» ሲል ሚራኸ ጠየቀው::

«ሺህ ጊዜ ብንዘጋጅ ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም:: ቢኖርም ከዚህ ሠራዊት ጐን ቆሜ ከእንግዲህ አልዋጋም:: ልንገርህ ሚራኸ? ይሄ ሠራዊት አያሸንፍም:: በውስጡ ብዙ ባለጌዎች አሉበት:: ጠሩን አሰልፈው የሚያስጨርሱ ቅጥረኞች ተሰግስገውበታል:: አሁን እነዚህ ደፋሪዎች ቅጥረኞች ላለመሆናቸው ምንም ማረጋገጫ የለንም:: የገበሬ ሚስቶችና ልጃገረዶች እየተደፈሩ ነው:: ጨዋዎችና የዋሆች እናቶቻችን እየተደፈሩ ነው:: ወታደር እየተፈራረቀባቸው ደም የሚሸኑ ሴቶች ሥፍር ቁጥር የላቸውም:: ብዙ የተከበሩ ባለትዳሮችና ሴቶች አንገታቸውን ደፍተዋል:: የካህን ሚስት ሳትቀር ቄሱ መስቀሉን ይዞ እየገዘተና እየተማፀነ ተደፍራለች:: ሴት ተማሪዎችና የገበሬ ልጆች ያለ እድሜያቸው ልጅ አዝለዋል:: ከፊሎቹ የማያውቁትን ወታደር ልጅ አርግዘዋል:: ይህ ሁሉ የሆነው በጥቂት ቅጥረኞችና በባለጌዎች ነው:: ይህ ሁሉ ርግማንና እንባ የሚፈስበት ሠራዊት እንደሚሸነፍ ከወዲሁ መገመት አያዳግትም:: የገበሬ ልጅና ተማሪ ታፍሶ ያለበቂ ሥልጠና እና ስንቅ ወደ ጦር

ግንባር እየተማገደ እንዴት ነው ድል የሚገኘው? በዚህ ሠራዊት ውስጥ እናት ሀገራቸውን ከገንጣዮች ለመታደግ የሚፋለሙት እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ሀገሪቷም እነዚህን ጀግኖች በየጦር ግንባሩ እያጣች ነው:: ጀግኖችና ሀቀኛ ልጆቿ ደማቸውን እያፈሰሱላት አድርባዮችና ቅጥረኞች የሚሸሙባት ናት ይህች አገር::» እንባው አንቆት ፀጥ አለ ዣንጊዳ::

«አዎ:: ልክነህ ዣንጊዳ የሀገራችንን ጥፋት ቆመን ከምናይ እግራችን እንደመራን ብንሄድ ይሻላል::»

«ሚራዥ.... እግራችን አይመራንም ጭንቅላታችን እንጂ:: ጭንቅላት ነው እግርን የሚያዘው:: ችግራችንም መምራት የሚገባው ስለማይመራን ነው::»

«ልክ ነህ ዣንጊዳ:: ስለተሳሳትኩ ይቅር በለኝ::»

«የሚጋነን አይደለም:: ከሁሉም በላይ ስህተትን አምኖ ማሻሻል ይበልጣል:: ያልተሳሳተ አይማርም» አለ ዣንጊዳ::

«ሚራዥ ያልኩህን እንዳትረሳ በፍጥነት ዋርድያዎችን መቆጣጠር አለብን::»

«እኔ ነኝ የምቆጣጠራቸው» አለች ወጥ ቤቷ ሻንጣዋን አዝላ:: ከመጣች ቆይታለች:: ቆማ እያዳመጠቻቸው ነበር:: «ባለ ውለታዬ ናችሁ:: እናንተን መርዳት አለብኝ:: እንኩ ሻንጣዬን ያዙልኝ:: የባትሪ ምልክት ሳሳያችሁ ብቻ ትመጣላችሁ:: ርቧቸው ስለነበር ምግብ እንዳመጣላቸው ተማፅነውኛል:: ግን ቢያንስ አርባ ደቂቃ መታገስ አለባችሁ:: ቃኝዎች እንዳይዟችሁ ጓዙን ደብቁትና ሽንት ቤት የምትሄዱ ምሰሉ:: ሁሉን ነገር ለእኔ ተውት::»

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት መዳረሻ ላይ የባትሪውን ምልክት አዩ::ጓዛቸውን ተሸክመው ወደ በሩ ሲሄዱ ዋርድያዎች ወዳድቀዋል::

«ፍጠኑ::» አለች ወጥ ቤቷ:: «ሌላ አደጋ ውስጥ ሳንገባ ማምለጥ አለብን:: ጥያቄ አልቀበልም» ሻንጣዋን ከሚራዥ እጅ ተቀብላ ወደ ጫካው ተመሰገች:: እነሱም ተከተሏት::

ጐህ ሲቀድ ተሰነይን በርቀት አልፈው ከሱዳን ጠረፍ ሊደርሱ የስድስት ሰዓታት የእግር ጉዞ ይቀራቸው ነበር::... አስቸጋሪው ጉዞ ከዚህ በኋላ እንደሆነ ነገረቻቸው:: ከኋላቸው የሚከተሉ ፈላጊዎች ሊኖሩ ከመቻላቸውም በላይ በአካባቢው ከነበረው የጦርነት ውጥረት አንፃር በሌላ ጦር እጅ የመውደቃቸው አደጋ በዛው ልክ እንደሆነም ጭምር:: ....ከአንድ አለታማ ሸለቆ ውስጥ ሲደርሱ ዐሐይ እግሯን ሰደደች:: ሸለቆው ውስጥ ተደበቁ::

«ሜሮዳ እባላለሁ::»

«ዣንጊዳ እባላለሁ እሱ ደግሞ ገዳማዊው ሚራዥ ነው::» ሁላቸውም የፈካ ገፅታ ታየባቸው::

«አሁን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል::» አለች

«ጥያቄ አንድ::» አለ ዣንጊዳ::

«ዋርድያዎቹን እንዴት ገደልሻቸው?»



«ምግቡ ተመርዞ ነበር:: ተመለሰ?»

«በትክክል ተመልሶልኛል::»

«የሚቀጥለውን የጥያቄ እድል ለገዳማዊው ልስጥ:: ስሙን ማን ነበር ያልከኝ?»

«ሚራዥ»

«ሚራዥ... ያንተ ጥያቄስ?» አለች ወደ ሚራዥ ዞራ:: መልስ አልሰጣትም:: ወደ ምሥራቅ ዞሮ ከንፈሩን ብቻ እያንቀሳቀሰ ነበር::

«የጠዋቱን ፀሎት እያደረሰ ነው:: ሁል ጊዜም እነደዚህ ነው» አለ ዣንጊዳ::

«እሺ እንተ ሁለተኛውን ጥያቄ ጠይቀኝ::»

«ስለሚቀጥለው ጉዞ መነጋገር እንችላለን?» አላት ዣንጊዳ::

«በደንብ::» ሻንጣዋ ውስጥ የተጣጠፈ ካርታ አውጥታ ነፃ ቀጠናዎችንና የጦር ሠራዊት የሠፈረባቸውን አካባቢዎች አሳየችው::

«ይህ አካባቢ የህወሐት ይዞታ ነው::» ዣንጊዳ በግርምት እየተመለከታት ነው::

«ይህኛው ደግሞ የሻዕቢያ::» ፍጥነቷና ንግግሯ የወጥ ቤት አይመስልም::

«ወጥ ቤቷ.. ይቅርታ.. ሜ..ሮዳ.. ሜሮዳ ስለአንቺ ማንነት ማወቅ እንችላለን?» ሚራዥ ፀሎቱን ጨርሶ ካርታው ላይ አፍጥጦ ነበር:: አሁን ግን እሷ ላይ አፈጠጠ::

«ወጥ ቤቷ ሜሮዳ ነኝ!» ፈገግ አለች::

«አትቀልጂ ንገሪን::» ዣንጊዳ ደግሞ ጠየቃት::

«እሱን ለሌላ ጊዜ እንተወው:: አሁን በአላማ አንድ ሆነናል:: ስለዚህ አብረን የጀመርነውን ጉዞ መጀመሪያ እንጨርስ ሌላው አይመልጠንም::»

«ተስማምተናል ወጥ ቤት:: ስለካርታው ትንታኔሽን ቀጥይ» ሚራዥ በሚያስገመግም ድምፁ አጉተመተመ::

«እዚህ ካምፕ ላይ ሶስት ብርጌድ ሠራዊት አለ:: እዛኛው ላይ ደግሞ ሁለት ብርጌድ::» ካርታው የሰሜን ኢትዮጵያን የወታደራዊ ቁልፍ ቦታዎችና የጦር ሰፍሮችን የያዘና በመረጃ የተሞላ ነው:: የወታደር ብዛት፣ የመሳሪያ አይነት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዛት፣ ወታደራዊ ብቃት፣ የመልክአ ምድር ድጋፍ በካርታው ግርጌ በቁጥርና በኮድ ምልክቶች ታጭቋል::

«ከዚህች ሴት ጀርባ አንድ ትልቅ ኃይል አለ::» ሲል አሰበ ዣንጊዳ:: «ማንም ይኑር ማን ብቻ እኔንና ሚራዥን ከዚህ ጥልፍልፍ እሳት ታውጣን::»

«አሁን.....» አለች ሜሮዳ:: «ልብሶቻችሁን አውልቁ::» ሁለቱም «ምን?» አሉ ወደሷ በአንድ ላይ አፍጠው:: ሻንጣዋን ፈትታ ሶስት የተለያዩ የሴት አሮጌ ቀሚሶችና የተቀዳደዱ ነጠላዎች አወጣች::

«ለዛሬ ሴት መሆን አትፈልጉም?» አለች እንዲለብሱት እየጋበዘቻቸው::

«እንሆናለን እንጂ::» አለ ዣንጊዳ በሞተ ድምፅ:: ሚራዥ ቀሚሱን ሲለብስ ሳቁ አፈነው::
«እኔ ግን ሰው ቢያገኘኝ የምስቅ ይመስለኛል::ለመሆኑ ጢም ያለው ሴት አለ?» አለ ሚራዥ ሳቁ እየመጣ::

«ሞልቶ::»

«ሙት በይኝ እስቲ::»

«ግዴለህም ጢምህን እኔ ድራሹን አጠፋልህና በነዚህ ቀለሞች ሳሰማምርህ ቁርጥ ባል የገጠር ሴት ነው የምትመስለው:: ግንባርህን ሸብሸበው::»

«ሸብሸቤ ልንዝ?»

«ሸበሸብኸው በዚህ ቀለም ከቀባሁት በኋላ ስትለቀው ቀለሙ በሚፈጥረው ሸንተረር የተሸበሸበ ይመስላል:: ከዚያም አሮጊት ትመስላለህ::» አለችና ሜሮዳ እንደነገረችው አደረገችለት::

ፊቱን በሰጠችው መስተዋት እያየ ከተገረመ በኋላ ሻንጣውን ማዳበሪያ ውስጥ ከተተችለትና ወገቡ ላይ ጭና በነጠላ አስነገተችው:: ምርኩዝ አስይዛው ጉንበስ ብሎ መሄድ አለማመደችው:: አጭር የሴት ጥላም ያዘ:: ዣንጊዳን ደግሞ በራሱ አቁርሮ እንዲሸከም አደረገች:: በወገቧ ሻንጣዋን ጠቅልላ ተሸክማ እሷ ከፊት፣ ሚራዥ ከመሃል፣ ዣንጊዳ ደግሞ ከኋላ ሆነው ጉዟቸውን ቀጠሉ:: በጦርነቱ የተፈናቀሉ ሴቶች ነው የሚመስሉት::

ገላጣ ቦታዎች ላይ ወሬ እየሰለቁ አስቸጋሪ ቦታዎችን ደግሞ ድምጥማጣቸውን እያጠፉ ብዙ ርቀት ከተጓዙ በኋላ የሚንደቀደቅ ድምጽ ሲሰሙ ሁላቸውም በድንጋጤ ወደኋላቸው ዞሩ::

አረንጓዴ ሬንጀር ቀለም ያለው ሄሊኮፍተር ደርሶባቸዋል:: ከሄሊኮፍተሩ በር ላይ መትረየስ ወድሮ የመገናኛ ሬድዮ ጆሮው ላይ የሰካው ተኳሽ በሬዲዮው እየወሸከተ ቁልቁል አንዳች ነገር ያስሳል:: ዓይኑ ቁጥቋጠውና ቋጥኙ ላይ ሁሉ ይቃብዛል::

ሄሊኮፍተሩ ዝቅ ብሎ እየበረረ ይንደቀደቃል:: በሬድዮ የሚለፈልፈውና መትረየስ የወደረው ወታደር ጥቁር መነፅሩን አውልቆ በጠር ሜዳ መነፅር ሲመለከት ሶስት ቡትቶ የለበሱ ሴቶች ውልብ አሉለት መነፅሩ ውስጥ:: መትረየሱን አስተካክሎ በፍጥነት አነጣጠረባቸው::

«ምን ይሻላል?» አለ ሚራዥ

«እኔ እንጃ!!» አለ ዣንጊዳ ተስፋ በቆረጠ ድምጽ::

«የመሮጥ አዝማሚያ እንዳታሳዩ::» አለች ሜሮዳ::

«እንዴ ለምን ሮጠን ቋጥኙ ውስጥ አንገባም?»

«እንዳትሮጡ ብያለሁ:: ዝም ብላችሁ በተረጋጋ ሁኔታ ተራመዱ»



«እየቀረቡን እኮ ነው::»

«ብንሮጥም አናመልጣቸውም:: እሳት የሚተፋ መትረየስ እኮ ነው ያነጣጠሩብን::»

አካባቢውን ያነዋወጠ ፍንዳታ ሲሰሙ በድንጋጤ ደንዝዘው ወደ ኋላቸው ዞሩ:: ሄሊኮፍተሩ በእሳት እየጋየ ወደታች ተምዘገዘገ::

«አሁን በፍጥነት መሮጥ አለብን:: እንሩጥ::» አለች ሜሮዳ:: ሚራዥ ሴት መሆኑን ረስቶ ጉባጣውን አቃንቶ ይፈተለክ ዠመር:: ዣንጊዳም ቀሚሱን እስከጭኑ ከፍ ከፍ አርጎ ከኋላ ተከተላቸው::

ሄልኮፍተሩ እየጋየ ሲወድቅ ፓይለቱ በፓራሹት ወደ ላይ ተመንጥቆ ወጥቶ ከአንድ አነስተኛ ኮረብታ ላይ ሲያርፍ አዩት::

«ራሱ በራሱ ነው የነደደው?» ሚራዥ ከኋላዋ እየሮጠ ጠየቃት::

«አይደለም:: በጠላት አየር መቃወሚያ ተመትቶ ነው» አለች ሜሮዳ:: «ይህንም እጠብቅ ነበር:: ቀጠናቸውን አልፈው በጠላት ክልል ውስጥ ገብተው ነበርና::» እየተፈተለኩ አንድ ሸለቆ ውስጥ ገብተው ተደበቁ:: ጀንበር እስክትጠልቅ በሸለቆው መካከል ባገኙት ዋሻ ውስጥ አምሽተው ወደሱዳን የሚገቡበትን እቅድ መንደፍ ጀመሩ::

«እናንተ ሴቶች» አለች ሜሮዳ በፀጥታ አዘቅት ውስጥ የገቡት ጓደኞቿን:: «ሴትነቱ አይበቃችሁም?»

«እኔ ግን ተመችቶኛል:: ቀሚሱ የማረብኝ አይመስላችሁም?» አለ ሚራዥ መቀነቱን እየፈታ::

«እራትስ ብንቀማምስ ምን ይመስላችኋል?» ብላ ከሻንጣዋ ውስጥ በፌስታል የቋጠረችውን ምግብ ፈትታ አቀረበች:: ሚራዥና ዣንጊዳ ተያዩ:: ሙሉ በሙሉ አላመኗትም:: የሚከተሏትም በጥንቃቄ ነበር::
«ገብቶኛል:: የዋርድያዎች እጣ ፈንታ እንዳይደርሳችሁ ፈርታችሁ ነው አይደል? እመኑኝ እኔ እናንተን የማጠቃበት ምክንያት የለኝም» ብላ ጥቅልል አርጋ በወንድ አጉራረስ ቀድማ ቀመሰችላቸው:: «በእውነት እናንተ ባለውለታዬ ናችሁ:: እነዚያ ሁሉ ወታደሮች ቢፈራረቁብኝ ኖሮ እስከአሁን ደም ሸንቼ ልሞት እችል ነበር:: እናንተ ታደጋችሁኝ እንጂ ::»

አካባቢው ሙሉ በሙሉ በጨለማ ከተዋጠ በኋላ ለቀጣዩ ጉዞ መዘገጃጀት ጀመሩ:: ቀሚሶቻቸውን በጀለቢያ ቀየረችላቸው:: ሙስሊም የአረብ ሴቶች የሚለብሱትን ዓይነርግብም ከለበሱ በኋላ የሱዳን ዜጎች ለመምሰል የሚያስችላቸውን ገፅታ እስኪላበሱ ድረስ ራሳቸውን አስተካከሉ::

«እነዚህ ዘዴዎች የሞከርኳቸውና ውጤታማም ስለሆኑ አትስጉ» ብላ የሱዳን መታወቂያዎችን አውጥታ ስትሰጣቸው

ባግራሞት ተመለከቿት፡፡ ሁለቱም መታወቂያዎች በሴት ስሞች የተዘጋጁ ናቸው፡፡

«ቆይ» አለ ዣንጊዳ «አንቺ ማን ነሽ?» ሚራዥ ተጨምሮ፡፡

«ወጥ ቤቷ ሜሮዳ፡፡»

«አትቀልጂ፡፡»

«የምንነጋገርበት ጊዜ አሁን እንዳልሆነ አልነገርኳችሁም?»

ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ ውስጥ እየወደቁ እየተነሱ ለአራት ሰዓታት ያክል ተጉዘው ከጠረፍ ጠባቂዎች ሊደርሱ አራት መቶ ሜትር ያህል ሲቀራቸው

«ቁሙ!» አለቻቸው፡፡ «እየደረስን ነው፡፡» ከሻንጣዋ ውስጥ ያወጣችውን የተሰባበረ ሬዲዮ የሚመስል ነገር ገጣጥማ መነጋገር ጀመረች በእንግሊዘኛ ቋንቋ፡፡ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ሬድዮው ወደ እሷ ደወለ፡፡

«ዊ አር አን ዘ ዌይ ...ሺሺሺ ... ዊ ... ሺሺ አር ..ሺሺ ... ኦን ...ሱዳኒዝ ...ቦደር ናው፡፡ ሺሺ ... ካም ...ሺሺ ...አሉን ...ሺሺ ፈርስት ኘሊስ ...466፡፡ ዩ ካን ካም ቱ ዘ ቦርደር ናው፡፡» ሜሮዳ እዚሁ እንዲጠብቋት ነገረቻቸውና ወደ ጠረፍ ጠባቂዎች ገሰገሰች፡፡

አካባቢው ፀጥ ረጭ ብሏል፡፡ መብራቷን ለቃ ሞተሯን ያጠፋችውን ላንድ ክሩዘር መኪና ክላሽንኮቭ የታጠቁ ታጣቂዎች ከበዋታል፡፡ መኪናዋ ውስጥ ከኋላ ተቀምጦ የነበረው ነጭ ሰውዩ ወርዶ ከጠባቂዎች አለቃ ጋር ለብቻ ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሜሮዳ ተመልሶ «ጓዝሽንና ሰዎችሽን ይዘሽ መምጣት ትችያለሽ አሁን» አላት፡፡

ሜሮዳ በፍጥነት ወደነ ሚራዥ ከመጣች በኋላ ይዛቸው ሄደችና መኪናዋ ውስጥ ገቡ፡፡ መኪናዋ ፊቷን መልሳ ወደ መጣችበት ሽመጠጠች፡፡

ሜሮዳ የሲ.አይ.ኤ ሰላይ መሆንዋን ያወቁት ሱዳን ካርቱም ከተማ ውስጥ በተከራዩችላቸው አነስተኛ ቤት ለሳምንታት ከቆዩ በኋላ ነበር፡፡

በሞቃታማዋ ካርቱም ከተማ ውስጥ ለወራት ከቆዩ በኋላ በሜሮዳ እገዛ አሜሪካን ሀገር ገብተው ሁለቱም የሎሳንጀለስ ከተማ ነዋሪዎች ሆኑ፡፡

ዣንጊዳ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ማስረጃውን አገኘ፡፡ ሚራዥም በሎሳንጀለስ ከተማ ደቡባዊ ምዕራብ ዳርቻ በአትክልተኝነት ተቀጥሮ ከቆየ በኋላ ዣንጊዳ በህክምና ሙያው ስለተቀጠረ በእርሱ እርዳታ ትምህርት ቤት ገባ፡፡

ትምህርቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቁ ምክንያት የሆነው ቀድሞ የተማረው የገዳሙ ውስጥ የአብነት ትምህርት ሲሆን ከዓመታት በኋላ ለተመረቀበት የህክምና ሙያ መንስኤ የሆነውም በውትድርናው ወራት ያየው የቁስለኞች ሥቃይ ነው፡፡



ዶ/ር ሚራዥ እሉ ከተባሉ ሰርጂኖች ተራ ለመመደብ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ከዶ/ር ዣንጊዳ ጋር ግንኙነታቸው እስከአሁን አልተቋረጠም፡፡ ዶ/ር ዣንጊዳ ወደ ሚሠራበት በቴክሳስ ግዛት ውስጥ ወደ ሚገኘው አውስቲን የህክምና ማዕከል ብቅ እያለም ይጠይቀዋል፡፡

ሜሮዳ አልፎ አልፎ እየመጣች ትጠይቀዋለች፡፡ በዚህ አፓርታማ ስምንተኛ ፎቅ ላይ የሚንሳፈፈውን የዝምታ መንፈስ የምትሰብረው ሜሮዳ ናት፡፡ ሰሞኑን ግን ጥፍት ብላለች፡፡

ዶ/ር ሚራዥ ልብሱን አውልቆ በቁም መስታወቱ ውስጥ ከተገተረው ምስሉ ላይ አንገቱን የኋሊት ጠምዝዞ የጀርባውን ንቅሳት ሲመለከት ብዙ ቆይቶአል፡፡ «ዴርቶጋዳ» ምንድን ነው?» ይላል ለብቻውን፡፡ «ለምንስ እኔ ላይና ኢንጂነር ሻጊዝ ጀርባ ላይ የተሳለው ንቅሳት አንድ አይነት ሆነ.... አይቲንክ.... ዊ ሃቭ ሳምቲንግ ኢን ከመን!.....አንድ የጋራ ምስጢር ከጀርባችን ሳይኖር አይቀርም»

ስለንቅሳቱ ሲያስብ ከቆየ በኋላ መልሶ ደግሞ ስለ ኢንጂነር ሻጊዝ የልብ ህመም ማሰብ ጀመረ፡፡

«እነዚህን ሁለት ምስጢሮች መፍታት አለብኝ፡፡» ብሎ ብቻውን እየተነጋገረ እያለ ስልኩ ተንጫረረ፡፡

«ሃሎ?»

«ጤና ይስጥልኝ ዶ/ር ሚራዥ፡፡»

«ጤና ይስጥልኝ ኢንጂነር ሻጊዝ» አለ ሚራዥ ሲጠብቀው በመደወሉ ተደስቶ፡፡

«በ101ኛ መንገድ ቁልቁል እየነዳሁ ነው፡፡ ከነገርኩህ ቦታ እጠብቅሃለሁ፡፡»

«መጣሁ ኢንጂነር፡፡ መጣሁ....» ፈጥኖ ስልኩን ዘግቶ መለባበስ ጀመረ፡፡ ሚራዥ ሁሌም እንደሚያዘወትረው ሰማያዊ ጅንስ ሱሪና ነጭ ቲሸረት ከለበሰ በኋላ ፎቁን በአሳንሰር ወረደ፡፡ ሰማያዊ ኘራዶዋን መኪና አስነስቶ ወደ 101ኛ አውራ ጐዳና አሳብሮ ገባ፡፡

# ፬

## ሎሳንጀለስ ፡ ሳንታሞኒካ መናፈሻ

ጀምበሯ በፓስፊክ ውቅያኖስ ሰማይ ጠርዝ ላይ ፍም መስላለች:: የፀሐይዋ ወርቃማ እግሮች የውቅያኖሱን ውሃ የቀለጠ ወርቅ አስመስለውታል:: ዝናቡ ላይ የሚዋልል የወርቅ ውሃ ይመስላል:: የውቅያኖሱ ወርቃማ ማዕበል ግድግዳ መስሎ ይመጣና ከባህሩ ዳርቻ ላይ ሲደርስ አሸዋው ላይ ዕርቃናቸውን ከሚንከባለሉት ልጃገረዶች ጀርባ ላይ ብትን ብሎ ይመለሳል::

ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ዳርቻ ያለችው 'ሳንታ ሞኒካ መናፈሻ በልጃገረዶችና በኮበሌዎች ሳቅ ደምቃለች:: ዓይንን ቆንጥጦ ቀልብን አሟጦ የሚይዘው የሴቶች ዕርቃን ገላ ላይ ዓይናቸውን የሚያንከባልሉ ጎረምሶች ጨዋታቸውን አድርተውታል::

ዶ/ር ሚራዥና ኢንጂነር ሻጊዝ እርቃናቸውን በአሸዋው ላይ በሚፈነድቁ ሴቶችና ጥንዶች የተሞላውን የባህር ዳርቻ ትርኢት የዘነጉት ይመስላሉ:: አእምሮአቸው በአንድ የጋራ ጉዳያቸው ላይ ተወጥሯል:: አብሯቸው አንድ ነጭ ሰውዩ ተቀምጧል:: ሰውየው ከወየበ ጥርሱና መፃጉዕ ከመሰለ ገፆታው ጋር ቅጥነቱ ተዳምሮ መቃብር ፈንቅሎ የተነሳ አስክሬን ይመስላል:: ላለፉት አሥራ ሰባት አመታት በተሰማራበት የንቅሳት ሙያ የታወቀና ትርፋማ የሆነ ሰው ነው:: ሲናገር ፈጣን ነው::

ወዲያው አንዲት ነጭ ካዲላክ መኪና በፍጥነት መጥታ እንደቆመች አራት ጥቁዋቁር የለበሱ ሰዎች ወደ መናፈሻው ገብተው ተቀመጡ:: አንደኛው ዓይኖቹን ሚራዥና ሻጊዝ ላይ ተክሎ ክንዱ ላይ እንደ ሰአት ባሰረው መነጋገሪያ በፍጥነት ያንሾካሾካል::

የራሺያ ዘይቤ ባለው እንግሊዝኛ «ታቃላችሁ?» አለ የንቅሳት ባለሙያው:: «አሜሪካ የንቅሳት ዲዛይን ማዕከል ነች:: በተለይም በ1891 ዓ.ም በኤሌክትሪክ ኃይል ለሚሠራ የመጀመሪያው የንቅሳት መሳሪያ የባለቤትነት መብት ከተሰጠ ወዲህ» ጉሮሮውን ቶሎ ቶሎ ይጠራርጋል:: ጉሮሮውን ጠራርጐ ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ:: «ብዙ የአሜሪካ የሀንድ ጐሳዎች በተለይ ሰውነታቸውንና ፊታቸውን ይነቀሳሉ:: ጥቂት ጐሳዎች በተለይ ሰውነታቸውንና ፊታቸውን ይነቀሳሉ:: የካሊፎርኒያ ጐሳዎችም በተለያዩ ቀለማት ቆዳቸውን ይነቀሳሉ:: በኒውዝላንድ የእሪ ጐሳዎች በአጥንት ስባሪ ፊታቸው ላይ የተጠ ማዘዘ ዲዛይን ያለው ንቅሳት ይነቀሳሉ:: በጃፓን የአየኑ ጐሳዎች፣ በናይጀሪያ የኢቦ ጐሳዎች፣ የአሪዞና ፒማ ህንዶችና የማላያ ሴኖዬ



ጐሳ አባላት በእሾህ ወይም በመርፌ መሰል መሳሪያዎች ይነቀሳሉ» ሁለቱም በንቃት ንግግሩን እያዳመጡት ነው::

«ታውቃላችሁ?» አለ ሲጋራውን ምጐ:: «ንቅሳት ከክርስቶስ ልደት በፊት በተቀበሩ የግብፃውያን ያልፈራረሱ ሬሳዎች ላይም ተገኝቷል:: የጥንታዊት ግሪክና የሮም ደራሲያን ግሪካውያን፣ ፈረንሳውያን፣ ጀርመናውያንና እንግሊዛውያን ንቅሳት ይጠቀሙ እንደነበር ፅፈዋል::»

«ለምን ጥቅም ነበር የሚነቀሱት?» አለ ሚራዥ ለረጅም ጊዜ ካዳመጠው በኋላ:: ለሻጊዝ ግን ንቅሳቱ ብዙም ግድ የሰጠው አይመስልም:: የዶ/ር ሚራዥን ስሜት በጥልቀት የሚመረምር ይመስላል::

«እኛጋ የሚነቀሱት ብዙዎቹ የፍቅረኞቻቸውንና የሚወዱትን ሰው ስም አንዳንዶች ደግሞ የተወለዱበትን ዓመተ ምህረትም ይነቀሳሉ:: እኛ የማናውቃቸው ዲዛይኖችንም ይነቀሳሉ::» ሲጋራው እጁ ላይ ሲያልቅ ሌላ ሲጋራ አቀጣጠለ::

«ሌላ በንቅሳት ዙሪያ የምታውቀው ምስጢር ይኖራል?» አለ ዶ/ር ሚራዥ:: ሁል ጊዜም ምስጢር የሆኑ ነገሮች ቀልቡን ይገዙታል:: 'በግልፅ ከማገኘው አልማዝ ይልቅ የተደበቀ ትርኪ ምርኪ ነገር ይመስጠኛል' ይላል ዘወትር::

«ሌላ?» ሲጋራውን እንደ እናት ጡት ምጥምጥ አድርጎ ጠብቶ:: «ሮማውያን ወንጀለኞችንና ባሮችን እንዲነቀሱ ያደርጉ ነበር::» ሁለቱም ተያዩ:: ሚራዥና ሻጊዝ:: «ወንጀለኞችና ባሮች ይነቀሱ ነበር? ወንጀለኞች ልንሆን አንችልም:: ባሪያ ፍንገላም ቆሟል:: ምናልባት ግን ከባሪያ ፍንገላ የመለጥን ቢሆንስ? በጃንሆይ ጊዜ የባሪያ ፍንገላ?» አለ ዶ/ር ሚራዥ በውስጡ::

ሰውየው ንግግሩን ቀጠለ:: «በእርግጥ አንዳራድ ሰዎች እኔ የማላውቃቸውን ምስጠራዊ ነገሮችን እንድነቅስላቸው ዲዛይን ሰርተው ይመጣሉ»

ዶ/ር ሚራዥ ቲሸርቱን ዝቅ አድርጐ የጀርባውን ንቅሳት ለነጬ ሰውዩ አሳየውና ወደ ቦታው መለሰው:: «ይህን ዓይነት ንቅሳት አይተህ ታውቃለህ?» አለው::

«እስቲ እስቲ መልሰህ አሳየኝ?» ሰውየው እንደቱርክ ዶሮ የተመለጠ የመሰለውን አንገቱን አስጐ ንቅሳቱን ለረጅም ጊዜ ተመለከተው:: «ዴርቶጋዳ» የማያውቀው ፊደል:: በ'ቶ' ፊደል ላይ የተቀረፁትን ውስብስብ ቁጥሮች እየተመለከተ «ይቅርታ ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም»አለ:: «ግን ተራ ነገር አይመስለኝም:: በንቅሳቱ ላይ ያሉት ቁጥሮች ምናልባት በዘፈቀደ የተቀመጠ አይመስለኝም:: በ'ቶ' ፊደል ላይ ያሉት ቁጥሮች ምናልባት አንድን ምስጢራዊ ነገር የሚያመለክቱ ይመስለኛል:: ምናልባት ንቅሳቱን የነቀሳችሁን ሰው ብታናግሩት የተሻለ ሳይሆን አይቀርም»

«የነቀሰን ሰውማ በህይወት የለም» አለ ሻጊዝ።

የሁለቱንም ተመሳሳይ የጀርባ ላይ ንቅሳት ካየ በኋላ አንገቱን እየነቀነቀ «አንድ የጋራ የሆነ ምስጢራዊ ነገር ሳይኖራችሁ አይቀርም።» ብሎ የጨረሰውን የሲጋራ ቁራጭ በጫማው መሬት ላይ ደፈጠጠው።

ሰውየው ኢንጂነር ሻጊዝን በአትኩሮት ይመለከተዋል ከዚህ በኋላ ከኢንጂነሩ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው መፈለጉን ዓይኖቹና አኳኋኑ ያሳብቃሉ። ኢንጂነር ሻጊዝ በንቅሳቱ ላይ እንደሚራኽ ትኩረት ቢሰጥ የበለጠ ቅርርቦሹን ማስፋት ይችል ነበር። ኢንጂነሩ ግን ለንቅሳቱ ደንታ የሌለው ይመስላል።

የንቅሳት ባለሙያውን ካሰናበቱት በኋላ ብቻቸውን ተቀምጠው ለየግላቸው ጥቂት አሰላሰሉ። «በነገራችን ላይ እኔ ድሮ ገዳሙ ውስጥ እያለሁ ስለኢትዮጵያውያን ንቅሳቶች አንድ መነኩሴ አጫውተውኝ ነበር።» አለ ሚራኽ ፀጥታውን ለመስበር።

«ምን ሲሉ አጫወቱህ?» አለ ሻጊዝ ከሃሳቡ ባንኖ።

«የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስቲያኖች የክርስትና ስማቸው እንዳይጠፋባቸው ሰውነታቸው ላይ ይነቀሱት ነበር። በድንገት በማይታወቁበት ቦታ ቢሞቱ ክርስቲያኖች መሆናቸው ታውቆ በፀሎተ ፍትሐት እንዲቀበሩ።» አለ ሚራኽ መነኩሴው ያጫወቱትን ለማስታወስ እያማጠ።

«አዎ።ሌላው የነገሩኝ ነገር .....ኢትዮጵያውያን ስሞቻቸውን በየዘመኑ ለዋውጠዋል። ለምሳሌ በዘመነ አሪት ስሞቻቸው ለየግላቸው ልዩ ልዩ ነበር። ማለትም አንዱ በአንዱ ስም አይጠራም ነበር። ለምሳሌ 'አብርሃም' 'አብርሃም' ነው። በዚህ በኛ ዘመን ግን ብዙ አብርሃም የሚባሉ ሰዎችን እናውቃለን። እኔ አንድ ሰው 'አብርሃም' ተብሎ ሲጠራ ትዝ የሚለኝ የመፅሐፍ ቅዱሱ አብርሃም ነው። ዋናው ቁም ነገራችን ግን ስለንቅሳቱ ነው።»

«እሺ ንቅሳቱን በተመለከተ ሌላ ምን ነበር የነገሩህ?»

«ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሲጠመቁ ደግሞ የክርስትና ስም ወጣላቸው። ለምሳሌ ገብረ ኢየሱስ፣ ወለተ ማርያም እየተባሉ ይጠሩ ጀመር። በኋላ ደግሞ የሐይማኖት ግጭት ሲነሳ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስቲያኖች በስማቸው እየታደኑ ይገደሉ ጀመር። በዚህ የተነሳ የክርስትና ስማቸውን በንቅሳት ሰውነታቸው ላይ በመደበቅ አበበ፣ ከበደ፣ ወዘተረፈ እየተባሉ መጠራት ጀመሩ። አሁን ያለንበት ትውልድ መጠሪያ ስሙን ያገኘውም ከዚህ ሂደት በኋላ ነው። ስለዚህ ንቅሳት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ትርጉም ያለው ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በነፃነት እምነታቸውን ማራመድ ባልቻሉበት ወቅት የክርስትና ስማቸውን በንቅሳት የሚደብቁበትን ያህል ሌሎች ምስጢሮችንም በንቅሳት ማስቀመጥ እንደሚችሉ መገመት ቀላል ነው።» ሚራኽ ነገሮችን ሁሉ ከእርሱ ንቅሳት ጋር



ለማገናኘት ቢጥርም ስለነሱ ንቅሳት ጠብ የሚል ነገር ሊያገኝ አልቻለም።

«ስለመሃለኛው ፊደል ስለ 'ቶ' የምታውቀው ነገር ይኖራል? ምናልባት ፊደል በፊደል ማየቱ ሳይሻል አይቀርም።» አለ ሻጊዝ እንደገነበር ጠልቀው የሚያዩ ዓይኖቹን ወደ ሚራኽ ቀስሮ።

ስለ 'ቶ' ፊደል አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ማንበቤን አስታውሳለሁ።» አለ ሚራኽ ጥንታዊውን መጽሐፍ እያስታወሰ። «እንደ መጽሐፉ 'ቶ' ፊደል ሰውንና ክርስቶስን ይወክላል። በአጭሩ 'ቶ' ፊደል የህይወት ምልክት ነው። በመካከለኛው ጥንታዊት ኢትዮጵያ በካራን የፀሐይ አምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ የምሥራቁ ግድግዳ ከአልማዝና ከዕንቁ፣ ከእምራልድና ከወርቅ እንዲሁም በተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች ያሸበረቀ እንደ ነበር ተጽፏል። ከዚህ በታች ደግሞ የሁለት ሴት አናብስት ቅርፅ አለ። ከላያቸው መሃሉ የህይወት ምልክት የሆነ 'ቶ' ፊደል ያለበት ፀሐይ ተስሏል። መጽሐፉ 'ቶ' ፊደል የመጀመሪያው ሰውንና ክርስቶስን የሚወክለው የህይወት ምልክት መሆኑን ያስረዳል»

«በነገራችን ላይ ሳንድ የቴክኖሎጂ ስብሰባ ባንድ ወቀት ግብፅ ሄጄ ነበር። አንዳንድ ጥንታዊ መካናትን ስጎበኝ ይህን ፊደል ያየሁት ይመስለኛል» አለ ኢንጂነር ሻጊዝ ጉብኝቱን እያስታወሰ።

«አዎ። ልታየው ትችላለህ። ምክንያቱም ዛሬ ታሪክ ከመገልበጡ በፊት ግብፅ የኢትዮጵያ ልጅ ነበረች። እንዲያውም ግብፃውያን በአንድ ዘመን ኢትዮጵያውያንን ያመልኩ ነበር። የጥንት ግብፃውያን ኬሜቶች የአባይ ወንዝ ምንጭ ከጨረቃ ተራሮች ሥር እንደሆነና ኢትዮጵያም የአማልክት ምድር እንደሆነች ያምኑ ነበር። የፒራሚድ አሠራርን፣ የቤተመቅደስ አሠራርን፣ ስነ ፈለክንና ሌሎች ጥበባትን ከኢትዮጵያውያን አማልክቶቻቸውና ከግብፅ በስተደቡብ ከሚኖሩ ህዝቦች እንደተማሩ በሂሮግሊፊክስ ስዕላዊ ጽሑፎችና በታሪክ ፀሐፊዎችም ከትበውታል። በእርግጥም አንተ እንዳየኸው በግድግዳ ስዕሎቻቸው ላይ አማልክቱ በእጆቻቸው የሚይዙት ልዩ የህይወት ምልክት የሆነው 'ቶ' ፊደል ምንጭ ከጨረቃ ተራሮች ሥር ካለችው የአማልክቱ ምድር ኢትዮጵያ ነች።»

«እንዳልከው ይህ ምልክት ከኢትዮጵያ ፊደሎች አንዱ ነው። ከክርስቶስ ልደት በኋላም ከመስቀል አይነቶች እንደ አንዱ ሆኖ መወሰዱን እኔም አውቃለሁ። በተለይም በወሎና በበጌምድር የሚገኙ ሴቶች ይህንን ምልክት በግንባራቸው ላይ ይነቀሱታል» ኢንጂነር ሻጊዝም የሚያውቀውን አከለበት።

«ያም ሆነ ይህ በእኛ ንቅሳት ላይ ያለው 'ቶ' ግን በሌሎች ነገሮች የተሞላ ነው። ቁልፍ ነገር ይመስለኛል» አለ ሚራኽ የፊደሉ ቅርጽ ወደ ቁልፍነት ማዘንበሉን እያየ።

«ምናልባት ያንድ ምስጢራዊ ነገር ቁልፍ ይመስለኛል።»

«ሌሎች ፊደላትስ?»

«በጥቅሉ ዴርቶጋዳ የሚለው ቃል ስለዚህ ምስጢራዊ ነገር ብዙ መረጃዎችን የያዘ ይመስለኛል»

ይህንንና ሌሎች መሠረታዊ ነገሮችን ሲጨዋወቱ ከቆዩ በኋላ ስለ ኢንጂነር ሻጊዝ የጤንነት ጉዳይ መነጋገር ቀጠሉ።

«ጤንነትህ እንዴት ነው አሁን እየተመለሰ ነው?» አለ ዶ/ር ሚራዥ በረጅሙ ተንፍሶ።

«እያገገምኩ ነው። ግን ያው ከሁለት ወር በኋላ መልሼ መቀደዴ የማይቀር ጉዳይ ነው። የልቤ ጉዳይ ዘላቂ መፍትሔ እስካላገኝ ድረስ ስቀደድ ስሰፋ መኖር እጣ ፈንታዬ ነው።»

«ኢንጂነር» አለ ሚራዥ በትካዜ። «በዚህ ወቅት ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ማከናወን እፈልጋለሁ።»

«ምን ምን ነገሮችን?» ሲል አንጂነር ሻጊዝ ጠየቀው።

«አንደኛ የአንተን የልብ ችግር መፍታት እፈልጋለሁ። የዚያችን ደሀ ሀገር ችግር ለመፍታት በተነሳሀበት ወቅት የገጠመህ አስቸጋሪ ጉዳይ የግልህ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቷን እንወዳለን የሚሉትንም ይመለከታል። ለአሜሪካ የሠራኸውን ሩቡን ያህል እንኳ ያች ደሀ ሀገር ትፈልጋለች። ሀገሪቷን የረቀቀ ቴክኖሎጂ ባለቤት ማድረግ የሚቻለው እንዳንተ ያሉ የቴክኖሎጂ ሰዎች ተባብረው ከተነሱላት ነው። እስራኤልን መልሰው በ1948 የገነቧት ሰዎች ጥቂት ሀገራቸውንና ህዝባቸውን የሚወዱ ጽዮናውያን ናቸው። ለውጥ ለማምጣት ብዛት ብቻ ሳይሆን ቁርጠኛ አቋም ያላቸው ጥቂት ሰዎች በቂ ናቸው። አንተ ደግሞ ቁርጠኛ አቋም ካላቸው ሰዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ ነህ። ወንጌልን ለአለም ይሰብኩ ዘንድ ኢየሱስ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርት አሥራ ሁለት ብቻ ናቸው። ኢትዮጵያን መልሶ ለመገንባትም ግዴታ ሚሊዮኖች አያስፈልጉም። ጥቂት ቁርጠኞች በቂ ናቸው። ጥቂት ቁርጠኞች ሚሊዮኖችን ከኋላቸው ያስልፋሉ። ስለዚህ አንተን ማዳን አንዱ ጉዳዬ ነው። ሁለተኛው ዋና ጉዳይ ደግሞ የንቅሳታችን ምስጢር ማፈላለግ ነው።»

በልቡ የያዘው ግን ሌላ ልዩ ጉዳይ አለው። ሲጳራን መፈለግ። ግን ወዴት ብሎ እንደሚፈልጋት ግራግብት ብሎታል። ሞኝ ያስመስለኛል ብሎ ባይተወው ኑሮ ማስታወቂያ ለማስነገርም አስቦ ነበር። «በዓለም ላይ ከ6 ቢሊዮን በላይ ህዝብ ነው ያለው። ሴቶችም ከግማሽ በላይ ይሆናሉ። ከዚህ መሃል ሲጳራን እንዴት ልታገኛት ትችላለህ?» ብሎት ነበር አንድ ቀን ገቨንጊዳ። እሱ ግን ልቡ ቀርጦለት ረስቶአት አያውቅም።

«ለማንኛውም ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ። ራስህን በጥንቃቄ ያዘው። በማስተዋል ሁሉንም እናደርገዋለን።»አለ ሻጊዝ። «...ማስተዋል ይጋርድሃል ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ይላል ቅዱስ መፅሐፍ።»

እየተነጋገሩ ወደ መኪኖቻቸው ሲገቡ ጥቋቁር መነፅር አድርገው ተቀምጠው የነበሩት ሰዎችም ወደ መኪኖቻቸው ገብተው ተከተሏቸው።



ዶ/ር ሚራዥ ከኢንጂነር ሻጊዝ ተለይቶ ወደ ቤቱ ሲጓዝ አራቱን ሰዎች የያዘችው ነጭዋ ካዲላክ መኪና እየተከተለችው ነበር። በ101ኛው አውራ ጎዳና ተገንጥሎ ወደ አፓርታማው በሚወስደው መንገድ ሲታጠፍም ነጭዋ ካዲላክም አብራው ታጠፈች። መኪናውን ለማሳለፍ ፍጥነቱን ሲቀንስ ካዲላኩም ፍጥነቱን ቀንሶ ከኋላው ተከተለው። መኪናው ውስጥ ያሉትን ሰዎች በጉን መስታወቱ ለማየት ቢጥርም ሊለያቸው አልቻለም።

ወደቤቱ እንደገባ በመስኮቱ በኩል ቁልቁል ካዲላክዋን እየተመለከተ እያለ ከአፓርታማው መኪና ማቆሚያ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ። መኪናው ውስጥ ቦንብ ተጠምዶ እንደነበር ሲያውቅ በድንጋጤ ተንቀጠቀጠ። ወዲያው አካባቢው በፖሊስ መኪና ድምጽ ተዋጠ።

ካዲላክዋ ከአካባቢው ከተሰወረች ከደቂቃዎች በኋላ ፖሊሶች ሚራዥን በጥያቄ ያጣድፉት ጀመር።

«ስለተፈጠረው ነገር የምታውቀው ነገር አለ?»

«በፍፁም የማውቀው ነገር የለም።»

«ግባ።»

«የት ነው የምገባው?»

«ቃልህን መስጠት አለብህ።»

«የምን ቃል ነው ምሰጣችሁ?»

«ሁሉንም ነገር በኋላ እንነጋገራለን። ቃልህን ልትሰጥ ይገባል።»

ሰማያዊና ቀይ ቀይ ጨረር የሚተፋት የፖሊስ መኪናዎች ሚራዥን ይዘው ተወነጨፉ።

# ፳

ዶክተር ሚራዥ ለፖሊስ ቃሉን ሰጥቶ ከተመለሰ በኋላ ከወደሜት እንደተሳበ የማያውቀውን ደብዳቤ ኢንቨሎፑን ከመቅደዱ በፊት ለዶክተር ገርንጊዳ ስልክ ደወለ:: ከሥራም ስለተፈናቀለ ወደ እስቲን ሄዶ ከዶክተር ገርንጊዳ ጋር ለመሥራት አስቧል::

«ሃሎ» አለ ሚራዥ::

«ጤና ይስጥልኝ! እስቲን የህክምና ማዕከል?»

«አዎ ጤና ይስጥልኝ:: ምን እንርዳዎ?» የሴት ድምፅ መለሰለት::

«ዶ/ር ገርንጊዳን ነበር እባክዎ?» ሲል ጠየቀ ሚራዥ::

«ተሳስተዋል ጌታዬ::» አለች ሴቷ ከወዲያኛው ጫፍ

«ይህ ቴክሳስ ውስጥ ያለው እስቲን የህክምና ማዕከል አይደለም?»

«ነው ጌታዬ:: ግን ዶክተር ገርንጊዳ ወደ ሥራ ከገቡ ሁለት ወር አልፏቸዋል» አለች ሴትየዋ:: «ይህን አገር የሰማውን ጉዳይ አላወቁም እስከአሁን? ዜና አያዳምጡም ማለት ነው::» ቀጥላ የተናገረችውን ማመን አቃተው:: በድንጋጤ ደንግዞ የስልኩን እጀታ በቀስታ ዘጋው::

«የፈጣሪ ያለህ!» አለ ሚራዥ ከው ብሎ::

ከሁለት ወር በፊት የተላለፈ ዜና ይደገምለት ይመስል ጠረጴዛው ላይ የርቀት መቆጣጠሪያውን አንስቶ ቴሌቪዥኑን ከፈተው:: እየተላለፈ የነበረው የጡት ማስያዣ ማስታወቂያ ነበር:: ጡት ማስያዣውን የምታስተዋውቀው ሴት ገርንጊዳን የዋጠችበት ይመስል አፍጦ ቴሌቪዥኑ ውስጥ ተመለከታት:: ሰርቃንዋን ቆማ የጡት ማስያዣውን ከክብ ጡቶቿ ላይ አውልቃ አንሶላ ውስጥ ወደሚጠብቃት ወንድ ስትሄድ ወንዱ ደግሞ ከአንሶላው ውስጥ ወጣ ብሎ አልጋው ላይ የጣለችውን ጡት ማስያዣ ባዶ ደረቱ ላይ ለብሶ እየሳቀ ወደ አንሶላው ውስጥ ይዟት እስኪጠልቅ ማስታወቂያውን ቆሞ በመመልከት በራሱ ተገረመ::

የላኪ አድራሻ የሌለውን ደብዳቤ ኢንቨሎፕ ቀዶ ውስጥ ያለውን መልእክት ሊያነብ ሰፍ ብሎ ሲመለከት ከባዶ ወረቀት ጋር ተፋጠጠ:: «ባዶ ወረቀት?» ሲል ብቻውን ጮኸ:: «ማነው ሊያሳብደኝ የሚጣጣር!» ጠረጴዛውን በቡጢ ነርቶ ከጥጉ ያለውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ:: ተደርድረው ቤቱን የሞሉት መፃሕፍቱ ያናግሩት ይመስል ዓይኑን አንቀዋለለባቸው::

በሰማው አንድ አስደንጋጭ ዜና ዓይኖቹን ከመጻህፍቱ መደርደሪያ ላይ ነቅሎ ከቴሌቪዥኑ ስክሪን ላይ ወረወራቸው::



ቅብጥብጧ ሴት ጋዜጠኛ ጡቶቿን በከፊል አጋልጦ በሚያሳይ ጥቁር ልብስ ከታጀለው ደረቷ በላይ ያለውን አጭር አንገቷን ሰበር ሰካ እያደረገች የምታነበንበውን ዜና ማመን አልቻለም::

«በትናንትናው ምሽት እውቁ የንቅሳት ባለሙያ ሚስተር ጆንስ መኪናው ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ ህይወቱ አለፈ:: ሚስተር ጆንስ ላለፉት አስራ ሰባት አመታት በንቅሳት ሞያ ተሰማርቶ የኖረ ትርፋማ ሰው ሲሆን ትናንት አመሻሹ ላይ በሎሳንጀለስ ከተማ ዳርቻ በምትገኘው ሳንታ ሞኒካ መናፈሻ ከሁለት ሰዎች ጋር ሲዝናና አምሽቶ ወደ ሥራ ቦታው ሲመለስ መኪና ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ ህይወቱ ማለፉን ፖሊስ ገልጿል:: አብረውት ከነበሩት ሰዎች በአንደኛው ዶክተር ሚራዥ በሚባል ሰው መኪና ውስጥም የተጠመደ ፈንጂ ፈንድቶ ቃጠሎ እንዳስነሳ ሲገለፅ ዶክተሩ ከመኪናው ከወጣ በኋላ ቦንቡ በመፈንዳቱ ከህይወት ሊተርፍ ችሏል:: ቦንቡን ያጠመዱትን ሰዎች ይዞ ለፍርድ እንደሚያቀርብ ፖሊስ የገለፀ ሲሆን ህብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግም አያይዞ ገልጿል::»

ዜናው እንዳበቃ ላቡ በግንባሩ ጭርር ሲል በመዳፉ ሞዥቆ አገጩን በእጁ አስደግፎ በድንጋጤ ተዋጠ::

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?» ራሱን ጠየቀ:: «ማነው እያጠመደኝ ያለው? ለምን የንቅሳት ባለሙያውስ ተገደለ? እኔንስ ማነው ቦንቡን ያጠመደው?» ድምፁ ከጣራ በላይ እስኪሰማ ድረስ ብቻውን እየጮኸ ነበር::

«እጅህ የማትችለውን ጉዳይ እየነካካ እንደሆነ አላወቅህም? ሚስተር ሚራዥ!» ሲል ከኋላው የሚናገር ድምጽ ሰምቶ ሲዞር ጥቁር ጭምብል ለብሶ ሽጉጥ ካነጣጠረበት ሰው ጋር ተፋጠጠ:: ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ «ምን?» አለ ዶክተር ሚራዥ::

«አዎ:: ጉረኛ ነህ:: ጤና ያጣህ ዶክተር!» ጣቱን ወደ ምላጩ ላከው::

«ምን እንደምትል አልገባኝም:: የያዝከውን ነገር መለስ አድርገውና ብንነጋገር የተሻለ ነው» አለ ዶ/ር ሚራዥ ጭንብሉ ውስጥ ያለውን ገጸ ሊያረጋጋ::

«በሽተኛ ሰው መሆንህ እየገባኝ ነው:: በሽተኞች በሽተኞችን ለማዳን ሲነሱ ማየት ትልቁ የአለማችን አስቂኝ ቀልድ ነው::»

«እየውልህ ...ለምን አንግባባም::»

«እንዳትንቀሳቀስ:: ባለህበት::»

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?»

«እንደዚህ:: ይሄው እጅህን በእጅህ ልትቆርጥ የቀረህ የእኔ ጣት ምላጩን እስኪስብ መጠበቅ ብቻ ነው:: ግን ይህ ቂልነትህ

በገሃነም ውስጥም የሚያኖርህ አይመስለኝም። በገሃነም ውስጥ ያሉት እንዳንተ ያሉት ቂሎች አይደሉም።»

«እየውልህ ....»

«ዝም በል! ለመሆኑ ኢንጂነሩ ያስፈለጋችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠምዳችሁ ልታርሱት ነው? የምንረዳችሁ ገንዘብ ለእህያ መግገር አይበቃችሁም? አርፋችሁ በአህያችሁ አታርሱም? መልካም ጉዞ ሐኪምና ታካሚ ወደ ሌለበት ገሃነም በሽተኛው ዶክተር...» ብሎ የሽጉጡን ምላጭ ሊስብ ሲል በአፍጢሙ ተደፋ። የድምፅ ማፈኛ በተገጠመለት ሽጉጥ ጭንብል ያጠለቀውን ገዳይ መትታ የጣለችው ሜሮዳን ከኋላ ቆማ ሲያያት ከሰማይ የወረደች መልአክ መሰለችው። ገዳዩ በግንባሩ ወለሉ ላይ እንደተደፋ ከጀርባው በልቡ ትክክል ደገመችው።

በድንጋጤ ተራምዳ ሚራዥን አቀፈችውና «ቶሎ መውጣት አለብን» አለችው። «የምትፈልገውን ጓዝ ቶሎ ቶሎ እንጫን።»

«መኪናዬ እኮ ተቃጥሏል። አልሰማሽም?» አላት ሚራዥ ከደረቱ ተጠግታ እንዳቀፈችው።

«እሱን አውቃለሁ» አለችው። «የጭነት መኪና ይገኝ መጥቻለሁ።»

«ይህ እንደሚሆን ታውቂ ነበር እንዴ?» አላት የሲ.አይ.ኤ ኤጀንት መሆንዋን የዘነጋው ይመስል።

«እንዴት አላውቅም?» አለችው አስገርሟት።

«እነማን ናቸው እነዚህ ሰዎች?»

«ሲ.አይ.ኤዎች።»

«ቆይ እንዴት?»

«ከዛ ሰውዬ ጋር በጀመርከው ጉዳይ ነዋ!»

«ከማን ጋር?»

«ሁለት ነገር ልንገርህ። አንደኛው ... የኢንጂነር ሻጊዝን የልብ ቀዶጥገና ምስጢር ማነፍነፍ ጀመርክ። ሁለተኛው ከሆስፒታሉ ብትባረርም ከኢንጂነሩ ጋር ብዙ ጊዜ አብረህ ታየህ። ስለዚህም ሊያስቆሙህ ፈለጉ። እንድትወገድ ተወሰነ።»

«የንቅሳቱ ባለሙያ ግድያስ በምን ምክንያት ነው?»

«ከሩሲያ ደህንነቶች ጋር ግንኙነት ነበረው። ወደናንተ ከመምጣቱ በፊት ከራሺያዎች ጋር በአንድ ነገር ላይ እንደተደራደረ ሲ.አይ.ኤ ደርሶበታል።»

«ምንድን ነው የተደራደረው?»

«የራሺያ የቴክኖሎጂ ሰላዮች የንቅሳት ባለሙያው ከሻጊዝ ጋር ግንኙነት እንዳለው ካወቁ በኋላ ኢንጂነሩን ጠልፈው ወደራሺያ ለመውሰድ እንዲረዳቸው ጠቀም ያለ ገንዘብ ሰጥተውታል። የንቅሳቱ ባለሙያ ደግሞ በትውልድ ሩሲያዊ ነው። ስለዚህ እንዲወገድ



ተወሰነበት። በነገራችን ላይ እንድትወገዱ የተወሰነባችሁ ሁለታችሁ ብቻ አይደላችሁም።»

«ደግሞ ሌላም አለ?»

«ሌሎችም አሉ። ህንዶች፣ ፓኪስታኖች፣ ጃፓኖች፣ እስራኤሎች፣ ቻይናዎች፣ ኢራኖች... እሱን ለመውሰድ እያንዣበቡ ነው። የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎችም እየተከታተሉት ነው።»

«የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች?»

«አዎ። የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች።»

«ለምንድን ነው የሚፈልጉት እነሱ ደሞ?»

«ሊያስወግዱት ይፈልጋሉ።»

«የፈጣሪ ያለህ! ... ለምን?»

«ሰውየው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እጁን አስገብቷል።»

«እና ቢያስገባስ ሀገሩ አይደለች እንዴ?» አለ ሚራዥ ደንግጦ። «ደግሞ እኮ አባብለው ሊይዙት የሚገባ ሰው ነው። ምንም አይነት የፖለቲካ አመለካከት ይኑረው ሀገሪቷ ተቀብላ እውቀቱን መጠቀም አለባት። አመለካከቱ የግሉ ነው። የዚህን ሰው የቴክኖሎጂ እውቀት ለማግኘት የአለማችን ሀገራት የማያድኑት ከእሱ ፍቅር ይዟቸው ነው እንዴ ድሮስ? እንዴት ሀገሩ በሯን ትዘጋበታለች? እንዴት የሀገሩ ልጆች ለመግደል ያድኑታል?» ገነፈለ።

«አልገባህም በቃ» አለችው ሜሮዳ። ደረቅ ፈገግታዋን እያሳየችው።

«የጀመረው የፖለቲካ ትግል ሰላማዊ ትግል አይደለም። ጦርነት አውጇል። ይህን ነው እያልኩህ ያለሁት።»

«አይምሰልሽ። ሰውየውን ቀርቤ አይቸዋለሁ።» አለ ሚራዥ ድምፁን ለዘብ አድርጎ።.... «የጦረኝነት ስሜት ውስጡ የለም።»

«ውስጡ ባይኖርም በጥጉ ያሉ ሰዎች የገፋፉት ይመስለኛል።»

«ቢሆንም..... መወገድ የለበትም። ሀገሪቱ የመንኩራኩር ማምጠቂያ ጣቢያና የረቀቀ የቴክኖሎጂ ማዕከል ባይኖራትም በሳተላይትና በዘመናዊ ራዳር ያለው እውቀቱን ልትጠቀምበት ይገባታል። እስኪ አስቢው ይህ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ መቶ ሰው ቢያሰለጥን እንኳ ራሱን አባዝቶ አገሪቷን በቴክኖሎጂ ማበልፀግ አይችልም? በዛ ላይ ገንዘብ ያለው ሰው ነው። የረቀቁ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ወደሀገሩ እንዲያስገባ መጐትጐት ሲገባ ማሳደድ?»

«አሁንም ያልገባህ ነገር አለ።»

«ሳይገባኝ ይቅር አልኩሽኮ።»

«ያም ሆነ ይህ አሜሪካ ትፈልገዋለች። ከህዋ ምርምሯ ጀርባ ሌላ ሀገራዊ ምስጢር ይዟል። የረዥም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎቿ፣የራዳሮቿ፤የሳተላይቶቿ፤ የቴክኖሎጂ ምርምር ጣቢያዎቿ ሌሎችም ወታደራዊና ሳይንሳዊ ምስጢሮቿ በእጁ እንደመሆናቸው

መጠን ትጠብቀዋለች:: ዓይን የሚያዩና ጭልፊቶች ሁሌም በዙሪያው ያንዣብባሉ:: ከኢትዮጵያም ሆነ ከማንም ሀገር ሰው፣ ገዳዩም ሆነ ወዳጅ ጋር ከተገናኘ እንደሁኔታው ያገኘው ሰው እስጊ ከሆነ ይወገዳል:: አንተ ግን አመለጥክ:: በንቡ ከመኪናህ ከወጣህ በኋላ ለምን እንደፈነዳ ታውቃለህ፧ ...ክንተ መኪና ውስጥ የተጠመደው በንብ መቆጣጠሪያ በእጁ ገባ:: በነጨ ካዲላክ ከሚከታተሉህ ሰዎች ጅርባ መኪናዋ ውስጥ ሆኜ እየተከታተልኩህ ነበር:: ከመኪናህ ወጥተህ ስምንተኛ ፎቅ ላይ ሳይህ አፈነዳሁት::» ይህን በማድረጓ ምናልባት ከሲአይኤ የሚጠብቃት አደጋ እንዳለ ብታውቅም ሲሞት ዝም ማለት አልቻለችም፤ ትወደዋለች::

«ወጥ ቤቷ ሚሮዳ መቼም አንቺ እኮ አስገራሚ ሰው ነሽ» አላት:: «ከጦር ካምፑ አትዮጵያ ውስጥ ጀምሮ ህይወቴን እየታደግሽልኝ ነው::» ይህን እየተነጋገሩ ኢቃውን እየሸከፉ ነበር::

«ከሁሉም በላይ» አለ ሚራጎ:: «መፃሕፍቶቼን ጥዬ ወደ የትም ንቅንቅ አልልም::»

«የተወሰኑትን ብቻ ምረጥና እንሂድ ይልቅ ሁሉን ማግበስበስ አያስፈልግህም::»

«በፍፁም አላደርገውም:: የምመርጠው መጽሐፍ የለም:: ሁሉም መጻሕፍት ባለውለታዎቼ ናቸው:: መጻሕፍቶቼ ስንት ረጃጅም ቀኖችንና ጀግጃጋ ሌሊቶችን አሳጥረውልኛል መሰለሽ!»

«ሌላ መርሳት የሌለብህ ነገር አለ?» አለችው ዓዙን ሁሉ ጠቅልለው መኪና ማቆሚያው ውስጥ ከቆመችው መኪና ውስጥ ከጫኑ በኋላ::

«አዎ:: ጊታሬን ረስቼዋለሁ:: ጊታሮቼን!»

«ጊታሮቼን?» ስትል ጠየቀችው:: «ደሞ ስንት ሆኑ? »

«ባለፈው ቀን አንድ ኢትዮጵያዊ ሽማግሌ ሰውዬ ሌላ ጊታር ሰጠኝ:: አልነገርኩሽም ለካ:: ሰውየው ሁል ጊዜ በፓስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ ጊታር ስጫወት እየመጣ ይመለከተኝ ነበር:: ባለፈው ከአንድ ሳምንት በፊት የጊታር ስጦታ አበረከተልኝ:: ምንድን ነበር ያለኝ?» ሲል ራሱን ጠየቀ::

«ምን አለህ?» አለችው ሰቃውን መኪናው ላይ እያመቻቸች::

«አዎ:: እንዲህ ነው ያለኝ:: 'እስከ ህይወትህ ፍፃሜ ጊታሩን አትጣልብኝ አደራ:: ጊታሩን አትጣለው:: ለሌላ ሰውም አትስጥ:: በህይወቴ ሁሉ እንደዚህ ያለ ስጦታ ለማንም ሰጥቼ አላውቅም:: በዚህ የጊታር ዜማ አንድ ቀን ወደ ጥልቁ ምስጢር ትገባለህ' አለኝ::»

«ሰውየውን ታውቀዋለህ እንዴ?»



«ኧረ አላውቀውም:: ግን ...ጊታሩን ሲሰጠኝ «ስፈልግህ ነበር! በመጨረሻም አገኘሁህ» ብሎኝ ነበር:: ለምንድን ነበር የምትፈልገኝ? ብለው ይህን ጊታር ልሰጥህ' ብሎኝ ከፊቴ ተሰወረ::

«ሰብድ መሆን አለበት:: ወይም የጊታር አፍቃሪ ራስታ ወይም ደሞ ሾጥ ያደረገው መሆን አለበት» አለችው::

«እኔ'ጃ:: ሰውየው ሽማግሌ ነገር ነው:: ቢሆንም ጊታሩን አልጥልበትም:: ላምጣው::»

የረሳውን ጊታር ይዞ ተመለሰ::